# በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና

## ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

**የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት**

**የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር**

**ከ2013-2014ዓ.ም የአማርኛ ቋንቋ ማጠቃለያ ፈተናዎች የይዘትተገቢነት ግምገማ በጉራጌ ዞን እዣ ወረዳ በየዋኸንየ አጠ/2ኛ/ደ/ እና መሰናዶ ትምህርት ቤት በዘጠነኛ ክፍል ተተኳሪነት ለሁለተኛ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት**

**በ**

**ሞገስ አዲስ**

**ነሐሴ 2016 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

# ከ2013-2014ዓ.ም የአማርኛ ቋንቋ ማጠቃለያ ፈተናዎች የይዘት ተገቢነት ግምገማ በጉራጌ ዞን እዣ ወረዳ በየዋ'ሽንየ አጠ/2ኛ/ደ/ እና መሰናዶ ትምህርት ቤት በዘጠነኛ ክፍል ተተኳሪነት

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የድኅ ረምረቃ መርሃ ግብር ለሁለተኛ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት

በ

በሞገስ አዲስ

ለ

ፕሮፌሰር ጌታሁን አማረ

ነሐሴ 2016ዓ.ም

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር ለሁለተኛ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት በጉራጌ ዞን ከ2013-2014 ዓ.ም ለዘጠነኛ ክፍል በተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ ማጠቃለያ ፈተናዎች የይዘት ተገቢነት ግምገማ፣ በሚል እርዕስ በተግባራዊ ስነልሳን የአማርኛ ቋንቋን ማስተማር መርሃ ግብር የሁለኛ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት በሞገስ አዲስ የቀረበው ይህ ጥናት የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና የወጥነት መስፈርት ስለማሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል፡፡

## የፈተና ቦርድ አባላት

የአማካሪ ስም-------------------------- ፊርማ----------------ቀን----------

የውስጥ ፈታኝ ስም------------------- ፊርማ---------------ቀን----------

የውጭ ፈታኝ ስም ------------------------------ ፊርማ-------------ቀን---------

## ማረጋገጫ (Declaration)

በጉራጌ ዞን እዣ ወረዳ በየዋሸንየ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከ2013-2014 ዓ.ም ለዘጠነኛ ክፍል በተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ ማጠቃለያ ፈተናዎች የይዘት ተገቢነት ግምገማ፣በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር በተግባራዊ ስነ-ልሳን የአማርኛ ቋንቋ ማስተማር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ ወጥ ስራ መሆኑንና የተጠቀምኳቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢዎች የተደረጉና የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥናቱ ህጋዊ የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን በፊርማ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ሞገስ አዲስ

ፊርማ-------------------------------

ቀን-----------------------------------

# ምስጋና

ከሁሉም አስቀድሜ ስናፍቀውና ሳቅደው የነበረውን ሁለተኛውን የህይወቴ ምዕራፍ እውን እንዲሆን ላደረጉ ለልዑል እግዚያብሄርና ለእናቱ ለቅድስት ድንግል ማሪያም ምስጋና ይገባቸው፡፡ በመቀጠልም ይህ ጥናት ከዚህ እንዲደርስ ሳይሰለቹና ሳይታክቱ ጥልቀት ያለው አስተያየት በመስጠት፣ ስህተቶችን በማረም የተለያዩ ምክረ ሀሳቦችን ለሰጡኝ አማካሪየ ፕሮፌሰር ጌታሁን አማረ  ምስጋናየ የላቀ ነው፡፡ እንዲሁም ትልመ ጥናቴን በማስተካከል መስመር ላስያዙልኝና ስለምርምር የተሻለ ፅንስ ሀሳብ እንዲኖረኝ ላበረከቱልኝ ብርሃኑ ንጌሴ፣ ሀምዱ መሀመድ ምስጋናየ ይድረሳቸው፡፡ ከዚህም በመቀጠል ይህን ጥናት ስሰራ ሁሌም ከጎኔ በመሆን በገዘብ፣ በሃሳብና በቁሳቁስ የምትችለውን ሁሉ ላደረገችልኝ ባለቤቴ ማርታ ጌትነት ምስጋና ይደረሳት፡፡ በመጨረሻም ለጥናቱ የሚያስፈልጉ የተለያዩ ሰነዶችን ለተባበሩኝ እና ለጥናቱ የሚሆኑ መረጃዎችን ለሰጡኝ የየዋሽንየ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን ጥሩሀ አበበ  እና ጠብቀው ሙሉ ምጋናየ ይድረሳቸው፡፡

# አጠቃሎ

*የዚህ ጥናት አላማ በጉራጌ ዞን በእዣ ወረዳ በየዋኽንየ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለዘጠነኛ ክፍል ተዘጋጅተው የቀረቡ አማርኛ ቋንቋ የማጠቃለያ ፈተናዎችን የይዘት ተገቢነት መገምገም ነው፡፡ ጥናቱ አይነታዊ የአጠናን ዘዴን የተከተለ ሲሆን ገምጋሚ የምርምር ንድፍን መሰረት አድርጎ ተሰናድቷል፡፡ የንሞና አመራረጡ አመቺ ስልትን የተከተለ ነው፡፡በፈተና የሰነድ ፍተሻ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት የተገኙትነን መረጃዎች መተንተን ተችሏል፡፡ ትንተናዎቹም በገለጻዊና በትረካዊ መልክ ቀርበዋል፡፡፡፡ የጥናቱ ግኝቶችም እንደሚያሳዩት የተዘጋጁት ምዘናዎች የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ በሚገባ የማይመዝኑ፣የአደረጃጀት ችግር ያለባቸው፣ አውዳዊ ያልሆኑ፣ መስፈርቶች ያልተዘጋጁላቸው፣ ከችሎታ መለኪያ ፈተና አዘገጃጀት መርሆዎች አንፃር ውስንነት ያለባቸው እንደሆኑ መረጃዎቹ አመላክተዋል፡፡ ስለሆነም የሚዘጋጁት የቋንቋ ፈተናዎች ከመርሃ ትምህርቱና መማሪያ መፅሀፉ ጋር ያላቸው ትስስር የተሻሉ ቢሆንም ሁሉንም የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በትክክል አካቶ ከማቅረብ አንፃር፣ የተመረጡት የይዘቶች ተገቢነት፣ አደረጃጀት፣ ነጠላ ከመሆን፣ በአውድ ከመቅረብ፣ ከማሳሳት ሀይል፣ በጥያቄዎቹ ግንድ ላይ ከመቅረብ፣ ሁሉን አካታች ከመሆን፣ ካላቸው የቁጥብነት ሁኔታ፣ ውስንነቶች እንዳለባቸው መደምደሚያ ላይ የተደረሰ ሲሆን የቀጣይ የመፍትሄ ሃሳቦችም ተቀምጠዋል፡፡*

## ማውጫ

ይዘት ገጽ

ማረጋገጫ (Declaration) ........ iv
ምስጋና ........ 1
አህፅሮተ ጥናት ........ 1
ምዕራፍ አንድ ........ 1
መግቢያ ........ 1
1.1.የጥናቱ ዳራ ........ 1
1.2.የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 8
1.3 የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች ........ 10
1.4 የጥናቱዓላማ ........ 10
1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 10
1.6. የጥናቱ ወሰን ........ 12
1.7. የጥናቱ ውስንነት ........ 12
ምራፍ ሁለት ........ 14
የክለሳ ድርሳናት ........ 14
2.1 የቋንቋ ፈተና ንድፈ ሐሳብ ........ 14
2.2. የቋንቋ ፈተና ዓይነቶች ........ 15
2.2. 1 የችሎታ መለኪያ ፈተና (Achievement test) ........ 16
**2.2.2 የይዘት ተገቢነት ........ 17**
2.3 የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት ........ 17
ምዕራፍ ሦስት ........ 21
የአጠናን ዘዴ ........ 21
3.1 የጥናቱ አይነት ........ 21
3.2. የጥናቱ ንድፍ ........ 22

3.3 የመረጃ መሰብሰብያ መሳሪያዎች ........ 22

3.3.1 የሰነድ ፍተሻ ........ 22

3.3.2 ቃለ መጠይቅ ........ 23

3.4 የመረጃ አተናተን ዘዴው ........ 23

3.5. የምርምሩ ስነ- ምግባር ........ 23

ምዕራፍ አራት ........ 24

የመረጃ ትንተና ማብራሪያዎች ........ 24

4.1.1 ከይዘት አካታችነት አንጻር የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........ 34

4.1.2 ከፈተና እቅድ ሰንጠረዥ አንፃር የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........ 35

4.1.3 ከይዘት ተገቢነት አንፃር የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........ 36

4.1.4 የቀረቡት የቋንቋ ጥያቄ ይዘቶች ካላቸው የቁብነት ደረጃ አንፃር የተደረገ ትንተና ........ 37

4.1.5. ከቋንቋ የትምህርት ይዘት ቅለትና ክብደት መረጃዎች ትንተና ........ 38

4.1.6. ከቋንቋ የይዘት አውዳዊነት በተመለከተ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........ 39

4.1.7. ከቋንቋ ጥያቄዎች የየይዘት አወቃቀር ( አደረጃጀት) አንፃር የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........ 41

4.1.8 የጥያቄዎቹን ማዕከላዊ ሀሳብ በግንዱ ላይ ከማቅረብ አንጻር የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........ 42

4.1.9. የቋንቋ ጥያቄዎች የይዘት ተገቢነት በነጠላ ሃሳብ ከመሆን አንፃር የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........ 43

4.1.10. የቀረቡት የቋንቋ ይዘቶች ከአሳሳች ተገቢነት አኳያ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........ 44

4.1.11.የተዘጋጁት የቋንቋ ፈተናዎች የይዘት ተገቢነት ካላስፈላጊ ጥቆማ የወጡ ጥያቄዎችን መፈተሸ ........ 45

4.2 የጥናቱ የውጤት ማብራሪያ ........ 47

ምዕራፍ አምስት ........ 50

ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና የመፍትሄ ሀሳቦች ........ 50

5.1 ማጠቃለያ ........ 50

5.2 መደምደሚያ ........ 52

5.3 የመፍትሄ ሀሳቦች ........ 53

አባሪዎች ........ 61

## የሠንጠረዥ ማውጫ


ሰንጠረዥ1፡-ለዘጠነኛ ክፍል በተዘጋጀው መርሃ ትምህርት ውስጥ የትምህርት ይዘቶች ውክልና ሲታይ ........................................................................................................................................ 25

ሰንጠረዥ2፡ በመማሪያ መፅሃፉ ውስጥ የተካተቱት ቋንቋ ይዘቶችን መጠንን የሚያሳይ መረጃ............ 26

ሰንጠረዥ3፡- በመርሐ ትምህርቱ፣በመማሪያመፅሀፍቱና በፈተናዎች መካከል ያሉት ይዘቶች ግንኙነት በቁጥርና በመቶኛ ........................................................................................................... 27

ሰንጠረዥ 4፡በሁለቱም አመት በተዘጋጁት ፈተናዎች ውስጥ ምን ምን የቋንቋ ይዘቶች ተካተዋል........ 29

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1.የጥናቱ ዳራ

ቋንቋ አሁን ባለንበት ክፍለ ዘመን ቁልፍ የመግባቢያ መሳሪያና እንደ አንድ ትልቅ የጥናት መስክ ተደርጎ ትምህርታዊ፣ ምርምራዊ፣ አስተዳደራዊ ተግባራትን በአግባቡ ለማከናዎን ያለው አስፈላጊነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል፡፡ ስለ ቋንቋ ከሚጠኑ ጉዳዮች ውስጥ ደግሞ አንዱ ምዘና ነው፡፡ አሁን ካለው ዘመናዊ አሰተሳሰብ አኳያ በቋንቋ መማር ማስተማር፣ የምዘና ስልት፣ አተገባበር ብለም ፍልስፍና ካለፉት ዘመናት አንፃር መሻሻሎች ቢታዩበትም አሁንም ክፍተቶች ያሉበት መሆኑን በየጊዜው የሚደረጉ አውደ ጥናቶች እንደሚጠቁሙ (Tamen፣ 2007) ያስረዳሉ ፡፡ ቋንቋን መፈተንና መመዘን ከቋንቋ መማር ማስተማር ተነጥሎ ሊታይ የማይችል አንዱ የመማር ማስተማር ሂደት ሲሆን በቋንቋ ትምህርት እድገትና ጥራት ላይ የራሱ የሆነ አወንታዊ ገፅታ አለው (Tamen፣2007)፡፡ ምዘናን በተመለከተ የዘርፉ ምሁራን እንደየ ፍልስፍ ናቸው ደረጃ፣ እንደየ ግንዛቢያቸው ብሎም እንደየ ትምህርት ደረጃቸው በተለያየ መልክ ሲፈርጁት ይሰተዋላል፡፡

የቋንቋ ምዘና አሁን ካለንበት ደረጃ ለመድረስ ውስብስብ የሆነ በርካታ ታሪካዊ ሂደቶችን አልፎ የመጣ ነው፡፡ የተለያዩ የዘርፉ ምሁራን የምዘና ታሪካዊ ሂደቶችን በተመለከተ የሚያዩበት እሳቤና አመዳደብ የተለያ ነው፡፡የቋንቋ ፈተና የሚታይበት ሁኔታ በርካታ ስለሆነ ከታሪካዊ ዳራው መጀመር ተገቢ ነው፡፡

Heaton (1988) የፈተና ታሪካዊ እድገትን በተመለከተ አራት የቋንቋ ፈተና የእድገት ደረጃዎች ወይም ዘዴዎች እንዳሉ ይገልጻሉ፡፡ እነሱም፡- ድርሰት ወትርጉም ዘዴ (The Essy Test)፣ መዋቅራዊ ዘዴ (The Struacture approach)፣ ውህዳዊ ዘዴ (The Intractive Approch)፣ ተግባቦታዊ ዘዴ(Communicative Approch)፡፡ Spolsky (1976) የፈተና የእድገት ደረጃዎችን በሶስት ሲከፍቸው ፤ Madson(1983)ከ Spolsky ሃሳብ ጋር ይስማማሉ፡፡ በሌላ በኩል ጫንያለው (2010) (Weir and shaw፣2005) ን ጠቅሰው እንደገለፁት ታሪካዊ ሂደቱም በአራት መሰረታዊ የጊዜ ቀመር (ዘመን) ከፍለው ይመለከቱታል፡፡ እንደ ተመራማሪዎቹ አገላለፅ

የ21ኛው ክፍለ ዘመን የካምብሬጅ የቋንቋ ምዘና ፍልስፍና ብቃት ማረጋገጫን መሰረት ተደርጎ የተከፈለ እንደሆነ ይገልፃሉ። በዚህ ምርምር የምንመለከተውም ጫንያለው (2010) (Weir and shaw፣2005) ጠቅሰው ያቀረቡትን የፈተና ታሪካዊ ዳራ ነው። እነዚህ ዘመናት እ.ኤ.አ (ከ1800-1945)፣ (ከ1945-1970)፣ (ከ1975-1984) እና ከ1984-21ኛው ክፍለ ዘመን በሚል ተከፍለው ይቀመጣሉ።

የመጀመሪያው የቋንቋ ትምህርት ምዘና ታሪካዊ ዘመን የሚባለው ከ1800-1945 ያለውን ሁሉ የሚያጠቃልል ሲሆን ከባህሪያዊ ፍልስፍና (Behavraile school of thougth) ጋር የተዛመደ ነው። ከ1800-1945 በፊት የነበረው የቋንቋ ትምህርት የምዘና ሂደት ከሚጠበቀው የብቃት ደረጃ ላይ የደረሰ አልነበረም (Weir 2003፣ 2005)። የባህሪያዊያን አቀንቃኞች እንደሚሉት ምዘናው ውበት ያላቸውን የሰዋስው ቃላት እንዲያውቁ ይደረግ ነበር ይላሉ። የባህሪያውያን ስልተ ትወራ በቋንቋ ምዘና (ፈተና) የትኩረት ነጥቦች ብለው የጠቁሚቸው አንድን ቋንቋ ወደ ሌላ ቋንቋ ትርጉም መስጠት ነበር። ከፈረንሳይ ወይም ከጀርመነኛ ወደ እንግሊዘኛ ትርጉም በመፃፍ ለሶስት ሰዓት እንዲሰሩ በመስጠት የእንግሊዘኛ ቋንቋ ሰዋስው ይዘትን ያካተተ ምዘና መስጠት የሚል ነበር (Weir፣2005)። በተጨማሪም ከቅድመ ሳይንሳዊ ምዘና ዘመን በፊት የነበረው የቋንቋ ምዘና አይነት የተማሪዎችን የመማር ዕድገት ለማሳደግ መነሻ ያደርግ የነበረው ጽንሰ-ሃሳቦችን በመሸምደድ ላይ በመሆኑ የተማሪዎችን የሽምደዳ ዕውቀት ከማሳደግ ውጭ በሌሎች ክሂሎችና የእውቀት ዘርፎች ላይ ለውጥ ሊያሳይ አለመቻሉን (Nunan 1989:12) ጠቁመዋል።

የባህሪያዊያን አቀንቃኞችም የሚሰጡት የቋንቋ ምዘናዎች የተማሪዎችን የመማር ብቃት ሊያመጣ በሚችል መሰረት ላይ የቆመ አይደለም ሲሉ ተቃራኒ አስተሳሰቦች ሊነሳባቸው ቻለ። ስለሆነም በወቅቱ በትምህርቱ ላይ ሊለኩ የሚችሉ ውጤቶችን ትኩረት በውስጠት ቅደም ተከተላዊ ሽምደዳዎችን በመተው የቋንቋ እውቀትን ማጎልበት እንደሚገባ ስምምነት ላይ ተደረሰ ሲሉ (weir and shaw፣2005) ይገልፃሉ። በነዚህም የስነልቦና ባለሙያዎች ቀድም ሲል የነበረውን በቃል የማንበብና መልሶ የመናገር ምዘና ወደ አንብቦ የመረዳት ምዘና እንዲሸጋገር አድርገዋል (Weir 2005፣ Gipps፣1996)።

ሁለተኛው የቋንቋ ምዘና ታሪክከ1945-1970ዎቹ ያለውን ጊዜ የሚያካልል ሲሆን የአዕምሮአዊያን ግንባታ የመማር ንድፍ ሃሳብ (cognitive construction theories) አቀንቃኞች

ተፅዕኖ ጎልቶ የወጣበት ዘመን እንደነበር (ጫንያለው 2010) (Weir 2005)ን ጠቅሰው ያስረዳሉ፡ ፡ የዚህ ፍልስፍና ትኩረት የቋንቋ ምዘና በጥልቀት ማሰብን የሚያሳይ መሆን አለበት የሚል ነው። በ1960 በመስኩ ምሁራን በተደረገ ጥናት ከእንግሊዘኛ ወደ ሌላ ቋንቋ በመተርጎም መመዘን በተማሪዎች ላይ ያመጣው ለውጥ የለም የሚል ሃሳብ ተነሳ። ቋንቋን በውህደትና በጥምረት በማስተማር መመዘን ነው ለውጥ ማምጣት የሚችለው። የመዋቅራዊ ስነልቦና አቀንቃኞች የቋንቋ ምዘና፣ የተማሪዎችን ሰዋስዋዊ የቋንቋ ዕውቀትና የስነልሳን ብቃት የሚያጠናክር መሆን አለበት በማለት ሃሳባቸውን ገለጹ።

ጫንያለው (2010) እንደሚገልፁት የቪጎትስኪ ፍልስፍና ደጋፊዎችም በ1995 አሁንም ከላይ የቀረቡት የአዕምሮታዊያን የቋንቋ የምዘና ስልቶች ተማሪዎችን ከሽምደዳ የሚያወጣና ግንዛቤን የሚያጎለብት አይደለም ሲሉ ነቀፋ ደረሰባቸው። እንደገና የፈተና ቦርድ መቋቋም አለበት ሲሉ ወሰኑ። በቀረበው ውሳኔ መሰረት ኮንሰስሽፕ የተባለ የምዘና ቡድን እንዲቋቋም ሃሳብ አቀረቡ። ይህ ደግሞ በካምብሬጅ የምዘና ቦርድ ተቀባይነት አግኝቶ በስራ ላይ ዋለ። ጫንያለው (2010) Hanson(1993)ን ጠቅሰው እንደገለፁት ከ1970 በኂላ የምዘናውም አይነት ሆነ የማስተማር ዘዴው እየተቀየረ መጣ። የምዘናው የትኩረት አቅጣጫም ውጤትን መሰረት ያደረገ መሆን እንዳለበት የመስኩ ምሁራን ሃሳብ አቀረቡ። ምዘናውም በጊዜ ሂደት ዘመናዊ ስልትን እየተላበሰ መጣ። ስለዚህ ምዘናው በተማሪዎቹ ላይ የባህሪም ሆነ የአስተሳሰብ ለውጥ ባለማምጣቱና ችግር ፈች ባለመሆኑ የምዘና ባለሙያዎችን እያስጨነቃቸው መጣ። ከዚህም ችግር ተነስተው በተማሪዎች ስነ-ልቦና ላይ ያተኮረ ምዘና መስጠት ተጀመረ። ምዘናውም ቀስበቀስ የራሱን የአመዛዘን ስርዓት ሊከተል እንደቻለ ባለሙያዎች ያስገነዝባሉ። ስነ ልቦናዊ ምዘናውም ቢሆን የሚፈለገውን ችግር መፍታት ባለመቻሉ እንደገና የመማሪያ ቴክስት ማዘጋጀት ተጀመረ። የሽምደዳ ምዘና በተማሪዎች ላይ ለውጥ ባለማምጣቱ በገለፃና በውይይት ምዘና ሊተካ ቻለ። ስለሆነም መማሪያ መፅሃፍና ምዘናዎች ውህደት እንዲራቸው ተደረገ።

ሶስተኛው የምዘና ታሪክ የምንለው ደግሞ ከ1975-1984 ዘመን ያለውን የሚያጠቃልል ሲሆን ፅንሰ ሃሰቡ በቴክስት ስነ- ልቦናዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ አውዶች በቋንቋ ትምህርት ምዘና ያላቸው ሚና የሚቃኝበት ነው ሲሉ ጫንያለው (2010) (Weir 2005፣ Gipps፣1996)ን በመጥቀስ ይተነትናሉ። ይህ ጊዜ ልእለ አዕምሮአዊያን በትምህርት ምዘና ላይ የነበራቸው ሚና የቀነሰበት እና ማህበራዊ ግንባታ የመማርና የምዘና ንድፍ ሃሳብ እያደገ የመጣበት ወቅት ነበር፡

፡ ዘመኑ ከግንዛቢያዊ እይታ ባሻገር መሰረቱን የጣለው ማህበራዊ እይታ አንብቦ የመረዳት የቋንቋ ምዘና ላይ ነበር፡፡ የሚማሩትም ተማሪዎች ወቅቱ የሚጠይቀውን ቴክኖሎጅ ተጠቅሞ አለምን ለመቀየር በሚደረገው ጥረት ሁሉ ድረሻውን የሚወጣ እንዲሆን ነበር፡፡ የዚህ ዘመን የቋንቋ ምዘና ቅርፁም ሆነ ይዘቱ ስፋት ያለው ሲሆን የመጨረሻ ግቡም መላውን የህብርተሰብ ክፍል ተጠቃሚ ማድረግ ነው (Smith 1987)፡፡ በዚሁ ወቅት የሰው ልጅ አዕምሮ ከተለያዩ ማህበራዊና ባህላዊ ፅንሰ ሃሰቡች የተዋቀረ አለመሆኑን የሚከራከሩ ግባታውያን (constactivism) ስልተ ትወራ ብቅ ማለቱን ጀመረ፡፡ ምዘና እውን የሚሆነው በመደበጀው ብቻ ሳይሆን በኢመደበኛ የምዘና ስልት እንደሆነ ለመሞገት ሞከሩ፡፡

ይህ የቋንቋ የመማር ማስተማርና የምዘና ዘመን በባህሪያዊያን፣በአዕምሮታውያን፣ ማህበራውያንን በአንድ ላይ ከማሰባሰቡም በላይ በተለያዩ ማህበራዊ ትስስሮች የሚነሱ ውዝግቦችን ይዘጋል የሚል እሳቤ ነበር፡፡ በመጭረሻም ማኅበራዊ እድገት እንደገና በእጅጉ ያንሰራፋበት፣ ብዙ ተመራማሪዎች የቋንቋ ሰዋስው ማስተማሪያ ዘዴዎችን፣ የምዘና ስልቶችን የይዘት፣ አካታችነትንና የመርጃ መሳሪያ አጠቃቀሞችን ሁሉ በተሻለ መልኩ መጠቀምና ውጤታማ ለመሆን የተቻለበት ጊዜ ነበር (Bachman፣1996) ፡፡

አራተኛው የፈተና ዘመን ከ1984-21ኛው ክፍለ ዘመን ያለውን ያካትታል፡፡ ይህ የፈተና ስልት ተግባቦታዊ ዘዴ ሲሆን ከውህዳዊ ዘዴ ጋር ይመሳሰላል፡፡ ሁለቱም ዘዴዎች ከቅርፅ እና ከመዋቅር ይልቅ ለአጠቃላዩ የንግግር ውጤትና ፍቺ ትኩረት ስለሚሰጡ ይመሳሰላሉ፡፡ ይሁን እንጂ የተግባቦታዊ ፈተና ዘዴ የቅድሚያ ትኩረት ተፈታኙ ቋንቋውን በተግባቦት ውስጥ እንዴት እንደሚጠቀምበት መመርመር ነው (Heaton ፣ 1988፣18-19)::

ከዚህ በላይ ከቀረበው የምሁራን ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው የመጀመሪያው የቋንቋ ምዘና ዘመን ከማህበራዊ ፍልስፍና አስተምሮ ጋር የተቆራኘ ሲሆን የትኩረት ነጥቡ ከአፍ መምቻ ቋንቋ ወደ እንግሊዘኛ ቋንቋ እንዲተረጎሙ የሚያዝ ነበር፡፡ ይሁንና በተማሪዎች ግላዊ የመረዳት ብቃት መሰረቱን የጣለ ሳይሆን ሽምደዳን ብቻ የተከተለ ስለነበር የራሱ የሆኑ ጉድለቶች እንደነበሩበት መረዳት ይቻላል፡፡ የተማሪዎችን የእውቀት ክፍተት ለመሙላት ተብለው ትኩረት የሚሰጣቸው ደረቅ ሰዋስዋዊ ትርጉም ስለነበሩ በተማሪዎች የቋንቋ ግንዛቤ ላይ አወንታዊ ገፅታ አለመኖሩን ያሳያል፡፡ የሰዋስው ትምህርትና ምዘና በተደራጀ ሁኔታ ከህይማኖት እሳቤ ወጥቶ

ወደ መንግስት ትምህርት ቤት በመምጣት እራሱን የቻለ የጥናት መስክ መሆን እንደቻለ መረዳት ይችላል፡፡

ይህንን ክፍተት ለመሙላት ሁለተኛው የምዘና ዘመን ብቅ ማለት ጀመረ፡፡ ዘመኑም በቋንቋ ምዘና መሰረት ያተኮረው የአዕምሮታዊያን አቀንቃኞች ሃሳብ ጎልቶ የወጣበት ዘመን ነበር፡፡ ስለሆነም ባህሪያውያንን በመቃረን የቋንቋ ምዘናን ከሽምደዳ ይልቅ በጥልቀት ማሰብን መሰረት ያደረገ መሆን አለበት የሚል ንድፈ ሀሳብ ይዘው እንደመጡ ያሳያል፡፡ በቋንቋ ፈተና ከክሂሎችና ከስነ ፅሁፍ የትምህርት ይዘቶች ጋር ተዋህዶ የቋንቋ መዋቅርን እና የስነ-ልሳንን እውቀት ማዳበር እንደሚያስፈልግ ስምምነቶች ቢፈጠሩም የቪጎትስኪ ደጋፊዎች ደግሞ አሁንም ያለው የምዘና ስልት ከሽምደዳ ያልወጣ በመሆኑ መሻሻል አለበት የሚል ሀሳብ በመሰንዘሩ ሌላ የምዘና ቦርድ እንዲቋቋም ስምምነቶች ተደረጉ፡፡

በመሆኑም ማህበራዊና ግንባታዊ የቋንቋ ምዘና የሚባል ፍልስፍና ገኖ መውጣቱን ቀጠለ፡፡ ይህም ዘመን ከሌሎች በተለየ መልኩ ለቋንቋ ምዘና የበለጠ ትኩረት የተሰጠበት ሲሆን እውቀት ማህበራዊ እይታ እንዲኖረው ማድረግ ችሏል፡፡ በመጨረሻም የቋንቋ ምዘና አለማቀፋዊ እውቀትን የሚያተርፍ በመሆን ችግር ፈቺ ብሎም ማህበራዊ፣ ክህሎታዊ፣ ውህዳዊና አውዳዊ የሰዋስው ይዘትና አቀራረብን ይዞ መዘጋጀት አለበት የሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ተችሏል፡፡ አሁን እየተገለገልንበት ለምንገኘው የቋንቋ ትምህርት መፈጠር ምክንያት የሆነው ጥንታዊ የሰውስው የምንለው ነው፡፡ ሀገራችን የሰዋውስውን ትምህርት በስነ- ትምህርት ለመስጠት የወሰደችው ከመዋቅራዊ የስዋስው ውጤት ነው፡፡ ስለሆነም አሁን ያለው የቋንቋ የምዘና ሂደት ዘመን ወለድ ከምንለው የምዘና ሂደት መሆኑንና አለመሆኑን በጥናቱ ለመፈተሽ ይሞከራል፡፡ በዚህ ጥናት አሁን ያለው የቋንቋ ምዘና አግባብነትም ምን ሊመስል እንደሚችል በጥናቱ ትኩረት የሚሰጣቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡

አግባብነት በቋንቋ ትምህርት፣ በስነ-ልቦናና በስነ-ትምህርት ምዘና ውስጥ በጣም ጠቃሚ ጉዳይ ተደርጎ ይታያል፡፡ ምክንያቱ በፈተና ትክክለኛነት ላይ የሚያተኩር ጉዳይ በመሆኑ ነው (Messick,1995)፡፡ ስለሆነም በዚህ ጊዜ አግባብነት ከፈና ውጤቶች ብቻ ሳይሆን ከፈተና ትክክለኝነት ጋር በከፍተኛ ሁኔታ የተዛመደ ፅንሰ ሀሳብ መሆን ያስረዳሉ፡፡ በአንድ ፈተና ውስጥ ብዙ አይነት እውቀትና ክህሎትን መለካት የሚችሉ ጥያቄዎች ይኖራሉ፡፡ Messick (1989፡13) እንደገለፁት “ተገቢነት የፈተና ወይም ሌላ የምዘና አይነት ውጤቶችን መሰረት

በማድረግ የሚሰጡ ማጠቃለያዎች ወይም የሚከናወኑ ድርጊቶች በቂና ተገቢ መሆናቸውን በተጨባጭ ማስረጃ በንድፈ ሀሳባዊ ትንታኔዎች የመደገፋቸውን መጠን የማረጋገጥ የተቀናጀ ግምገማዊ ፍርድ ነው" በማለት ገልፀውታል፡፡ አንድን ምዘና ትክክል ነው ለማለት የተመደበለት ጊዜ፣ የይዘቱ መረጣ፣ ትክክለኝነት፣ አውዳዊነት ሁሉ ትኩረት የሚገባቸው ነገሮች ናቸው ይላሉ፡፡

የፈተና አቀራረብ የይዘት ተገቢነት እንዳይኖር ሰበብ ከሚሆኑ ሁነኔታዎች መካከል አንዱና ዋንኛው ነገር አንድን ፈተና በተሳሳተ ሁኔታ መጠቀም እና ለማካተት መሞከር ነው፡፡ አንድ ፈተና አግባብ የሚሆነው ለተዘጋጀለት አላማ ብቻ ሲውል ነው፡፡ ስለሆነም ከተቀመጠው አላማ ውጭ የሚጨምር ማንኛውም ጉዳዩ በፈተናው ተገቢነት ላይ አግባብ ያልሆኑ ትንታኔዎችን እና አሳቤዎችን ሊያስከትል ይችላል፡፡ በሌለሳ በኩል አግባብ ያልሆነ ጉዳይ የምንለው ደግሞ ተገቢ ያልሆነ የፈተና ይዘት ምርጫ ማካተት ነው፡፡ ይህን ለማስወገድ የፈተናው ጥያቄዎች የፈተና አዘገጃጀት መርህን ተከትለው መሰናዳት አለባቸው፡፡ በተመሳሳይ በፈተናው ላይ የግልፅነት መጓደል፣ የተሳሳተ መረጃና በፈተናው ላይ የሚኖር ጥላቻ አግባብነት እንዳይኖር ዋና መሰናክል ሊሆኑ ይችላሉ (Henning 1987)፡፡

Bachman (1990) የቋንቋ ምዘና መሰረታዊ ግንዛቤ ውስጥ የMessick (1989)ን የአግባብነት ፅንሰ ሀሳብ ተጠቅመውበታል፡፡ ይህን ሁኔታ ተከትሎ በአሁኑ ጊዜ በቋንቋ ፈተና ውስጥ አግባብነትን እንደ አሀዳዊ እሳቤ መመልከቱ በስፋት ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ ለምሳሌ Weir (2005) የአግባብነት ስያሜ የአውድ አግባብነትን (context validity)፣ የንድፈ ሀሳብ-ተኮር አግባብነትን (theory-based validity)፣ ውጫዊ አግባብነትን (external validity) እና የሚያስከትለውን ተፅእኖ አግባብነትን (consequential validity) አካቶ የሚይዝ ጥቅል መጠሪያ አድርገው ተጠቅመውበታል፡፡ የአዘጋጁት ማህበረ-ግንዛቤያዊ ማዕቀፍ ጥንታዊውን ይዘት ተኮር (contnent based)፣ "ችሎታ-ተኮር" (trait-based) እና"ተግባር ተኮር" (task-based) ዘዴዎችን የሚያቀራርብ ነው (Weir, 2005)::

አንደ Weir (2005) ገለፃ፣ እነዚህ ሶስት ውስጣዊ የቋንቋ ፈተና ጉዳዮች የችሎታ አግባብነት (construct validity) አዲስ ፅንሰ-ሀሳባዊ እሳቤን ይመሰርታሉ፡፡ ፈተናውም በይበልጥ ከይዘቱ አቀራረብና አግባበብነት አኳያ ይተነተናል፡፡ የችሎታ አግባብነትን (construct validity) የአውድ አግባብነት፣ የግንዛቤና የይዘት አግባብነት በአንድ ላይ አጣምሮ ይይዛል፡፡

የአውድ አግባብነት አንድን የቋንቋ ተግባር በተሳካ ሁኔታ ለማከናወን የሚያስፈልጉትን የቋንቋና የይዘት ግብዓቶችን፣ እንዲሁም የሚፈለገውን ክንውን የሚገልፁ የተግባሩ መቼት ባህሪያትን ያመለክታል (Weir, 2005):: ይለቁንስ በማህበራዊ አውድ ውስጥ ይከናወናሉ፡፡ ከምዘና አንፃር፣ የፈተና ተግባራት መግለጫ ቃላት ተግባሩ የሚከናወንበትን አውዳዊ ጉዳዮችን ያመለክታሉ፡፡ እነዚህ ጉዳዮች ደግሞ የተወሰኑ ግንዛቤያዊ ሂደቶችን እንደሚመልሱ፣ እንደሚያቅዱና እንደሚያከናውኑ ይወስናሉ (Madson, 1983)፡፡

ከነዚህ የአግባብነት አይነቶችና መስፈርቶች መካከል በዚህ የጥናት ክፍል የበለጠ ትኩረት የሚደረግበት የአውድ፣ አቀራረብ፣ ሁሉን ይዘቶች አካታችነት፣ ይቶች የቀረበበት መንገድ፣ የግንዛቤ እና እውናዊ አግባብነት ናቸው፡፡ የፈተና ይዘት አላማን መሰረት በማድረግ የችሎታ መለኪያ ፈተና ታሳቢ ያደርጋል፡፡ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የቋንቋ ፈተና የራሱ የሆነ የይዘት አመራረጥ ተገቢነትና አላማዎች አሉት፡፡ አላማውም የታላሚውን ቋንቋ የቃላት አደረጃጀት፣ የስርዓት ተገቢነት፣ የምዕላዶች ቅንጅት፣የስነ-ፅሁፍ፣የክሂል፣ ቋንቋን በትክክል መግለፁን፣ የይዘት ንሞና አመራጥ፣ የሀረግና የአረፍተ ነገሮች አግባብነትና ሀሳብን ያለግድፈት ለመግለፅ ፋይዳው የጎላ ነው(Heaton,1990)::

ከላይ ከቀረበው ሃሳብ መረዳት እንደሚቻለው አንድን ፈተና መገምገም በአንድ ፈተና ውስጥ ያለውን አሉታዊና አወንታዊ ተፅኖዎችን በመለየት በቀጣይ ለሚኖረው መማር ማስተማርና የፈተና ዝግጅት መሰረታዊ የሆነ ክህሎትና እውቀት ጥሎ ያልፋል፡፡ አንድን ፈተና በትክክል መገምገም ከተቻለ ከግምገማው የሚገኘው ውጤት ለቋንቋ ትምህርት መሻሻልና ተማሪዎችን ምን ያክል እየመዘነን እንደሆነ አጋዥ ናቸው፡፡ በአሁኑ ወቅት ትልቅ ችግር እየሆነ የመጣው ትክክለኛ ምዘና በማዘጋጀት ተማሪዎችን በወጉ መመዘን አለመቻል ነው፡፡ ስለሆነም የቋንቋውን ትህምርት አላማ መሳካትና አለመሳካቱን ማረጋገጥ እየተቻለ አይደለም፡፡ በዚህ ጥናት የሚደረገው ግምገማ ምዘናዎቹ ከስርአተ ትምህርቱ፣ ከመማሪያ መፅሀፉና ከመምህሩ መምሪያ ጋር አያይዞ የቀረበው የትምህርትን ይዘትን ወካይ ንሞናን መሰረት አድረጎ ማቅረቡንና አለማቅረቡን በመተንተን፣ ምዘናው የቋንቋ ይዘት መረጣንና አቀራረብን ተከትሎ መዘጋጀቱን ሙያዊ አስተያየትና የማስተካከያ ሀሳቦችን ከማፍለቅ ላይ ያተኩራል::

ከዚህ በመነሳት የአማርኛ ቋንቋ ማጠቃልያ ፈተናዎች የይዘት ተገቢነት በየዋኸሃንየ አጠ/2/ደ/ት/ቤት በ9ኛ ክፍል ተተኳርነት በሚል ከላይ በተገለፀው ከፈተና ንድፈ ሐሳብ በመነሳት የይዘት ተገቢነት መገምገም ነው፡፡

## 1.2.የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህ ጥናት በጉራጌ ዞን በእዣ ወረዳ በየዋኸንየ አጠ/2ኛ/ደ/ት/ቤት ከ2013-2014 ዓ.ም በተዘጋጁ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ማጠቃለያ ፈተናዎች የይዘት ተገቢነትን መገምገም ነው፡፡ አጥኝው በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ጥናት እንዲያካሂድ በመሰረታዊነት ያነሳሳው ጉዳይ የሚከተሉት ናቸው፡፡

የመጀመሪያው በተለያዩ ጊዚያት የስምንተኛ፣የዘጠነኛ ክፍል እና የ10ኛ ክፍል ክልላዊና ብሄራዊ ለአማርኛ ቋንቋ በተዘጋጁ ፈተናዎች ዙሪያ አቀራብና የይዘት ተገቢነት፣ፈተናዎች የቀረቡት ይዘቶች፣ ከስርዓተ ትምህርቱ፣ ከመርሃ ትምህርቱና ከመማሪያ መፅሃፉ ጋር ያለቸውን ተዛምዶ በተመለከተ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሙያነት ጥናት ተደርጎባቸዋል፡፡ እነዚህም በለጠ (1995) ለዘጠነኛ ክፍል የሚዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ለደረጃው ከቀረበው ትምህርት ጋር ያላቸው ተዛምዶ አግባብነትና ተጠያቂነት የሚል ነው፡፡ ሲሳይ (2007) ከ2001-2007ዓ.ም በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሁለተኛ ደረጃ ማጠቃለያ ፈተና የይዘት ተገቢነትና አቀራረብ ግምገማ፣ ተስፋየ (2000) የአማርኛ አሰልጣኝ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ፍተሻ በትግርይ ክልል በሚገኙ ሶስት የትምህርት ኮሌጆች፡፡ ታለጌታ (2005) የሀገር መከላከያ ሰራዊት ከ2001-2004ዓ.ም ድረስ ለርቀት ትምህርት መርሃ ግብር የቀረቡ የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ብሄራዊ ፈተና ከመማሪያ መፅሃፉ ጋር ያላቸው ዝምድና ለማስተርስ ድግሪ ማሙያነት ተብለው ጥናታዊ ፅሁፎች ቀርበዋል፡፡

የጥናቶቹም ውጤት እንዲያመለክቱት በቋንቋ ትምህርት የፈተና አቀራረብ ላይ ስር የሰደዱ ችግሮች እንዳሉ ነው፡፡ አንዳንዶቹ ደረጃቸውን የጠበቁ የይዘት ተገቢነትና አቀራብ መስተዋሉና ጥያቄዎቹ ለይዘት ትኩረት መሰጠቱን ሲገልፁ ሌሎች ደግሞ አግባብነቱ ላይ ተቃራኒ ሃሳቦችን አንፀባርቀዋል፡፡ የተወሰኑት ደግሞ ክፍተቶችን አግዝፈው ያወጡታል፡፡ ለሰዋስውና ለክሂል ትምህርት ይዘት ትኩረት ያልተሰጡበት ጊዜ እንዳለና በተወሰኑት ጥናቶች ደግሞ ሰዋስውን ከግምት ውስጥ ያስገቡ ናቸው የሚል ገፅታዎች ይታያሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ለስነ-ፅሁፍ የበለጠ ትኩረት ሲሰጥ ለሌሎች የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች የተሰተው ትኩረት አነስተኛ

እንደሆነ ነው፡፡ለምሳሌ በለጠ (1995) ለዘጠነኛ ክፍል በተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ ለደረጃው ለቀረበው ትምህርት ሊመጥን የሚችል የይዘት ተገቢነትና አካታችነት የጎደለው እንደሆነ ያሳያል፡፡ እውነተኛና ትክክለኛ የይዘት ንሞና መረጣ ፈተናው እንዳልተከተለ ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል ሲሳይ (2007) ከ2001-2007ዓ.ም በሀገር አቀፍ ደረጃ ማጠቃለያ ፈተናዎች አቀራረብ ግምገማ በሚል ባቀረበው ጥናት በማጠቃለያ ሀሳቡ እንዳቀረበው ፈተናው የይዘት ውክልና ተገቢነት እንደጎደለው ያሳያል፡፡ ከአመት ወደ አመት የተሰጡት ፈተናዎችን ስናይ የይዘት ውክልና ልዩነቶች ይታያሉ፡፡ እንዲሁም ተስፋየ (2000) የአማርኛ አሰልጣኝ መምህር የተከታታይ ምዘና አተገባበር ፍተሻ በትግራይ ክልል በሚል ባካሄዱት ጥናት ፈተናዎች የይዘት ውክልና ተገቢነታቸው ሲታይ የተሸለ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ታለጌታ( 2005) ከ2001-2004ዓ.ም ለርቀት መርሃ ግብር የቀረቡ የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ብሄራዊ ፈተና ከመማሪያ መፅሃፍቱ ጋር ያላቸው ዝምድና በሚል በቀረበው ጥናት ፈተናው ከመማሪያ መፅሃፍቱ ይዘት ጋር አንፃራዊ ምጥጥኖሽ ቢኖርም በተወሰኑት አመት የቀረቡት ፈተናዎች የይዘት ትክክለኝነትና ውክልና ችግሮች ያሉበት እንደሆነ ያሳያል፡፡

ስለሆነም በአጥኝዎች መካከል የተለያየ የፈተና ትንተና ገፅታዎች ይታያሉ፡፡ ስለዚህ በምሁራኖች መካከል ያለውን የምርምር ክፍተቶች ለማረጋገጥና በአሁኑ ስዓት እየተሰጡ ያሉ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ምን ደረጃ ላይ እንዳሉ ለመገምገም ነው፡፡ ስህተቶቹም ከፈተና አቀራረብ ከይዘት ተገቢነትና አግባብነት አንፃር ሲገመገሙ አካታች አለመሆናቸውና ለፈተና የቀረቡት ጥያቀዎች አብዛኞቹ ከመርሃ ትምህርቱና ከመማሪያ መፅሃፉ ጋር ያልተጣጣሙ እንደሆነ መረዳት ተችሏል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ እንዳጠና ያነሳሳኝ ሌላው ጉዳይ በየዋሽንዬ አጠ/2ኛ/ደ/ት/ቤት በኩል እየተዘጋጁ ለ9ኛ ክፍል በሚሰጡ የአማርኛ ቋንቋ ማጠቃለያ ፈተናዎች ዙሪያ ሲፈተሽ ከዚህ በፊት በተመሳሳይ መልኩ አንድም ጥናት ባለመኖሩና የተማሪዎችን ችሎታ ለመለየት የሚዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ ፈተና የይዘት ተገቢነት ላይ የቀረበበትን መንገድ ምን እንዲመስል ለማወቅና ለማሳወቅ ነው፡፡

በሶስተኛ ደረጃ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ እንዳጠና ያነሳሳኝ ሌላው ነገር የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ይዘቶች በስራ አለም ላይ በደምሳሳው ሲፈተሹ ሁሉንም ይዘቶች ከይዘት ተገቢነት አንፃር ትኩረት ተሰጥጦ ሲሰራ አይስተዋልም፡፡ በትምህርት ቤት ደረጃም የሚሰጡ ምዘናዎች ከዚሁ ችግር

የሚላቀቁ አይሆንም፡፡ ይዘቶችም በአግባቡ ተካተው አለመገኘታቸው፣ ያልተካተቱትን ይዘቶች እንዳሉ ለመለየትና ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሽቆለቆለ የመጣውን የቋንቋ ትምህርት ውጤት ምክንያቱ ምን እንደሆነ ለመለየት ነው፡፡

## 1.3 የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች

1.የተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ከመርሃ ትምህርቱና ከመማሪያ መፅሀፍቱ ጋር ምን አይነት ግንኙነት አላቸው?

2.ከ2013-2014ዓ.ም በቀረቡት ጥያቄዎች ለየትኛው ይዘት የበለጠ ትኩረት የሰጡ ናቸው?

3. የተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ ማጠቃለያ ፈተናዎች የይዘት ተገቢነት መርሆዎችን ያሚሉ ናቸው?

4. የተዘጋጁት የማጠቃለያ ፈተናዎች ከፈተና የይዘት ተገቢነት አንጻር ምን ይመስላሉ?

## 1.4 የጥናቱዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በጉራጌ ዞን እነ ወረዳ በየዋሽንዬ አጠ/2ኛ/ደ/ት/ቤት የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ማጠቃልያ ፈተናዎችን የይዘት ተገቢነትን መፈተሽ ሲሆን የሚከተሉት ዝርዝር አለማዎች ይኖሩታል

1. የተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ከመርሃ ትምህርቱና ከመማሪያ መፅሀፍቱ ጋር ምን አይነት ግንኙነት እንዳላቸው  መፈተሽ፡፡
2. ከ2013-2014ዓ.ም በቀረቡት ጥያቄዎች ለየትኛው ይዘት የበለጠ ትኩረት የሰጡ እንደሆነ መፈተሽ፡፡
3. የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ማጠቃለያ ፈተናዎችን ከፈተና የይዘት ተገቢነት መርሆዎች አንፃር መፈተሽ፡፡
4. የተዘጋጀውት የማጠቃለያ ፈተናዎች ከፈተና የይዘት ተገቢነት አንጻር ምን እንደሚመስሉ መፈተሽ፡፡

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

የዚህ ጥናት አስፈላጊነትም ከተለያዩ ሁነቶች ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ይህ ጥናት ከማጠቃለያ ምዘናዎች፣አግባብነት፣ቋንቋ ፈተና የይዘት ተገቢነት፣ከትምህርት ይዘት ተገቢነት እና ትክክለኛነት ዙሪያ የሚያጠነጥን ሲሆን ፋይዳው ከተለያዩ እሳቤዎች አንፃር ይታያል፡፡ Harrrison (1983) እንደገለፁት የቋንቋ ትምህርት እና የቋንቋ ፈተና የማይነጣጠሉ፣በመማር

ማስተማር ሂደት ከፍተኛ ቁርኝት ያላቸው ሲሆን የቋንቋ ፈተናን ለመገምገም ስንነሳ ከትምህርቱ ይዘት፣ ከመማሪያ መፅሀፉ፣ ከአውዳዊነቱ፣ ካግባብነቱ መሆን እንዳለበት ያስረዳል።

በመሆኑም ጥናቱ ሲጠናቀቅ የሚከተሉት ፋይዳዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል።

የመጀመሪያው ስነ-ትምህርታዊ ፋይዳ ሲሆን በቋንቋ ትምህርትና በትምህርት ይዘቶች መካከል ያለውን ትስስሮሽ ያሳያል።ምዘናዎች ሲዘጋጁ ምን ምን ይዘቶችን ማካተት እንዳለባቸው፣በምን መልክና አግባብ መቅረብ እንዳለባቸው ይጠቁማል። መምህራን የቋንቋን ምዘና ሲያዘጋጁ ቀድመው ትኩረት ማድረግ ያለባቸውን ሁኔታ ያሳውቃል። የቀረቡት የማጠቃለያ ምዘናዎች በመፅሀፉ ውስጥ ያሉትን ይዘቶች ወካይ መሆናቸውን ለማወቅ ያግዛል፡ ፡ እንዲሁም ጥያቄዎችን ስናዘጋጅ ከመማሪያ መፅሁፉና ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ያላቸውን ዝምድና መሰረት አድርጎ መውጣት እንዳለበት ከማሳየቱም በላይ መፅሀፉን፣መርሀትምህርትቱና ምዘናዎችን በመገምገም ለቀጣይ በፈተና አወጣጥ ላይ መሰረታዊ ግንዛቤን ይሰጣል ተብሎ ይገመታል።

በሁለተኛ ደረጃ የሚነሳው የማጠቃለያ ምዘና አዘገጃጀት በተመለከተ የተለያዩ ንድፍ ሃሳባዊ እይታዎች ያንፀባርቃሉ። Weir (2005) እንደገለፁት የቋንቋ ትምህርት ፈተናዎች ሲዘጋጁ ህግጋትን፣ መዋቅርንና ስርአትን በቀጥታ በማቅረብ የተማሪዎችን የቋንቋ ስርአት እውቀትና ክህሎትን ማጎልበት አለበት የሚል እሳቤ አላቸው። ማህበራዊያን ደግሞ የቋንቋ ትምህርት ጥያቄዎች ሲዘጋጁ እውናዊ፣ ማህበራዊ፣ ስነ ልቦናዊና፣ ስነ-ትምህርታዊ፣ በሆኑ ጉዳዮች ላይ አውዳዊይነትን ጠብቆ መቅረብ አለበት የሚል አስተሳሰቦች ይሰነዝራሉ። ስለሆነም ይህ አሁን ያለውን የምዘና አዘገጃጀት አውዳዊና ስነ-ትምህርታዊ ነው ማለት ይቻላል (Harrrison (1983):: ስለሆነም አንድ ምዘና ሲዘጋጅ እንዴትና ምን መምስል እንዳለበት ያሳያል። በጉራጌ ዞን በእዣ ወረዳ በየዋኽንየ/አጠ/2ኛ/ደ/ት/ቤት ለዘጠነኛ በክፍል ደረጃ የሚዘጋጁት የማጠቃለያ የአማርኛ ቋንቋ ምዘናዎች ትኩረታቸው በየትኛው ንድፈ ሃሳብ ላይ እንዳነጣጠረ ግንዛቤ ይሰጣል። ምዘናዎች ሲዘጋጁ በተለይም ደግሞ የማጠቃለያ ፈተና ይዘት በፈተና ለማካተት ሲታሰብ የፈተና ይዘት ንድፍ ሃሳባዊ መርሆዎችን ተከትሎ መዘጋጀቱንና አለመዘጋጀቱን በተመለከተ መረጃ ይሰጣል።

ሶስተኛው ፋይዳ ደግሞ ከምርምራዊ ፋይዳው አንፃር የሚታይ ሲሆን በተመሳሳይ ሁኔታ የማጠቃለያ ፈተናው አቀራረብ ፣አመራረጥ፣ አግባብነት፣ ትክክለኛነትና ተገቢነት ዙሪያ ልዩ ልዩ እውቀትና መረጃዎችን ይሰጣል፡፡ በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ በተመሳሳይ ጥናት ለሚያካሂዱ መምህራንና ባለሙያዎች የተወሰነ ፍንጭ ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል መምህራንና ሌሎች የቋንቋ ባለሙያዎች የቋንቋ ፈተናዎች በሚያዘጋጁበት ጊዜ ማካተት ያለባቸውን እና የሌለባቸውን ምን አይነት መርሆዎችን መከተል እንዳለባቸው አቅጣጫ ያሳያል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ጥናቱ ትኩረት ያደረገው በጉራጌ ዞን እዣ ወረዳ በየዋኽንየ/አጠ/2/ደ/ት/ቤት በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ማጠቃለያ ፈተና የይዘት ተገቢነት በመፈተሽ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ጥናቱ ለክፍል ደረጃው ከተዘጋጁት የቋንቋ ፈተና፣መርሀ ትምህርትና መማሪያ መፅሀፍ አኳያ መፈተሽ ነው ፡፡ጥናቱ ከተጠቀሰው የክፍል ደረጃ ውጪ ያሉ ፈተናዎችን አያካትትም፡፡ ጥናቱ በተጠቀሰው ትምህርት ቤት ውስጥ የቀረቡትን የአማርኛ ቋንቋ ማጠቃለያ ፈተና የይዘት ተገቢነቱን መርምሮ ውጤቱን ያቀርባል፡፡

## 1.7. የጥናቱ ውስንነት

የዚህን ጥናት ተገቢነት ለማጎልበት በአጥኚው በኩል የተለያዩ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ በጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የሚያተኩሩ መሰረታዊ ጥቄዎች ተነድፈው፣ እርሰ ጉዳዩን ሊያሳኩ የሚችሉ አላማዎች ተቀርፀው፣የጥናቱን ችግር የሚያመላክቱ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ተለይተው፣ ለጥናቱ አስፈላጊው ስነ-ዘዴና ንድፍ ተመርጦ መረጃወዎቹ ተሰብስበዋል ፡፡ የተሰበሰቡትን መረጃዎች ከመሰረታዊ ጥያቄዎች አንፃር በመተንተን የተገኘውን የጥናት ውጤት ከጥናቱ አላማ አንፃር ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ የተገኘውን ውጤት መሰረት በማድረግ ለጥናቱ ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና የመፍትሄ ሀሳቦችን ለማቅረብ ተችሏል፡፡

ይሁንና ከላይ የተጠቀሱት ተግባራት ቢከናወኑም ጥናቱ ከተለያየ ችግሮች ሙሉ በሙሉ የፀዳ ነው ማለት አይደለም፡፡ በጥናቱም ያጋጠሙ ችግሮች የሚከተሉት ናቸው፡፡

የመጀመሪያው የጥናቱን ተገቢነት የበለጠ ለማጎልበት የተዘጋጁት ጥያቄዎች ከሁሉም የቋንቋ የፈተና መርሆዎች አንፃር ማየት አልተቻለም፡፡ ይኸውም የፈተናዎቹን አስተማማኝነት ለማረጋገጥ የፈተናዎቹ ምላሽ ስላልተገኙ እስተማማኝነታቸው በዚህ ጥናት ማረጋገጥ

አልተቻለም፡፡ ሁለተኛው የፈተናዎቹን የቅለት ክብደት መጠን ለማወቅ የፈተናዎቹ ምለሻ ስለሌለ በሙከራ ከማረጋገጥ ይልቅ በፅንስ ሀሳብ ደረጃ ብቻ መፈተሸቸው ሲሆን ሌላው ደግሞ አጥኝው በሚኖርበት አካባቢ የመብራትና የኔት ወርክ ችግር በመኖሩ ስራውን በቅልጥፋና ለመስራት እንደ አንድ ችግረ ነበር፡፡

አራተኛው ችግር አጥኝው የሚሰራበት አካባቢ ጥናቱን በአግባቡ ለመከወን የቤተ መፅሃፍትና መሰል ጥናቱን ለማጎልት የሚያስችል የሚነበቡ ነገሮች አለመኖር ሌላው ተጠቃሽ ችግር ነበር፡፡ይሁንና አጥኝው ይህን ሁሉ ችግር በመቋቋም መፍትሄ በመስጠት ጥናቱን ከግብ ማድረስ ችሏል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# የክለሳ ድርሳናት

## 2.1 የቋንቋ ፈተና ንድፈ ሐሳብ

ፈተና በቋንቋ ትምህርት ታሪክ ከረጅም ዘመናት ጀምሮ የመማር ማስተማሩ አካል ነው፡፡ ፈተና የተማሪዎችን ማንነት ለመለየት ሲሰራበት የነበረና አሁንም እየተሰራበት ያለ፣ የአንድን ተማሪ የቋንቋ እውቀትና ችሎታ፣ ድክመትና ጥንካሬ፣ ፍላጎትና የእለት ተዕለት መሻሻል ወዘተ በመለካት ውሳኔዎችን ለማሳለፍና ቀጣይ ተግበራትን ለማከናወን የሚያስችሉ መረጃዎችን የሚሰጥ መሳሪያ ነው (Ur፣ 1996) ናHughes፣ (1989) Brown፣ (1980፣251) በበኩላቸው "ፈተና ከዕለት ተዕለት የመማር ማስተማር ተግባር ጋር የተያያዘ አላማ ያለውና ተፈላጊውን የተማሪ ችሎታና እውቀት ለመለካት የሚያስችል ዘዴ ነው" በማለት ገልጸውታል፡፡በሌላ መልኩ ፈተና ለአንድ ትምህርት ፕሮግራም የተቀመጠ ዓላማ በተማሪዎች ዘንድ ምን ያህል ተፈፃሚ እንደሆነ ወይም ግብ መምታት አለመምታቱን ለማረጋገጥ ከሚያስችሉ መሳሪያዎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ Bachman (1995፣54) "ፈተና በመማር ማስተማር ላይ ውሳኔዎችን ለማሳለፍ የሚያስችለን ጠቃሚ መረጃዎች የሚሰጥ መሳሪያ ነው፡"ሲሉ ገልፀውታል፡፡ይህ የሚያመለክተው ፈተና ስለማስተማር ስልቱ፣ ስለትምህርት አቀራረብ፣ ስለትምህርት ይዘት፣ ተማሪዎች ስላሉበት የዕውቀትና ችሎታ ደረጃ የሚገኝበትና ውሳኔ የሚሰጥበት መሆኑን ነው፡፡

የቋንቋ ፈተናን አስመልክቶ Brown (2004፣ 3) እንደገለፁት "ፈተና የቋንቋ ክሂሎችንና ዕውቀትን ለመለካት የሚያስችል ዘዴ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡" ከዚህ ሃሳብ መገንዘብ እንደሚቻለው የቋንቋ ፈተና ተማሪዎችን እንዲማሯቸው የተነደፉ አጠቃላይና ዝርዝር የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎችን መሰረት በማድረግ የሚለማምዷቸውና የሚመሯቸው የቋንቋ ክሂሎችንና ዕውቀቶች ምን ያህል እንዳዳበሩና እንዳወቁ ለመለካት የሚያስችል የመመዘኛ መሳሪያ ነው፡፡ በመሆኑም በቋንቋ ትምህርት የተፈለገው የባህሪ ለውጥ መምጣት አለመምጣቱን ለመለየት በየደረጃው ፈተናዎች ተሰጥተዋል፡፡ በየደረጃው የሚሰጡት የቋንቋ ፈተናዎችም በተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት ላይ መረጃዎችን በመስጠት ልዩ ልዩ ውሳኔዎችን ለማሳለፍ ችለዋል፡፡ በቋንቋ ትምህርት ሂደት አይቀሬው አካል ፈተና ነው፡፡

ምክንያቱም ተማሪዎችም ሆኑ መምህራን በውጤት መበረታታትን ስለሚፈልጉና ስለሚሰጠው ትምህርት ሂደት ፈተናዎች የመረጃ ምንጭ ስለሆኑ ደጋፊዎች ናቸው Barker,(1989 : 27)::

ከቋንቋ ፈተና ትምህርት በኋላ ብቻ የሚሰጥ አይደለም፡፡ይህንን አመልክቶ አብረሃም (2003፣ ዓ.ም፣18) Mehrens & Lehman (1974፣3)ን በመጥቀስ ሲገልፁ የቋንቋ ፈተና ተማሪዎች የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብ፣ የመፃፍ ክሂሎችን እንደ የስነ ልሳን ዕውቀቶችና ከመማራቸው በፊት ያላቸውን የቀደመ ዕውቀትን ለመገምገም ወይም ከተማሩ በኋላ የቋንቋ ችሎታቸውን ለመለካትና ምን ያህል ለውጥ እንዳመጡ ለመረዳት የሚያገለግል የመመዘኛ መሳሪያ ነው፡፡

ይህ የሚያመለክተው የቋንቋ ፈተና ቅድመ ትምህርትና ድህረ ትምህርት መመዘኛነት ሊሰጥ መቻሉ ነው፡፡እነዚህ ቅድመና ድህረ ትምህርት የሚሰጡ ፈተናዎች የተለያየ ዓላማም አላቸው፡፡ የዚህ ትምህርት ትኩረት ግን ከትምህርት በኋላ የሚሰጥ የቋንቋ ፈተና አይነት ላይ ነው፡፡

## 2.2. የቋንቋ ፈተና ዓይነቶች

የቋንቋ ፈተናዎች ከሚሰጡት መረጃና ከሚዘጋጁበት ዓላማ የተነሳ የተለያዩ ናቸው፡፡ የተለያዩ ምሁራን የቋንቋ ፈተና ዓይነቶችን በተለያዩ መልኮችና አይነቶች ቢገልጹም በአራት ይከፍሏቸዋል፡፡ ለአብነት ብንመለከት Henning (1987) የብቃት መለኪያ (proficiency Test)፣ የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና (Aptitiude Test)፣ የችሎታ መለኪያ ፈተና (Achievement test) በማለት በሶስት ሲመድባቸው ፤ Alderson (1995) የምደባ ፈተና (Placement Test)፣ የእድገት መለኪያ ፈተና (Progress Test)፣ የብቃት መለኪያ ፈተና(proficiency Test)፣ የጥንካሬና ድክመት መለኪያ ፈተና (Diagnostic Test)፣ የችሎታ መለኪያ ፈተና (Achievement Test)ና የደረጃ መለኪያ ፈተና በማለት በስድስት እንደሚከፈሉ ገልፀዋል፡፡ (Brown2004) የቋንቋ ብቃት መለኪያ ፈተና (Language proficiency Test )፣ የምደባ ፈተና (Plecement Test)፣ የቋንቋ ቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና (language Aptitude Test)፣ የጥንካሬና ድክመት መለኪያ ፈተና (Diagnostic Test)ና የችሎታ መለኪያ ፈተና(Achievement Test ) በማለት በአምስት መድበዋቸዋል፡፡ Hughes፣(1989፣45)፣እና Brown(1980፣257)የቋንቋ ፈተና አይነቶችን የብቃት መለኪያ

ፈተና (Proficiency test)፣ የድክመትና ጥንካሬ መለኪያ ፈተና (Diagnosis test)፣ የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና (Placement test) እና የችሎታ መለኪያ ፈተና (Achievement test)" በማለት በአራት ይከፍሏቸዋል፡፡

2.2. 1 የችሎታ መለኪያ ፈተና (Achievement test)

የችሎታ መለኪያ ፈተና (Achievement test) መርሀ ትምህርቱና መማሪያ መፅሃፉን መሰረት በማድረግ ተማሪዎች የተማሩትን ይዘት ምን ያህል እንደተረዱ የሚፈተሽበት ሲሆን ክልላዊ፣ ብሔራዊና የክፍል ማጠቃለያ ፈተናችዎችን የሚመለከት የፈተና አይነት ነው (Heaton, 1980; Alderson et al, 1995)፡፡ የችሎታ መለኪያ ፈተና (Achievement test) ተማሪዎች ባሉበት የክፍል ደረጃ የሚመዘኑበት ሲሆን በተማሯቸው ይዘቶች ላይ ይመሰረታሉ፡፡ በዚህ የፈተና አይነት ጊዜ በክፍል ውስጥ የቀረቡ ይዘቶች እንደ የክፍለ ጊዜያቸው መጠን በመወሰንኑ ሁሉም ይዘቶች ሊወክሉ የሚችሉ የጥያቄ ናሙናዎች የሚካተቱበት በጥንቃቄ ሊዘጋጅ የሚገባቸው የፈተና አይነቶች ናቸው (Brown, 2004;47) ፡፡

የችሎታ መለኪያ ፈተና ተማሪዎች ወደሚቀጥለው ደረጃ ለማዘዋውር ወይም ባሉበት እንዲደግሙ እንደመሳሪያ ከማገልገሉም በላይ ተማሪዎችን በብቃታቸው ለመሸለም ወይም ከደረጃ ከፍ ለማድረግ ይረዳል፡፡ በመሆኑም ብዙ ትኩረት የሚያደርገው የክፍል ውስጥ ማጠቃለያ ፈተናዎችና ሀገር አቀፍ ፈተናዎች ላይ ነው፡፡ ይህ የፈተና አይነት በፈተና ውጤቶች የማስተማሪያ ዘዴውን፣ የትምህርቱን ይዘቶችና የሚያስተምሩትን መምህራን ወዘተ. ለመገምገም እንደመነሻ ሆኖ ያገለግላል፡፡ እንዲሁም በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ለሚመስረት አጥኚ ሰፋ ያለ መረጃ ሊያገኙበት የሚችል የቋንቋ ፈተና አይነት ነው (Harmer, 2001;322)፡፡

ይህ ፈተና ተማሪዎችን የትምህርት አቅም፣ ችሎታ በእቅድ ከተቀመጠው የትምህርት ይዘት ጋር በማመጣጠን የተማሪዎችን እውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ደረጃ በመወሰን ወደ ሚቀጥለው የትምህርት ክፍል ደረጃ የሚያልፉትና የማያልፉትን ለመለየት ይረዳል Henning,(1987)፡፡በመንግስት ሥርአት ትምህርት ተቀረጸና የተሰጠው ትምህርት ተማሪዎች ምን ያህል እንደጨበጡትና እንዳልጨበጡት ለመለየት የክፍል ደረጃ ለመወስን በመንግስት ታቅዶ የሚሰጥና የተማሪዎችን እውቀት፣ ክህሎት ደረጃ የሚለካ ፈተና የትምህርት ፈተና እንለዋለን (McnNarma, 1999) ::

ከምሁራን ንደፌ ሃሳባዊ ገለፃ መረዳት እንደሚቻለው የችሎታ መለኪያ ፈተና (Achievement test) ተማሪዎች በተማሯቸው የትምህርት ይዘቶች ላይ ተመስርቶ የሚሰጥ መሆኑን ብዙውን ጊዜ በትምህርቱ መጨረሻ ወይም ማጠቃለያ ፈተና ላይ የሚተገብር መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም በመርሀ ትምህርቱና በመማሪያ መፅሃፉ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

### *2.2.2 የይዘት ተገቢነት (content validity)*

"አንድ ፈተና ሊይዝ የሚገባውን የቋንቋ ትምህርት ይዘት ከየአይነቱ እንደየትኩረት ደረጃው በተመጣጠነ መልኩ በናሙናነት አካቶ የያዘ ማለት ነው፡፡" የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ዋና ትኩረት በይዘት ተገቢነት ላይ መሆን አለበት፡፡ ፈተናው ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ የተማሯቸውን ይዘቶች በናሙናነት አመጣጥኖ ከሆነ የይዘት ተገቢነት ይኖረዋል Hughes (2003፣ 26) ፡፡ ይዘታዊ ተገቢነት ማለት አንድ ፈተና በአንድ ትምህርት አይነት ውስጥ ለተካተቱ ይዘቶች ወካይ ናሙና ሆኖ የመዘጋጀት ብቃቱ ምን ያህል ነው? የሚለውን መሰራታዊ ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችል ጥሩ የቋንቋ ፈተና ባህሪ መለኪያ ነው፡፡ በመሆኑም በይዘታዊ ተገቢነት ውስጥ እንደ ቁልፍ ጥያቄ ሆኖ የሚነሳው የሚዘጋጀው ፈተና ትምህርቱን ዋና ዋና ይዘቶች በናሙናነት የማካተት ብቃቱ ነው፡፡ አንድ ፈተና ከመዘጋጀቱ በፊት ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነገር በትምህርት ክፍል ጊዜ ውስጥ ይዘቶች እንደቀረቡበት ሽፋን ብዛታና ማነስ ጋር ያለውን እውነታ ነው፡፡ አንድ ይዘት ክፍል ውስጥ ለመስተማር አምስት ክፍለ ጊዜ የሚፈጅ ከሆነ የአምስት ክፍለ ጊዜውን ያህል በፈተና ጥያቄው ላይ ማካተት አስፈላጊ ይሆናል(Gronlund 1982፣126)፡፡

በመርሀ ትምህርቱና በመማሪያ መፅሃፉ የቀረቡት ይዘቶች ከተሰጣቸው ትኩረት አንፃር በፈተናው ጥያቄዎች ውስጥ ሽፋን ሊያገኙ ይገባል፡፡ ይህም ፈተናው የሚያካትታቸው ጥያቄዎች በመርሀ ትምህርቱ ቀድመው የሰፈሩ የትምህርት ዓላማዎችን ተገቢ በሆነ መንገድ የሚወክሉና ለዓላማው ማስፈጸሚያ በቋንቋ መማሪያ መፅሃፉ ውስጥ ተካተው የቀረቡትን ይዘቶች የሚወክሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የተማሪዎቹን የቋንቋ ችሎታ በትክክል መለካት የሚችሉ መሆን ይኖርባዋል፡፡ ስለዚህ የቋንቋ ፈተናውን የይዘት ተገቢነት ለመጠበቅ መርሀ ትምህርቱንና መማሪያ መፅሃፉን መነሻ ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

አንድ ፈተና የይዘት ተገቢነቱን የጠበቀ እንዲሆን "በዝግጅቱ ውቅት የፈተና ንድፍ ማዘጋጀት አስፈላጊ መሆኑን Hughes (2003፣ 27) ና Fulcer (2010፣ 127) ይገልፃሉ፡፡ ይህን ማድረጉ ደግሞ" ይዘቶች በፈተናው ሳይካተቱ እንዳይቀሩ ለመረዳቱም በላይ ፈተናው ጠቃሚ በሆኑና የበለጠ ትኩረት በተሰጣቸው የትምህርት ይዘቶች ላይ እንዲያተኩሩ ያደርጋል" ይላሉ፡፡

ይህ የሚያመለክተው የፈተና ንድፍ በቅድመ ጥያቄ ዝግጅት የሚከናወን ተግባር በመሆኑ ተማሪዎች በተለያየ ጊዜ የተማሩዋቸው ይዘቶች ትኩረት አግኝተው በፈተናው እንዲካተቱ ማገዙን ያመለክታል፡፡ መምህራን ፈተና በሚያዘጋጁበት ጊዜ ሁሉ የፈተና ንድፍ የማዘጋጀት ልምድ ቢኖራቸውም የይዘት ተገቢነቱን የጠበቀ ፈተና ማዘጋጀት እንሚችሉ ይጠቁማል፡፡

የፈተና ንድፍ ፈተናው ከመዘጋጀቱ በፊት በውስጡ መካተት ያለባውን ይዘቶች ምን ያህል ጥያቄዎችን ከየይዘቱ በአይነት ተመርጠው መካተት እንዳለባቸው ለመወሰን ያገለግላል፡፡ እንደ Heaton (1990፣13) ፣ Alderson. et.al (1995፣ 9) ና Bachman and Palmer (1996፣ 177) ሃሳብ የይዘት ተገቢነቱን የጠበቀ እንዲሆን ይዘት መውሰኛ ሰንጠረዥ በማዘጋጀት ይዘቶችን ተገቢ ይሆናል፡፡ ይህም የሚያስገነዝበን የይዘት ተገቢነቱን የጠበቀወ ፈተና አዘጋጅቶ ተማሪዎችን በመፈተን ለመለካት የተፈለገውን ችሎታና እውቀት ለመለካት ያስችላል፡፡ ከፈተናው ውጤት የሚገኘውም መረጃ ጠቃሚ ውሳኔዎችን ለመለስጠት ያስችላል፡፡

## 2.3 የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት

ከዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ተዛማጅነት ያላቸው ልዩ ልዩ ጥናታዊ ፅሁፎች ይገኛሉ፡፡ ይህ ጥናት ከነዚህ ጥናቶች ያለውን ልነትና አንድነት እንደሚከተለው መመልከት ይቻላል፡፡ ገነት አታቱ (2011 ዓ.ም) (2005 እስከ 2010 ዓ.ም) በአስረኛ ክፍል በተዘጋጁ ብሔራዊ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱ የስነ ፅሁፍ ጥያቄዎች የይዘት ተገቢነትና አቀራረብ ግምገማ በሚል ርዕስ የሁለተኛ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረቡት ጥናታዊ ፅሁፍ ሲሆኑ አላማውም ከ2005 እስከ 2010 ዓ.ም ሀገር አቀፍ ፈተናዎች ድርጅት ለአስረኛ ክፍል መልቀቂያ በተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱ የስነ ፅሁፍ ጥያቄዎች የይዘት ተገቢነትና አቀራረብ መገምገም ነው፡፡

በሌላ በኩል ወንድሙ ነጋ (2011 ዓ.ም) በ2008ና በ2009 ዓ.ም የትምህርት ዘመን የተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ የማጠቃለያ ፈተናዎች የይዘት ተገቢነትና አስተማማኝነት በሰባተኛ ክፍል ፈተናዎች መነሻነት በሚል ርዕስ በሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት በከፊል የቀረበ ጥናት ሲሆን፣የጥናቱ ዓላማ በ2008ና በ2009 ዓ.ም በቦረዳ ሙሉ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች የተሰጡ የአማርኛ ቋንቋ ማጠቃለያ ፈተናዎች የይዘት ተገቢነት መፈተሽ ነው፡፡ የጥናቱ ውጤት በመርሀ ትምህርትና በመማሪያ መፀሃፍ የተካተቱ ይዘቶች ሙሉ በሙሉ በተተኳሪ ፈተናዎች ውስጥ በተመጣጣኝ ደረጃ አልተካተቱም፡፡

ቁምላቸው ጤናው (2010 ዓ.ም) ከ2007 እስከ 2009 ዓ.ም በዲላ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ሰልጣኞች የተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ የሰዋሰው ጥያቄዎች የይዘትና አዘገጃጀት ተገቢነት ፍተሻ በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ ሲሆን አላማውም ከ2007 እስከ 2009 ዓ.ም ለዲላ መምህራን ኮሌጅ ሰልጣኞች የተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ  ፈተና ጥያቄዎች ከፈተና አዘገጃጀትና የይዘት ተገቢነት አኳያ መፈተሽ ነው፡፡የጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተው የፈተናዎች የይዘት ተገቢነት በሚፈተሽበት ጊዜ የመርሀ ትምህርቱና መማሪያ መፅሃፉ ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች ነገር ግን በሶስቱም ፈተና ጥያቄዎች ላይ ያልተካተቱ ይዘቶች፣ እኩል የክፍል ውስጥ ይዘት ሽፋን በፈተናዎች ላይ የተለያዩ መጠን ተሰጥቷቸው መገኘታቸው ለይዘት ተገቢነት መቀነስ አንዱ መንስኤ እንደሆነ አመልክቷል፡፡

ትንሳኤ ብርሃኔ (1988 ዓ.ም) “የአማርኛ የቃላት አፈታተን በሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና መነሻነት (1980 - 1987 ዓ.ም)” በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበው ሌላ የተጠቀሰ ስራ ነው፡፡ ትንሳኤ በእነዚህ ስምንት ዓመታት የተሰጡ ብሔራዊ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎችን ተገቢ ወይም ጥሩ የመመዘኛ መሳሪያ መሆን አለመሆናቸውን መርምረዋል፡፡ በዋናነት ትክክለኛነትና አስተማማኝነት እንደ መመዘኛ በመውሰድ ያዩ ሲሆን በውጤቱም ከትክክለኛነት አንፃር አብዛኛዎቹ የቃላት ፈተናዎች መማሪያ መፅሐፍቱን መሠረት ያደረጉ አለመሆናቸውንና የአስተማማኝነት ደረጃቸውም ዝቅተኛ እንደሆነ  በዚህም ከ269 ጥያቄዎች 55 የሚሆኑት አንድ ትክክለኛ መልስ እንደሌላቸው አመላክተዋል፡፡ ከዚህ ሌላ አማርኛ የአፍ መፍቻቸው የሆኑ ተማሪዎች ካልሆኑት ይልቅ በውጤት እንደተሻሉ

አሳይተዋል፡፡አበበች ገብሩ (2004) ዓ.ም ከ1998-2003 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረቡ የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ የሰዋስው ጥያቄዎች ግምገማ በሚል ጥናት የተደረገ ሲሆን የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው ከቋንቋ የትምህርት ይዘት ተገቢነት አንፃር ሲታይ የፈተናው አዘገጃጀት የተወሰኑ አወንታዊ ጎኖች ቢኖሩትም የጥያቄዎቹ የመደገም ባህሪ፣ የወካይነት ችግር ያለባቸውና የተገቢነት ችግሮች እንዳሉባቸው ያሳያል፡፡የበለጠ ያዕቆብ (1995 ዓ.ም) ስራ "ለ9ኛ ክፍል የሚዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ለደረጃው ከሚቀርበው ትምህርት ጋር ያላቸውን የይዘት አግባብነትና የአጠያየቅ ብቃት" በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የተካሄደ ጥናት ሲሆን፣ የጥናቱ ውጤትም እንደሚያመለክተው ፈተናዎቹ ለደረጃው ከተዘጋጀው መርሃ ትምህርት ጋር ያላቸውን የይዘት አግባብነት ዝቅተኛ መሆኑን እና ከመማሪያ መፅሐፍ ይዘት አኳያ ሲታኙ ዝምድና እንደሌላቸው አመላክተዋል፡፡

ተስፋዬ መኮንን (2000 ዓ.ም) "የሶስት ዓመት ፈተናዎችን በመውሰድ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ከመርሃ ትምህርቱ ጋር ያላቸውን የይዘት ዝምድና" በሚል ርዕስ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ያጠኑ ሲሆን፣ የጥናቱ ውጤት እንደሚገልፀውም በሶስቱም አመታት ፈተናዎች ውስጥ የማዳመጥና የመናገር ክሂሎች አለመካተታቸው ተገቢነት እንደሌለው በተጨማሪም የመፃፍ ክሂል የፈተና ይዘቶች ከመርሃ ትምህርቱ ጋር የማይዛመዱ መሆናቸው፣ ከፈተናዎቹ ይዘቶች ውስጥ ከመርሃ ትምህርቱ ዝርዝር ዓላማዎችና ይዘቶች ጋር የማይዛመዱ እንዳሉ አመላክተዋል፡፡ታለ ጌታ (2005ዓ.ም) በሀገር መከላከያ ሰራዊት ከ2001-2004 ዓ.ም ለርቀት ትምህርት መርሀ ግብር የቀረቡ የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ብሄራዊ ፈተናዎች ከመማሪያ መፅሀፍቱ ጋር ያላቸው ዝምድና በሚል ርዕስ ጥናት አካሂዶ የተገነው ውጤት የሚያሳየው ጥያቄዎች በሚዘጋጁበት ጊዜ በእያንዳንዱ የቋንቋ ክሂል እና የእውቀት ዘርፎች ላይ የሚገኙ የትምህርት ይዘቶችን የሚወክሉ አይደሉም፡፡ ጥያቄዎቹ በብዛት የተካተቱት የቃል ክፍሎች እና የስነ ልሳን ዘርፎች ናቸው፡፡ ስለሆነም ለሌሎች የትምህርት ይዘቶች ትኩረት ያልሰጠ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ኤደን ብርሃኔ (2002 ዓ.ም) "ከ1995 - 2001 ዓ.ም በቀረቡ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች የቃላት አፈታተን ግምገማ በደብረ ማርቆስ ከተማ የሚገኙ ሁለት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት" በሚል ርዕስ የተጠና፣ ሲሆን የጥናቱ ዓላማ የዘጠነኛ

ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎችን የቃላት አፈታተን መመርመር ነው፡፡ በጥናቱም የተገኘው ውጤት በቃላት ጥያቄዎች ውስጥ በአገልግሎት ላይ የዋሉት የፈተና ማቅረቢያ መንገዶች የተለያዩ መሆናቸውንና የአማርኛ ቋንቋ የቃላት ፈተናዎች የተማሪዎችን የቃላት ችሎታ በተገቢው ሁኔታ የመመዘን ብቃት እንደሚጎድላቸው ታይቷል፡፡

በአጠቃላይ ይህ ጥናት በአማርኛ ቋንቋ ፈተና ላይ ማተኮሩ ከላይ ከተጠቀሱት ተዛማጅ ቀደምት ጥናቶች ጋር የሚለዩበትና የሚመሳሰሉበትን ሆኔታዎች ቀርበዋል፡፡ ጥናቱም በአማርኛ ቋንቋ ፈተና ላይ በተጠቀሱት ተዛማጅ ቀደምት ጥናቶች ጋር ሲያመሳስለው፣ ወንድሙ (2011 ዓ.ም)ና ትንሳኤ (1989ዓ.ም) በተገቢነትና እሰተማማኝነት ላይ መመስረታቸው ፣ሌላው በይዘት አቀራረብ ላይ ገነት (2001ዓ.ም)፣ ቁምላቸው( 2010ዓ.ም) ፣ አገኘሁ( 2006ዓ.ም)፣ በለጠ (1995ዓ.ም)፣ ተስፋዬ (2005ዓ.ም)እና ኤደን (2002ዓ.) ከጥናቱው ጋር ልዩ ያደርጋቸዋል፡፡በተጨማሪም እነዚህ ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር በጊዜና በቦታ ይለያያሉ፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

# የአጠናን ዘዴ

## 3.1 የጥናቱ አይነት

የዚህ ጥናት ዓላማ በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ማጠቃለያ ፈተና የይዘት ተገቢነት መፈተሽ ነው፡፡ ይህንን ጥናት ከግቡ ለማድረስ የተመረጠው አይነታዊ እና መጠናዊ የምርምር (Qualitative research and Quanititatve research) ዘዴ ሲሆን በአቀራረቡ ደግሞ ገምጋሚ የምርምር ንድፍን ተከትሎ ቀርቧል። ይህ የምርምር አይነት የተመረጠበት መሰረታዊ ምክንያት የጥናቱ እርዕስ፣የጥናቱ ባህሪ፣ መሪ ጥያቄዎቹና አላማው እንደሚያሳዩትና የሚሰበሰቡት የመረጃዎች ውጤቶች የመጠናዊነት ባህሪ ያላቸው እና መረጃዎቹ በአጠቃላይ የአይነታዊ ባህሪ ያላቸው በመሆኑ ነው። በሌላ አገላለፅ ለጥናቱ በመረጃ ምንጭነት የሚወሰዱትና የሚገኙት መረጃዎች ባህሪያቸው እስታስቲካዊ የሆኑ፣በመጠንና በቁጥር የሚይገለፁ እና በአይነታዊ፣ በገለፃና በትረካ መልክ የሚቀርቡ በመሆኑ ነው።ስለሁነም የተሰበሰቡት መረጃዎች በአይነት በአይነት በየፈርጃቸው በመመደብ ትረካዊ በሆነ መልኩ ተብራርተው ቀርበዋል፡ይህን ጥናት

ከግብ ለማድረስ በጥናቱ ውስጥ ተግባራዊ የተደረጉት አይነታዊ (Qualitative) እና መጠናዊ (Quantitative) የአጠናን ዘዴዎች ይሆናል፡፡ ስለዚህ በቁጥር ከሚተነተነው ውጭ ያሉ መረጃዎች ዓይነታዊ የምርመር ዘዴን ሲከተሉ በቁጥር የቀረቡት ደግሞ በመጠናዊ የተገለጹ ናቸው፡፡

## 3.2. የጥናቱ ንድፍ

ይህ ምርምር በአቀራረቡም ገምጋሚ (evaluation design) የምርምር ንድፍን መሰረት ያደርጋል፡፡ ይህ የምርምር ንድፍ ለዚህ ጥናት የሚመረጥበት ዋና ምክንያት ከ2013-2014 ዓ.ም ለዘጠነኛ የክፍል ደረጃ በት/ቤት ደረጃ እየተዘጋጀ የሚቀርቡት የአማርኛ ቋንቋ ጥያቄዎች ፈተናዎች የይዘት ተገቢነት አንፃር መገምገም በመሆኑ የጥናቱን ውጤት ለማስረዳትና ለማብራራት ከሌሎቹ የጥናት ንድፎች አኳያ በተሻለ መልኩ አመች ይሆናል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡፡ ይህ ማለት በት/ቤት ደረጃ እየተከናወነ ያለው የቋንቋ ምዘና ሂደት በሳይንስ ደረጃ ከተቀመጠው ፕሮግራም አንፃር ያለበትን ደረጃ መገምገም፣ መመርመር እና በፈተናው የይዘት ተገቢነት ላይ ያሉ ጠንካራና ደካማ ጎኖች በመለየት የሚያተኩር በመሆኑ ነው፡፡

## 3.3 የመረጃ መሰብሰብያ መሳሪያዎች

አንድን ጥናት በተያዘለት የጊዜ ገደብ በትክክልና በስርአት ለማጥናት በመጀመሪያ ትክክለኛና አስተማማኝ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን መምረጥና ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ ለዚህ ጥናት አስፈላጊና ጠቃሚ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ በመሆን በአብይነትና በቀዳሚነት የተወሰደው የሰነድ ፍተሻ ነው፡፡ ስለሆነም በሰነድ ፍተሻ የተገኘው መረጃ የጥናቱ መረጃ በመሆን አገልግሏል፡፡ ከሰነድ ፍተሻ በተጨማሪ ቃለ- መጠይቅ በሁለተኛና በአጋዥ ደረጃ የመረጃ መሰብሰቢያነት በመሆን ለዚህ ጥናት አገልግሏል፡፡

### 3.3.1 የሰነድ ፍተሻ

የዚህ ጥናት ትኩረት በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ማጠቃለያ ፈተናዎች፣ መርሀ ትምህርቱን መማሪያ መፅሃፍ የይዘት ተገቢነት ያላቸውን ዝምድና የሚመለከት በመሆኑ ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያው ሰነድ ፍተሻ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት የሚፈተሹ ሰነዶች የተሰጡ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎችና የ9ኛ ክፍል መርሃ ትምህርቶች እና መማሪያ መጻሕፍት ናቸው፡፡ ሌላው ደግሞ የተዘጋጁትፈተናዎችና አደረጃጀት በሰነድነት ይቆጠራሉ

፡፡ ፈተናዎቹም ከ2013-2014ዓ.ም በየዋ'ሽንየ አጠ/2ኛ/ደ/ትቤት ለ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የተሰጡ የአማርኛ ቋንቋ ማጠቃልያ ፈተናዎች ናቸው፡፡

### 3.3.2 ቃለ መጠይቅ

ለጥናቱ ደጋፊ መረጃዎችን ለማግኘት ቃለ መጠይቅ ሌላው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሆኖ አገልግሏል፡፡ ቃለ መጠይቅ ጠያቂና ተጠያቂ ፊት ለፊት በመገናኘት ጠያቂው ስለሚያነሳቸው ርዕሰ ጉዳይ ተጠያቂው ምላሽ የሚሰጥበት ሂደት ያለው መሆኑን ተመራጭ ያደርገዋል፡፡ ይህ ዘዴ ስራ ላይ ለማዋል የታሰበበት ምክንያት ፈተናዎችን፣ መርሀ ትምህርቶችና መማርያ መፅሃፍት ያላቸውን ዝምድና ለመፈተሽ በሚደረገው ሂደት በሰነድ ምርመራ የሚገኘውን መረጃ ለማጠናከር እና ተያያዥነት ያላቸውን ተጨማሪ መረጃዎችንም ለማግኘት ነው፡፡ ቃለ መጠይቁም የቀረበው ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን ነው፡፡

## 3.4 የመረጃ አተናተን ዘዴው

በዚህ ጥናት የተሰበሰቡትን መረጃዎች ለመተንተን አይነታዊ የመረጃ አተናተን ዘዴዎች ስራ ላይ ውልዋል። ጥናቱ አይነታዊ መረጃ የመተንተኛ ዘዴ ስልትን የተከተለበት ምክንያትም የጥናቱን ርዕሰ ጉዳዮች ለመግለጽ የሚያስችል ዘዴ በመሆኑ ነው። የጥናቱ የመረጃ መሰብሰብያ መሳሪያዎች ከሰነድ ፈተሻና ከቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ከተሰበሰቡ በኂላ በማደራጀትና የተደራጁትን በማቀናጀት አይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴን በመጠቀም በገለፃ ተተንትነው ቀርበዋል።

## 3.5. የምርምሩ ስነ- ምግባር

በዚህ ጥናት ሂደትም ከተደረገ ስነ-ምግባራዊ ሁኔታዎች ውስጥ በቅድሚያ የጥቱ እርዕስ እንደፀደቀ ከእዣ ወረዳ ትምህርት ፅ/ቤት የትብብር ደብዳቤ ለማፃፍ ተሞክሯል። በመቀጠልም ጥናቱ ወደ ሚካሄድበትና መረጃ ወደ የዋ'ሽንየ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በመሄድ የትብብሩን ደብዳቤ በማሳየት በአማርኛ ቋንቋ የማጠቃለያ ፈተናዎች ላይ አጥኚው ምርምር ማድረግ እንደሚፈልግ እና መረጃዎችን ከምዘና ኮሚቴዎች መሰብሰብ እንደሚያስፈልግ ስምምነት ላይ ተደረሰ። በስምምነቱ መሰረትም የሚሰጡት መረጃ ከጥናቱ አላማ ውጭ በመረጃ ሰጭዎች ላይ ምንም አይነት አሉታዊ ተፅዕኖ ማምጣት እንደማይችል በጋራ በመግባባት በቅንነት መረጃዎችን ለማግኘት ስምምነት ተፈጠረ። መረጃዎችን ከመረጃ

ሰጭዎች ፍላጎት ውጭ በምንም መልኩ የማይገለፁ መሆኑን  አጥኝው ግልፀነት መፈጠር ተችሏል፡፡  ስለሆነም አጥኝው የሚፈልገውን የሰነድና የቃለ መጠይቅ መረጃዎች በአግባቡ በማግኘት ጥናቱን መረጃ ሰጭዎችን በማይነካ መልኩ ለማከናዎን ችሏል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃ ትንተና ማብራሪያዎች

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በጉራጌ ዞን እዣ ወረዳ በዋሃንዬ አጠ/2/ደ/ት/ቤት የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ማጠቃልያ ፈተናዎችን የይዘት ተገቢነትን መገምገም ነው፡፡በዚህ ምዕራፍ ትኩረት የሚደረገው የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ ተግባራዊ ሆነው በተመረጡ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አማካኝነት የተሰበሰቡትን መረጃዎች በስርዓት በማቀናጀት የተገኘውን ውጤት በምዕራፍ ሁለት ከተነሱት ንድፍ ሃሳቦች እና በተመረጡት የመረጃ መተንተኛ ስልቶች ማብራራት ነው፡፡

የጥናቱን ውጤት ለማብራራት እንዲያመች በሁለት ንዑሳን ክፍሎች ተከፍሎ ቀርቧል፡፡ የመጀመሪያው ክፍል ከ2013- 2014 ዓ.ም ለ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የማጠቃለያ ፈተናዎችን ከይዘት ተገቢነት አኳያ የተገመገመበትን ሁኔታ የሚያሳይ ሲሆን የግምገማውም ትኩረት የተዘጋጁትን ፈተኛዎች ከመማሪያ መፅሃፍቱ፣ ከፈተናዎቹ እና ከመርሐ ትምህርቱ ጋር ምን አይነት ትስስር እንዳላቸውና ምን ምን የቋንቋ ይዘቶች እንደተካተቱ፣ ፈተናዎቹ ለየትኛው የትምህርት ይዘት የበለጠ ትኩረት እንደሰጡ ለማየት ተሞክሯል፡፡

በሁለተኛው ክፍል ደግሞ ምሁራን በሚያቀርቧቸው የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች አዘገጃጀትና አቀራረብ ከዚህ ቀደም ከተነሱ ንድፍ ሃሳቦች አንፃር የተዘጋጁት ጥያቄዎች ከቋንቋ ፈተና ዝግጅትና አቀራረብ መርሆዎች መሰረት ለዘጠነኛ ክፍል በተዘጋጁ ፈተናዎች ውስጥ ጥያቄዎች አቀራረብ ላይ ያሉ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ብሎም ፈተናው ትክክለኛ የቋንቋ ንሞናን ተከትሎ መዘጋጀትና አለመዘጋጀቱን በተመለከተ ያለውን መረጃ ያሳያል፡፡

## 4.1 የመረጃ ትንተና ማብራሪያዎች

በጉራጌ ዞን በእዣ ወረዳ በየዋሽንየ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከ2013-2014 ዓ.ም ለዘጠነኛ ክፍል ተዘጋጅተው የቀረቡ የማጠቃለያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች የይዘት ተገቢነት በተመለከተ በሰነድ ፍተሻና በቃለ መጠይቅ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ የተሰበሰቡትንም መረጃዎች ከጥናቱ መሪ ጥያቄዎች አንፃር እንደባህሪያቸው በቅደም ተከተል በማደራጀት እንደሚከተለው ለማብራራት ተሞክሯል፡፡.

የዚህ ጥናት የመጀመሪያው ጥያቄ የተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ከመርሃ ትምህርቱና ከመማሪያ መፅሀፍቱ ጋር ምን አይነት ግንኙነት አላቸው? የሚል ነው፡፡ የዚህን ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት በዋናነት በሁለቱም አመት(በአራቱም ወሰነ ትምህርት) የተሰጡትን የቋንቋ ፈተናዎች የፈተና ሰነዶች፣መርሃ ትምህርቱን፣መማሪያ መፅሀፉን፣መነሻ በማድረግ በትምህርት ቤቱ ለፈተና አዘጋጆች  ቃለ መጠይቅ በማድረግ የተገኙትን መረጃዎች በሰንጠረዥና በሀተታ እንደሚከተለው ለመተንተን ተችሏል፡፡

**ሰንጠረዥ1፡-ለዘጠነኛ ክፍል በተዘጋጀው መርሃ ትምህርት ውስጥ የትምህርት ይዘቶች ውክልና ሲታይ**

| ተ.ቁ | ይዘቶች | ዘጠነኛ ክፍል | |
|---|---|---|---|
| | | የይዘቶች መጠን | በመቶኛ ሲሰላ |
| 1. | ሰዋስው | 43 | 34.4 |
| 2 | ስነ-ፅሁፍ | 11 | 8.8 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 3. | ክሂል | 9 | 7.2 |
| 4. | ቃላት | 19 | 15.2 |
| 5. | ቋንቋ | 43 | 34.4 |
| | ድምር | 125 | 100 |

ከዚህ በላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው ከ2013 እስከ 2014 ዓ.ም ለዘጠነኛ ክፍል በተዘጋጀው መርሃ ትምህርቱ ውስጥ የተካተቱትን የትምህርት ይዘቶች ጥቅል መረጃ የሚያሳይ ነው። በሰነድ ፍተሻ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ አማካኝነት የተገኙት መረጃዎች እንደሚጠቁሙት በመርሃ ትምህርቱ ተማሪዎች እንዲማሩትና መምህራን እንዲያስተምሩት የተቀረፁትን የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች መጠን ሲቆጠሩ 125 ሲሆኑ በውስጡ ፣ክሂሎች፣ ሰዋሰው፣ስነ-ፅሁፍ፣ቃላት እና ቋንቋ ነክ ይዘቶች ተካተው ይገኛሉ።በመርሃ ትምህርቱ ከቀረቡት ይዘቶች አንፃር ሰዋሰው እና ቋንቋ ነክ ይዘቶች እያንዳንዳቸው (43) 34.4% የያዙ ሰሆን ስነፅሁፍና ክሂል ደግሞ (11) 8.7% እና (9) 7.2% በቅደም ተከተል ድርሻ ይዘዋል። ቃላት ደግሞ (19) 15.2% ድርሻ የሚሸፍን ሲሆን ከመርሃ ትምህርቱም ዝግጅት አንፃር ሲፈተሽ ተገቢ የይዘት አቀራረብ  እንዳልተላበሰ መረዳት ተችሏል።በመርሃ ትምህርቱ ከቀረቡት ይዘቶች አንፃር ሰዋስውና ቋንቋ  ሰፊ ሽፋን የተሰጣቸው ሲሆን በአንፀሩ ክሂሎችና ስነ-ፅሁፍ ግን በጣም ዝቅተኛ ሽፋን የተሰጣቸው ናቸው።አሁን ባልንበት ዘመን የቋንቋ ትምህርት መስጠት ያለበት ለክሂልና ለስነ-ፅፋፍ ወይም ለተግባቦት ሆኖ ሳለ ለቋንቋ መዋቅር ትኩረት መስጠቱ እንደውስንነት የሚታይ ነው፡

**ሰንጠረዥ2፡ በመማሪያ መፅሃፉ ውስጥ የተካተቱት ቋንቋ ይዘቶችን መጠንን የሚያሳይ መረጃ**

| ተ.ቁ | ይዘቶች | የይዘቶች መጠን | በመቶኛ ሲገለፅ |
|---|---|---|---|
| 1 | ሰዋስው | 65 | 39.39% |
| 2 | ስነ-ፅሁፍ | 40 | 24.24% |
| 3 | ክሂል | 20 | 12% |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 4 | ቃላት | 23 | 13.9% |
| 5 | ቋንቋ | 15 | 9% |
| | ድምር | 165 | 100% |

ከላይ በሰንጠረዡ የቀረበው መረጃ የሚያሳየው ከ2013- 2014 ዓ.ም የዘጠነኛን ክፍል ለማስተማር በቀረበው መማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የቀረቡትን የሰዋው ይዘቶችን የሚያሳይ ነው፡፡ በዚህም መሰረት በመማሪያ መፅሃፉ ውስጥ ከተካተቱት ይዘቶች መካከል አንዱ ሰዋሰው ሲሆን 65(39.39% ሽፋን ተሰጥቶታል፡፡ይህ የትምህርት ይዘት በውስጡ ስነ-ድምፅ፣ስነ-ምዕላድ፣ስነ-አገባብና ስነ-ፍቺ ይገኙበታል፡፡ሌላው ስነ-ፅሁፍ ሲሆን 40(24.24%) ሽፋን የተሰጠው ሲሆን በውስጡ ስነ-ቃል፣ስነ-ግጥም፣ልቦለድ ተውኔት፣ኢልቦለዳዊ ይዘቶች ተካተዋል፡፡ሌላውክሂልሲሆን20(12%)ያገኘሲሆን በውስጡም የማዳመጥ፣የመናገር፣የማንበብና የመጻፍ ይዘቶች ተካተዋል፡፡በዚሁ መማሪያ መፅሐፍ ቃላት 23(13.9%)፣ቋንቋ ነክ 15(9)% የይዘት ሽፋን ተሰጥቷቸዋል፡፡ከዚህ አንፃር አሁንም በመርሐ ትምህርቱ እንደተስተዋለው ለሰዋስው የትምህርት ይዘት ትልቅ ትኩረት የተሰጠ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ እጅግ አስፈላጊ የሆኑት ክሂልና ቃላት ብዙም ትኩርት የተሰጣቸው የትምህርት ዘቶች ባለመሆናቸው የትምህርት ግቡን የሳተ መማሪያ መፅሃፍ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡

ከዚህ ሀሳብ የምንረዳው በመማሪያ መፅሃፉ ተማሪዎች እንዲገነዘቧቸው የቀረቡት የትምህርት ይዘቶች የተሰጠው ደረጃ ከመርሃ ትምህርቱ ጋር የተሻለ ቅርርቦሽ እንዳላቸው ነው፡፡ ይህ ማለት ግን በመማሪያ መፅሃፉ ውስጥ ያሉት የቋንቋ ይዘቶች ሙሉ በሙሉ ከመርሐ ትምህርቱ ውስጥ ይገኛል ማለት አይደለም፡፡

**ሰንጠረዥ3፡- በመርሐ ትምህርቱ፣በመማሪያመፅሀፍቱና በፈተናዎች መካከል ያሉት ይዘቶች ግንኙነት በቁጥርና በመቶኛ**

| ይዘቶች | የቋንቋ ይዘቶች በመርሃ ት/ቱ ያገኙት ውክልና | በመማሪያ መፅሀፍቱ የተካተቱ ይዘቶች | በፈተናው የተካቱ የቋንቋ ይዘቶች ውክ ልና ከ2013-2014ዓ. |
|---|---|---|---|

| | መጠን | በመቶኛ | መጠን | በመቶኛ | መጠን | በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሰዋሰው | 43 | 34.4 | 65 | 39.39% | 56 | 35.% |
| ስነ-ፅሁፍ | 11 | 8.8 | 40 | 24.24% | 63 | 39.375% |
| ቃላት | 9 | 7.2 | 20 | 12% | 20 | 12.5% |
| ኪ.ሒ.ል | 19 | 15.2 | 23 | 13.9% | 20 | 12.5% |
| ቋንቋ ነክ | 43 | 34.4 | 15 | 9% | 1 | 0.625% |
| ድምር | 125 | 100 | 165 | 100% | 160 | 100% |

በሰንጠረዡ ያለው መረጃ እንደሚያሳየን የቀረቡት የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በመርሐ ትምህርቱ፣በመማሪያ መፅሐፍ እና በሁለቱም አመት (በአራቱም ወሰነ ትምህርት ) የቀረቡት የቋንቋ ጥያቄዎች ከተተኳሪ ፈተናዎች ውስጥ ያገኙትን የትኩረት ደረጃ የሚያሳይ ነው፡፡ ስለሆነም በፈተናዎቹ ውስጥ የቀረቡት የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በመርሐ ትምህርቱና በመማሪያ መፅሃፉ ውስጥ ካሉት የቋንቋ ይዘቶች በሚቀራረብ መልኩ መቅረባቸውን ያሳያል፡፡ በሁለቱም አመት የቀረቡት የቋንቋ ጥያቄዎች ይዘቶች ከመማሪያ መጽሐፉም ሆነ ከመርሐ ትምህርቱ ጋር ስናነፃፅራቸው የመቀራረብ እድል አላቸው እንጅ በመርሁ መሰረት እንዳልቀረቡ ግን መረዳት ተችሏል፡፡ ይህ ማለት በፈተናው የተካተቱት የቋንቋ ፈተና ይዘቶች መጠን በመርሐ ትምህርቱና በመማሪያ መፅሀፉ ከተሰጠው መጠን በላይ የላቀ ነው፡፡ ይህም በጥቅሉ ሲታይ በፈተናው የቀረቡት የቋንቋ ፈተና ይዘቶች 160 ትኩረት ሲያገኝ በመርሀ ትምህርቱ 125 ሲሆን በመማሪያ መፅሃፉ ደግሞ 165 ዋጋ ተሰጥቶታል፡፡ከዚህ መረጃ የምንረዳው የተዘጋጁት የቋንቋ ፈተናዎች ከመርሃ ትምህርቱና ከመማሪ መፅሀፉ ከተቀመጡት ይዘቶች አንፃር ተቀራራቢና ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ እንደሆኑ ለመረዳት ተችሏል፡፡ይህም ማለት ፍፁም ተመሳሳይ ናቸው ለማለት ሳይሆን ተቀራራቢ እንደሆኑ ነው፡፡

**ሰንጠረዥ 4:በሁለቱም አመት በተዘጋጁት ፈተናዎች ውስጥ ምን ምን የቋንቋ ይዘቶች ተካተዋል**

| ይዘቶች | በፈተናው የተካተቱ የቋንቋ ይዘቶችን አይነት የሚያሳይ መረጃ | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 2013 | | | | 2014 | | | | ድምር | |
| | 1ኛው ወሰነ | | 2ኛው ወሰነ | | 1ኛው ወሰነ | | 2ኛው ወሰነ | | | |
| | ብዛት | በ% | ብዛት | በ% | ብዛት | በ% | ብዛት | በ% | ብዛት | በ% |
| ሰዋስው | 20 | 50 | 16 | 40 | 12 | 30 | 8 | 20 | 56 | 35 |
| ስሰ-ጽሁፍ | 10 | 25 | 15 | 35.5 | 17 | 42.5 | 25 | 62.5 | 63 | 39.375 |
| ቃላት | 4 | 10 | 6 | 12 | 3 | 7.5 | 7 | 17.5 | 20 | 12.5 |
| ክሒል | 20 | 12.5 | 3 | 7.5 | 7 | 17.5 | 0 | 0 | 20 | 12.5 |
| ቋንቋ ነክ | 0 | 0 | 0 | | 1 | | 0 | 0 | 1 | 0.625 |
| ድምር | 40 | 100 | 40 | | 40 | | 100 | 100 | 40 | 100 |

ከዚህ በላይ ከቀረበው የሰንጠረዥ መረጃ ለመረዳት እንደሚቻለው በጉራጌ ዞን እዣ ወረዳ በየዋሸንዬ አጠ/2/ደ/ት/ቤት ለዘጠነኛ ክፍል ለሁለት ተከታታይ አመት እየተዘጋጁ የቀረቡ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎችን ስንመለከት ከቀረቡት አጠቃላይ ፈተናዎች ውስጥ 160 የሚሆኑት በተለያዩ መልክ የቀረቡ ነበሩ፡፡ በነዚህ ፈተናዎች ውስጥ ሰዋስው56(35%)፣ስነ-ፅሁፍ63(39.375%)፣ቃላት12(12.5%)፣ክሒል20(12.5%) ቋንቋ ነክ ይዘቶች 1(0.625%) በፈተና መልክ ተካተዋል፡፡ በነዚህ ስር ደግሞ የተለያዩ ንዑሳን ይዘቶች ተካተው ቀርበዋል፡፡ በዚህ መሰረት በሁለቱም አመት ከቀረቡት ፈተናዎች ውስጥ ለስነ-ፅሁፍ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው ሲሆን ከዚህ በመቀጥል ለሰዋስው የትምህርት ይዘት የበለጠ ትኩረት እንደተሰጠ ያመላታል፡፡በመቀጠልም ለክሂልና ለቃላት እኩል ትኩረት የተሰጠ ሲሆን ለቋንቋ ነክ የትምህርት ይዘቶች ግን በጣም አነስተኛ ትኩረት የተሰጠው ነበር፡፡ ከዚህ አኳያ የይዘት ስርጭቱ በአንፃራዊነት የተሸለ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡

ስለሆነም በ2013ዓ.ም በመጀመሪያው እና ሁለተኛው ወሰነ ትምህርት ከቀረቡት 80 ጥያቄዎች መካከል ስነፅሁፍ 21(26.25%)፣ ሰዋስው 36(45%)፣ ክሂል13(16.25%)፣ቃላት 10(12.5%) ቋንቋ ነክ ጥያቄዎች 0(0%) ቀርበዋል፡፡በዚህ ደረጃ ስንመለከት ደግሞ ለሰዋስው የበለጠ ትኩረት የተሰጠ ሲሆን ቀጥሎ ለስነ-ፅሁፍ የት/ት ይዘት ነው የበለጠ ትኩርት የተሰጠው፡፡በመቀጠልም ለክሂልና ለቃላት በቅደም ተከተል ትኩርት እንደተሰጠ ያሳያል፡፡ከዚህ አንፃር ተቀራራቢ የይዘት መረጣና አካታችነት እንዳለ ቢታመንም መሰረታዊ ልዩነቶች እንዳሉ ደግሞ መረዳት ይቻላል፡፡ በተናጠል ሲታይም እንደዚሁ በ2014ዓ.ም ከቀረቡት 80 ጥያቄዎች መካከል ስነ--ፅሁፍ 42(52.5) ከፍተኛውን ቦታ የያዘ ሲሆን በመቀጠል ሰዋስው 20(25) ድርሻ ተሰጥቶታል፡፡በሌላ በኩል ቃላት 10(12.5)፣ክሂል 7(8.75) እና ቋንቋ ነክ ጥያቄዎች ደግሞ 1(1.25) ቦታ አግንተዋል፡፡ስለሆነም ከመመማሪያ መፅሀፍና ከመርሃ ትምህርቱ ከተቀመጠው አንፃር የይዘት አካታችነት አንፃር ሲታይ የተሸለ እንደሆነ ቢታይም የቅርርብ መጠናቸው ደግሞ ልዩነት ይስተዋልባቸዋል፡፡ከዚህ አኳያ የተወሰኑ ውስንነቶች እንዳሉ ማየት ተችሏል

በሌላ በኩል በ2013 እና በ2014ዓ.ም በትምህርት ቤት ደረጃ ከተሰጡ ፈተናዎች የስርጭታቸውን መጠን በንዑሳን ይዘት በምናይበት ጊዜ በአንፃራዊነት የተሻለ ነው፡፡ በ2013ዓ.ም ከቀረቡት ይዘቶች መካል በሰዋስው ውስጥ ከሚገኙ የትምህርት ይዘቶች ውስጥ ምዕላድ፣ የቃል ክፍሎች፣የሀረግ አይነቶች፣ ስነ-አገባብ፣ አንቀፅ፣ የአረፍተ ነገር አይነቶች ስነ-ፍች ወዘተ ተካተዋል፡፡ ስነ-ፅሁፍን በምንመለከትበት ጊዜ፣ስነ-ቃል፣የስነ-ቃል አይነቶች፣ ኪነ ጥበብ፣ ስነ-ግጥም፣ ቅኔ፣ ምሳሊያዊ አነጋገር፣ ልቦለድና ተውኔት ተካተው ይገኛሉ፡፡ ክሒልን በተመለከተ፣ የመፃፍ፣ የማዳመጥና የንግግር ክሒልን ያገናዘቡ ጥያቄዎች አካተቶ ይዟል፡፡ ቃላትን በተመለከተ፣ የቃላት ፍቺ፣ አውዳዊ የቃላት ትርጉም የመሳሰሉትን ይዟል፡፡ ነገር ግን ምንም አይነት ቋንቋ ነክ የሆኑ ይዘቶች በፈተናው አልተካተቱም፡፡ በ2014ዓ.ም ከቀረቡ 80 ጥያቄዎች መካል ደግሞ ሰዋስው የቃል ክፍሎች፣አረፍተ ነገር፣ አያያዝ ቃላት፣ ስነ-ድምፅ፣ የሀረግ አይነቶች፣ አንቀፅ፣ መስራች ምእላድ፣ ስነ-አገባብ ወዘተ የተካተቱ ሲሆን ስነ-ፅሁፍን በተመለከተ ደግሞ ተውኔት፣ ልቦለድ፣ ኢ-ልቦለድ ስነፅሑፍ ቅኔ፣ ስነግጥም፣ አባባሎች፣ ምሳሊያዊ አነጋገሮች፣ ስነ-ቃል፣ ድርሰት ወዘተ በንዑሳን ይዘትነት በፈተናው የተካተቱ ጥያቄዎች ናቸው፡፡በሌላ በኩል ክሂልን በተመለከተ የመናገር ክሒል፣የማዳመጥ ክሒል፣የንባብ ክሂል ወዘተ በፈተናው ተካተዋል፡፡ በሌላ በኩል ቃላትን በምንመለከትበት ጊዜ አውዳዊ ፍችና ፈሊጥዊ ፍችዎች በፈተናው ተካተዋል፡፡በጥቅሉ ሲወሰድ በሁለቱም አመታት በቀረቡት

ጥያቄዎች ውስጥ የተሸለ የይዘት አካታችነት የታየ ሲሆን በሁለቱም አመት ለስነ-ፅሁፍና ለሰዋስው የበለጠ ትኩረት የተሰጠ ሲሆን ለቃላት፣ለቋንቋ ነክ እና ለክሒል የተሰጠው ትኩረት ተቀራራቢና አነስተኛ መሆኑ እንደ ውስንነት የተስተዋለበት ነው፡፡ በንዑሳን ይዘቶች ስርጭትም ቢሆን ለሰዋስውና ለስነ-ፅሁፍ የተሰጠው ትኩርት ከፍተኛ ሲሆን በአንፃሩ ለሌሎች የተሰጠው ትኩረት ዝቅተኛ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡

ከዚህ መረዳት የሚቻለው በመማሪያ መፅሐፉ የቀረቡት የሰዋስው ይዘቶችን ለማስተማር ከቀረቡት ጥያቄዎች ውስጥ ከፍተኛውን ስፍራ የያዘው ስነ-ፍችን ለመለማመድ የቀረቡት የሰዋሰው ይዘቶች ሲሆኑ በአንፃሩ በመማሪያ መፅሐፉ በጣም አነስተኛውን ድርሻ የያዘው ስነ-ድምፅ ነው፡፡ ስነ- አገባብና ስነ-ምዕላድ እንደቅደም ተከተላቸው ከስነ-ፍች ቀጥሎ የተሻለ ተመጣጥኖ ያላቸው የሰዋስው ይዘቶች ሆነው ተገኝተዋል፡፡ በፈተናዎቹም የቀረቡት የሰዋስው ይዘቶች መጠን በዚሁ ልክ የሚፈረጁ ናቸው፡፡ ነገር ግን በመማሪያ መፅሀፉና በፈተናዎቹ መካከል ያለው የሰዋስው የመጠን ሁኔታ ልዩነት አላቸው፡፡ በመማሪያ መፅሀፉና በሰዋስው ይዘቶች መካከል ያለው ቅርርቦሽ የተሻሉ ቢሆኑም ውስንነቶች እንዳላቸው ግን መረዳት ይቻላል፡፡ የተዘጋጁት የሰዋስው ፈተናዎቹ የተቀረፁበት ሁኔታ ደግሞ መማሪያ መፅሐፉ ላይ ካሉ የሰዋስው ይዘቶች እንደሆነ የተገኘውን ውጤት በመረጃ በማቅረብ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከስነ-ፅሁፍ አኳያ ለልቦለድና ለግጥም የተሰጠው ክብደት ከፍተኛ ሲሆን ለስነ-ቃልና ለለተውኔት የተሰጠው ክብደት ከሌሎች አንፃር አነስተኛ እና ፍትሃዊ ያልሆነ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፡ ፡በመሆኑም የፈተና መርሆዎችን የጣሰ የፈተና ዝግጅት እንደነበረ ለመረዳት ተችሏል፡፡በክሂል፣ በቃላትና ቋንቋ ነክ ጉዳዮች ላይ በዚሁ መልክ የሚገለፅ ነው፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የዚህ ጥናት ጥያቄ የነበረው በማጠቃለያ ፈተናዎቹ ውስጥ የቀረቡት የቋንቋ ጥያቄዎች ለየትኛው የት/ት ይዘት የበለጠ ትኩረት የሰጡ ናቸው? የሚል ነው፡፡

ለዚህም ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት በሁለቱ አመት የተሰጡ የፈተናዎችን ሰነድ መሰረት በማድረግ ለመተንተን የተሞከረ ሲሆን ከቀረቡት የሁለት አመተ ፈተናዎች የትምህርት ይዘቶች አንፃር ማለትም ከስነ-ፅሁፍ፣ከሰዋስው፣ከቃላት፣ከክሂልና ከቋንቋ ነክ ጉዳዮች አኳያ ለመፈተሽ ተሞክሯል፡፡ስለሆነም በሁለቱም አመት ማለትም በ2013 እና 2014ዓ.ም ከተሰጡ ፈተናዎች ውስጥ በጥቅሉ ሲታይ የበለጠ ትኩረት የተሰጠው ለስነ-ፅሁፍ የትምህርት ይዘቶች ሲሆን በመቀጠል ለሰዋስው ትምህርት ዘርፎች የበለጠ ትኩረት የተሰጠ ሲሆን ከዚያ

በመቀጠል ለክሂል፣ለቃላትና ለቋንቋ ነክ ይዘቶች በቅደም ተከተል የተሰጠ ነው። በዝርዝር ሲታይ በየወሰነ ትምህርቱ ከቀረቡት ፈተናዎች ለመረዳት እንደሚቻለው የትኩረት መስኮች ተለዋዋጭና ወጥነት ያላቸው አይደሉም።እንደዚህ እንዲሆኑ የሚጠበቅ ባይሆንም ከፈተና ፈተና ለአንዱ የተሰጠው ክብደት በሌለኛው ጊዜ ከተሰጠው ፈተና አንፃር የተለያዩ ናቸው። ይህንን ጉዳይ በመረጃ በጥቅሉ ስንመለከት በ2013 በመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት ስነ-ፅሁፍ 6(15%)፣ ሰዋስው 20(50%)፣ ክሒል10(25%) ቃላት 4(10%) እና ቋንቋ 0(0%) የስርጭት መጠን እንደተሰጠው ያሳያል።ስለሆነም በዚህ መረጃ መሰረት ለሰዋሰው የበለጠ ቦታ የተሰጠው ሲሆን በመቀጠል ደግሞ ለክሂል የተሻለ ቦታ ለመስጠት ተሞክሯል።በሌላ በኩል ዝቅተኛ ቦታ የተሰጠው ለቋንቋ ነክ የትምህርት ይዘቶች ነው። በ2013ዓ.ም በ2ኛው ወሰነ ትምህርት ከቀረቡት 40 ጥያቄዎች መካከል ሰዋስው 16(40%) ስነ-ፅሁፍ 15(35.5%)፣ ቃላት6(5%)፣ክሂል3(7.5%) እና ቋንቋ ነክ ይዘቶች ደግሞ 0(0%) ቦታ አግኝተዋል።በዚህ መረጃ መሰረት አሁንም ለሰዋስው የበለጠ ትኩረት የተሰጠ ሲሆን ለስ-ፅሁፍ ከሰዋስው ቀጥሎ ትኩረት የተሰጠ ይዘት ነው።ሌላው ቃላት እና ለቋንቋ ነክ ይዘቶች በቅደም ተከተል ትኩረት ለመስጠት ተሞክሯል።ከዚህ አንፃር በ2013ዓም ፈተና ሰዋስው የበለጠ ትኩረት የተሰጠ ሲሆን ለቋንቋ ነክ ይዘቶች ምንም አይነት ትኩረት እንዳልተሰጠ ያመለክታል። ስለሆነም ትክክለኛ የፈተና መርህን ተከትሎ እንዳልተዘጋጀ ለመረዳት ተችሏል።የ2014ዓ.ም ከቀረቡት 80 ጥያቄዎች ስንመለከት በ1ኛው ወሰነ ትምህርት 40 ጥያቄዎች የቀረቡ ሲሆን ስነ-ፅሁፍ 17(42.5%)፣ሰዋስው 12(30%)፣ክሒል 7 (17.5%)፣ ቋንቋ ነክ ደግሞ 1(2.5%) የስርጭት መጠን ተሰጥቷል።ስለሆነም ከቀረበው መረጃ ለመረዳት እንደተሞከረው ለስነ-ፅሁፍ የተሸለ ትኩረት የተሰጠ ሲሆን በመቀጠል ደግሞ ለሰዋስው የተሻለ ትኩረት ለመስጠት እንደተሞከረ ማየት ተችሏል።ነገር ግን አሁንም ለቃላትና ለቋንቋ ነክ ጉዳች ዝቅተኛ የስርጭት መጠን እንደተሰጣቸው መረዳት ይቻላል።ስለሆነም የይዘት አካታችነቱ ፍትሀዊነቱና በሳይንሱ መሰረት ሳይሆን የፈተና አዘጋጆቹ እንደፈለጉ እንዳወጡት ያሳያል። የ2014ዓ.ም የ2ኛው ወሰነ ትምህርት የቀረቡትን 40 ጥያቄዎወች በምንመለከትበት ጊዜ አሁንም ለስነ-ፅሁፍ 25(62.5%)፣ ሰዋስው 8(20%)፣ቃላት7(17.5%) ለክሒልና ለቋንቋ ይዘቶች 0(0%) የስርጭት መጠን ተሰጥቷቸዋል።ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው ለስነ-ፅሁፍ የተሰጠው ትኩረት ከሌሎቹ የትምህርት ይዘት አንጻር 62.5%የሚይዝ በመሆኑ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠውና በሌሎች የትምህርት ይዘቶች ተማሪዎች እንዳይለኩ የሚያደርግ ነው።

አንድ ይዘት ሰፊ መጠን በሚሰጠው ጊዜ በሌሎች ይዘቶች ተማሪዎች እንዳሉ ያደርጋል፡፡ ስለሆነም ለተወሰኑ የትምህርት ይዘቶች ትኩረት የተነፈጋቸው ሲሆን ለተወሰኑት ደግሞ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ይዘት ስርጭት ላይ ከፍተኛ ክፍተት እንዲፈጠርና ተማሪዎች መለካት ባለባቸው የትምህርት ይዘቶች ሳይለኩ እንዳይቀሩና ከፈተና ትክክለኛነት አንፃር ችግሮች እንዳሉ ለመረዳት ተችሏል፡፡

ከዚህ መረጃ መረዳት የሚቻለው በሁለቱ አመት የቀረቡት ፈተናዎች ሲዘጋጁ በዘፈቀደ እንጅ በወቅቱ የምዘና ሳይንስና የይዘት ንሞና መረጣን መሰረት ያደረገ እንዳልሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በምዕራፍ ሁለት በተለያዩ ንድፍ ሃሳቦች ለማንሳት እንደተሞከረው እና መርሃ ትምህርቱ እንደሚለው አንድ ፈተና ሲዘጋጅ እጅግ በጣም ጥንቃቄ የሚጠይቅ ሲሆን በመሰረታዊነት እንደፈተናው አይነት ፍትሃዊ የሆነ የይዘት ንሞና መውሰድ እንዳለበት ይታወቃል፡፡ ይሁንና ከ2013-2014 ዓ.ም በጉራጌ ዞን እኀ ወረዳ በየዋኽንየ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለዘጠነኛ የክፍል ደረጃ ተዘጋጅተው ከቀረቡት 160 ጥያቄዎች ውስጥ በሰዋስው መልክ የቀረቡት ከይዘት ትክክለኛነት አንፃር ስንመለከታቸው ችግር ያለባቸው እንደሆኑ ማየት ይቻላል፡፡ በጥቅሉ በፈተናው ውስጥ ለሰዋስው የተሰጠውን ትኩረት ስናይ ይበል የሚያሰኝ ነው፡፡ ነገር ግን በተናጠል በተከታታተይ አመት ከቀረቡቱ የሰዋስው ንዑሳን ይዘቶች አኳያ ስንመለከት ለስነ-ድምፅ የተሰጠው ትኩረት በጣም አነስተኛ ነው፡፡

በሁለቱም አመት ሆነ ተብሎም ይሁን ሳይታሰብ ለስነ- ፊች ከፍተኛ ቦታ እንደተሰጠ ማየት ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል ለስነ-አገባብና ለስነ-ምዕላድ ከስነ- ፍች ቀጥሎ ትኩረት የተሰጣቸው ይዘቶች እንደሆኑ ማየት እንችላልን፡፡ይህ ሁኔታ በሌሎቹም የትምህርት ይዘቶች የሚስተዋል ችግር ነው፡፡ ስለሆነም ፈተናው ሲዘጋጅ እንደ ይዘት ከሁሉም የቋንቋ ንዑሳን ይዘቶች በመርሐ ትምህርቱ እንደተሰጣቸው የጊዜና የስርጭት መጠን በማሰብ በንፅፅር መቅረብ ነበረበት፡፡ ለሰዋሰው ከተሰጠው ምጣኔ አኳያ ደግሞ ለሁሉም የትምህርት ይዘቶች ቦታ የሰጡ አይደሉም፡፡ ለሌሎችም ቢሆን ማለትም ለስነ-ፅሁፍ፣ ለቃላት፣ የተሰጠው ትኩረት ይቀራረባል እንጅ ተመጥኖ ተገቢ ንሞና ተወስዶ ተማሪዎችን በሁሉም የትምህርት ይዘት ለመለካት ለማብቃት ታስቦ እንዳልተዘጋጁ ያሳያል፡፡በሌላ አገላለፅ በአራቱ ዋና ዋና የስዋስው ይዘቶች ስር ላሉ የተለያዩ ሰዋስው ነክ የትምህርት ይዘቶች የተሰጠው ትኩረት አናሳ ነው፡፡ በየአመተ ምህረቱ ከተሰጡት የሰዋስው ፈተናዎች ውስጥ ለንዑሳን

የስዋስው ይዘቶች የተሰጠው እድል በጣም የተራራቀ ነው፡፡ በሁለቱም አመት ከቀረቡ ፈተናዎች ውስጥ ቋንቋ ነክ የሆኑና ለተለያዩ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት ይዘቶች ትኩረት አልተሰጠም፡፡ በመርሃ ትምህረቱና በመማሪያ መፅሃፉ በይዘትነት በብዛት ቢቀርም በፈተናው የተዘነጉ እንደሆነ ከሰነዱ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህም መሆኑ ደግሞ ከዚህ መርህ አንፃር ፈተናዎቹ ውስንነነት ያለባቸው እነደሆኑ መረዳት ይቻላል፡፡፡፡

**ሶስተኛው የዚህ ጥናት መሪ ጥያቄ የተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ ማጠቃለያ ፈተናዎች** የይዘት ተገቢነት መርሆዎችን ያሟሉ ናቸው? የሚል ሲሆን በቋንቋ ፈተና የተለያዩ ምሁራን ካስቀመጧቸው የፈተና መገምገሚያ መርሆዎች አንጻር እንደሚከተለው ለማሳየት ይሞከራል፡፡

### 4.1.1 ከይዘት አካታችነት አንጻር የተገኙ መረጃዎች ትንተና

እንደ አጠቃላይ ሲታይ አንድ የችሎታ መለኪያ ፈተና ሲዘጋጅ በመማሪያ መፅሀፉ፣በመርሃ ትምህርቱ የቀረቡ የትምህርት ይዘቶች ሁሉ እንደድርሻቸው በሳይንሱ መሰረት የፈተና አካል እንደሚሆኑ አይተናል፡፡

ፈተናዎች ከሚገመገሙበት አንዱ ከፈተና መርሆች ነው፡፡ከዚህ አንፃር በአራቱም ወሰነ ትምህርት የተዘጋጁት የቋንቋ ፈተናዎች በምዕራፍ ሁለት ከተነሱት ፅንሰ ሀሳቦች አንፃር ሲታይ ካሉት ነጥቦች ጥንካሬ ባሻገር በርካታ ውስንነቶች አሉት፡፡ፈተናዎች ከእውቀት፣ባሻገር ያሉት የባህሪ ለውጦችን የትምህርቱን አላማ ከቀላል እስከ መካከለኛ እውቀት ያላቸውን ተማሪዎች ከመለካት አንጻር ውስንነቶች ይታይባቸዋል፡፡ውስንነቶችን ከቋንቋ ፈተና ይዘት አመራረጥ ጋር ከሚነሱት መርሆዎች አኳያ ሲሆን እንደሚከተለው በገለፃ ይቀርባሉ፡፡ በመሆኑም ይዘቶቹ በየፈርጃቸው ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ ተመርጠው ይቀርባሉ፡፡ከዚህ አንፃር በሁለቱ አመት (በአራቱ ወሰነ ትምህርት) የተዘጋጁትን ፈተናዎች ስንመረም የፈተናና ምዘና ሳይንስ በሚለው መልክ በቋንቋ ይዘቶች ስር የሚገኙ ይዘቶችን አካተው የያዙ ናቸው ባያስብልም በአብዛኛው ይዘቶቹ ተካተው ይገኛሉ፡፡ ነገር ግን በአራቱም ወሰነ ትምህርት በቀረቡት ፈተናዎች ይዘቶች እኩልና ተመጣጣኝ ድርሻ እንደሌላቸው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በ2013ዓ.ም የመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት ሰዋሰው ከፍተኛውን ቦታ ሲይዝ ክሂልና ስነ-ፅሁፍ መጠነኛ ይዟል፣ቃላት ዝቅተኛ ሲሆን ቋንቋ ነክ በአንፃሩ ምንም አይነት ድርሻ

አልተሰጠውም፡፡በ2013ዓ.ም በ2ኛው ወሰነ ትምህርት ሰዋስውና ስነ-ፅሁፍ ከፍተኛውን ቦታ ሲይዙ ቃላት መጠነኛ ድርሻ ያየዘ ሲሆን ክሂል ደግሞ ዝቅተኛ ድርሻ ሲኖረው ቋንቋ ነክ የትምህርት ይዘቶች አሁንም ምንም አይነት ድርሽ አላገኙም፡፡ በ2014ዓ.ም የመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት ስነ-ፅሁፍ ከፍተኛ ድርሻ ሲሰጠው  ሰዋስው መካከለኛ፣ክሂል መጠነኛ ድርሻ ሲያገኝ ቃላትና ቋንቋ ነክ በቅደም ተከተል ዝቅተኛውን ድርሻ ይዘዋል፡፡ በ2014ዓ.ም በ2ኛው ወሰነ ትምህርት የስነ-ፅሁፍ ይዘት በጣም ከፍተኛ ድርሻ ሲኖረው በአንፃሩ ሰዋሰውና ቃላት መጠነኛ ድርሻ ሲያገኙ ክሂልና ቋንቋ ነክ በአንፃሩ ምንም ድርሻ እንዳልተሰጣቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡ይህ ችግር በቀረቡት በፈተናዎቹ ብቻ ሳይሆን በመርሃ ትምህርቱና መማሪያ መፅሀፍቱ ሲዘጋጅ መጠነኛ ክፍተት ቢኖርበትም በፈተናዎቹ የታየው ችግር ግን በጣም የገዘፈ ነው ማላት ይቻላል፡፡ስለሆነም ፍተሃዊ የሆኑ የይዘት ምርጫና አካታችነት እንደሚጎላቸው ከፈተና ሰነዱ መረዳት ይቻላል፡፡በሁለቱም አመት (በአራቱ ወሰነ ትምህርት) ከተሰጡት ፈተናዎች ውስጥ በፈተናው መካተት የነበረባቸው ነገር ግን በንሞናነት ያልተመረጡና ተማሪዎችን ለመለካት የተረሱ ይዘቶች መስተአምር፣የህይዎት ታሪክ ፣ የቋንቋ አመጣጥና መላምት ወዘተ ምንም አይነት ትኩረት ያላገኙ የትምህርት ይዘቶች ናቸው፡፡ይህም በመሆኑ  ከቋንቋ ይዘት አካታችነት አንፃር ሲፈተሽ ውስንነት ያለበት ነው ማለት ይቻላል፡፡

### 4.1.2 ከፈተና እቅድ ሰንጠረዥ አንፃር የተገኙ መረጃዎች ትንተና

አንድ የቋንቋ ፈተና ሲዘጋጅ መለካት የተፈለገውን ችሎታ በትክክል ለመለካት የግድ ትክክለኛ የፈተና እቅድ ሰንጠረዥ ያስፈልጋል፡፡ይሁንና በጉራጌ ዞን በእዣ ወረዳ በየዋሽንየ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሁለቱም አመት(በአራቱም ወሰነ ትምህርት) ለዘጠነኛ ክፍል ከተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ  የማጠቃለያ ፈተናዎች ውስጥ ፈተናዎች የተዘጋጁበት ተገቢ የፈተና እቅድ ማግኘት አልተቻለም፡፡ የፈተና እቅድ ናቸው ተብሎ በሰነድነት የተቀመጡትንም ቢሆን ስንመለከት የፈተና እቅድ ዝግጅትን ሊመጥኑ የማይችሉ፣ ከተዘጋጁት ፈተናዎች  ይዘቶች ጋር ግንኙነት የሌላቸውና ሳይሱን ያልተከተሉ ናችው፡፡ የቀረቡት ጥያቄዎችና በፈተና እቅድ ውስጥ የቀረቡት ይዘቶች እኩል አይደሉም፡፡ የተዘጋጁት የቋንቋ ፈተናዎች መያዝ ካለባቸው የፈተና ትዕዛዞች አንፃርና ከተመደበላቸው ጊዜ አንፃር ሲፈተሽ ውስንነት ያለባቸው ናቸው፡፡ከዚሁ ጋር በተያያዘ  የቋንቋ ይዘቶች መቅረብ በሚገባቸው የፈተና አወቃቅር ተደራጅተው ፣ተሰልተው፣ጥቅማቸውን ከግምት ውስጥ

አስገብተው ሳይሆን በተለመደው የፈተና አወጣጥ ስልት እንደሆነ መረደት ተችሏል። በቀረቡት የፈተና እቅዶች የፈተናውን አላማ እና ፈተናዎቹ መለካት የፈለጉትን ልኬቶች በትክክል ያገናዘቡ አይደሉም።የትኛውም ጥያቄ በየትኛው ሂሳባዊ ቀመር ተሰልቶ እነደቀረበ የሚያሳይ ነገር የለም።እንዲሁም የተዘጋጁት ፈተናዎች ከየትኛው ይዘቶች እንደቀረቡ፣ የሚያሳይ የፈተና ይዘት ቢጋር የላቸውም ።በመሆኑም ሊለካ የተፈለገውን ነጥብ ለመተንበይ በተፈለገው አላማ ከየትኛው ይዘት ፣ምን አይነትና ፣ምን ያክል መጠን ጥያቄ መዘጋጀት እንዳለበት ታስቦ ሳይሆን እንደመምህራኑ ችሎታና ብቃት መማሪያ መፅሀፉንና ሌሎች ከስርዓተ ትምህርቱ ውጭ የሚገኙ አጋዥ መፅሃፍት በመጠቀም ፈተናዎች እደሚዘጋጁ ለመረዳት ተችሏል።

### 4.1.3 ከይዘት ተገቢነት አንፃር የተገኙ መረጃዎች ትንተና

በፈተናው የቀረቡት የቋንቋ ጥያቄዎች ይዘቶች በአብዛኛው ከአስተሳብ ተገቢነት (construct validity) አንጻር ሲመረመሩ ውስንነት ያለባቸው እንደሆኑ ከሰነዱ መረዳት እንችላለን። የቀረቡት ጥያቄዎች የተማሪዎችን ስብዕና ችሎታና ክህሎት፣የአስተሳብ አድማሳቸውን ለማስፋት ፣የባህሪ ለውጥ ለማምጣት ቋንቋውን በአግባቡ ለመጠቀም በሚያስችል ሁኔታ የቀረቡ ሳይሆኑ እንደሳይንስ ትምህርት በቀጥታ ደረቅ የሆኑ የቋንቋ ይዘቶች ለማስገንዘብ በሚያስችል መልኩ የተዘጋጁ ናቸው ማለት ይቻላል።በሁለቱም አመት(በአራቱ ወሰነ ትምህርት) የቀረቡት የቋንቋ ጥያቄዎች ከዚሁ መርህ አንፃር ስንፈትሸው ውስንነት ያላባቸው ናቸው።በ2013ዓ.ም በመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት ከቀረቡት የቋንቋ ጥያቄዎች ውስጥ ተራ ቁጥር 3፣8፣9፣እና 22 ተገቢነታቸው የወረደ ነው።በ2013ዓ.ም በሁለተኛው ወሰነ ትምህርት ከቀረቡት ጥያቄዎች መካከል ደግሞ ተራ ቁጥር 1፣3፣8፣30፣ እና 39 ውስንነት ያለባቸው ናቸው።

በ2014ዓ.ም በመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት ከቀረቡት ጥያቄዎች ተራ ቁር 1፣3፣8፣30 እና 39 ውስንነት ያለባቸው ሲሆን በ2014ዓ.ም በሁለተኛው ወሰነ ትምህርት ከቀረቡት ጥያቄዎች ውስጥ ተራ ቁጥር 3፣5፣10፣21፣ እና 28 ውስንነት ያለባቸው ጥያቄዎች ናቸው፡ ፡ከዚህ አንፃር በሁለቱም አመት (በአራቱም ወሰነ ትምህርት) ከቀረቡት የቋንቋ ጥያቄዎች በ2014ዓ.ም በመጀመሪያው ወሰነ ትምህርትና በ2014ዓ.ም በሁለተኛው ወሰነ ትምህርት የቀረቡት የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች የተሻለ የመለካት ሀይል ያላቸው ሲሆን በአንጻሩ

በ2013ዓ.ም በመጀመሪው ወሰነ ትምህርት እና በ2013ዓ.ም በሁለተኛው ወሰነ ትምህርት የቀረቡት የቋንቋ ትምህርት ዘቶች ውስንታቸው የጎላ ሆኖ ተገኝቷል፡፡በሌላ በኩል የቀረቡትን የቋንቋ ይዘቶች ከግልብ ትትክክለኛነት(face validity) አኳያ ሲመረመሩ የፈተናዎቹ አጠያየቅ የፈተናዎቹ ትዕዘዝ ተማሪዎቹን በትክክል ለመለካት የታሰበውን ባህሪ ፣እውቀትና ክህሎት ያለማወቅ ችግሮች ይስተዋላሉ፡፡እርማቶቹን ለማቃለል ሲባል ተመሳሳይ መልሶችን መሰየም፣ሁሉንም ምዕራፎችና የትምህርት ንዑሳን ይዘቶች መካከል ያደረጉ የይዘት ንሞና ምርጫዎች ችግር ያለባቸው ናቸው፡፡

**4.1.4 የቀረቡት የቋንቋ ጥያቄ ይዘቶች ካላቸው የቁብነት ደረጃ አንፃር የተደረገ ትንተና**

ከ2013 ዓ.ም እስከ 2014 ዓ.ም የቀረቡት የቋንቋ ጥያቄዎችና መመሪያዎች ከቁጥብነት አንጻር ብዙም የከፋ ችግር አልታየባቸውም፡፡ጥያቄዎቹ ሲዘጋጁ በተቻለ መጠን ከቃላት አጠቃቀም ከመማሪያ መፅሀፍ አቀራረፅ፣ከሚሸፍኑት የገፅ ብዛት ችግር እንዳይፈጠር ትምህርት ቤቱ ከሚሰጠው መመሪያና ግንዛቤ አኳያ ከሰነዱና ከመምህራን ከተገኘው ቃለ መጠየቅ መረዳት ተችሏል፡፡ ነገር ግን በጣም ጥያቄ ለማሳጠር ተብሎ ገለጭ ቃላትና ሀረጋትን በማስቀረት አንዳንዶቹ ጥያቄዎች ምንን ለመጠየቅ እንደሆነ የሚያዳግቱ አሉ፡፡ በ2013ዓ.ም በመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት ከቀረቡት ፈተናዎች ውስጥ ትዕዛዝ ሁለት ያለው መመሪያ ጊዜና ቦታን ለመቆጠብ ሲባል ብቻ ገላጭነቱ በጣም ችግር የሚስተዋልበት ነው፡፡ስርዓተ ነጥቦችንና የቃል ክፍሎች በአንድ ላይ ስለተቀላቀለ ግልፅ በሆነ መንገድ የቀረበ አይደለም፡፡በዚሁ ፈተና የቀረቡ ጥያቄዎች አጭርና ግልፅ ናቸው ቢባልም የተወሰኑ ጥያቄዎች ግን የቁጥብነት ችግር ይታይባቸዋል፡፡ጥያቄ ተራ ቁጥር 37 እና 39 የቁብነት ችግር ያለባቸው ናቸው፡፡

በ2013ዓ.ም በሁለተኛው ወሰነ ትምህርት አራት መመሪያዎች ያሉት ሲሆን ከቀረቡት መመሪዎች ውስጥ አራቱም መመሪያዎች አጭርና ግልፅ ናቸው፡፡እንዲሁም በዚሁ ወሰነ ትምህርት ከተሰጡት የቋንቋ ፈተናዎች ውስጥ ጥያቄ ቁጥር 8 እና 26 በተወሰነ መልኩ የቁጥብነት ችግር ያለባቸው ሲሆን ሌሎቹ ጥያቄዎች በተሻለ መልኩ መቅረባቸው ከፈተና ሰነዱ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡በሌላ በኩል ደግሞ በ2014 ዓ.ም በመጀመሪው ወሰነ ትምህርት የቋንቋ ትምህርት ይዘትን ለመለካት የቀረቡት ሁለት መመሪያዎች ብቻ ሲሆን ሁለቱም ያልተንዛዙ አጭርና ግልፅ ናቸው፡፡በተመሳሳይ መልኩ በነዚህ መመሪዎች ስር ተማሪዎችን

ለመለካት የቀረቡትን ይዘቶች ስንመለከት  ቁጥብነታቸው በአንፃራዊነት ተገቢነት ያላቸው ናቸው፡፡በ2014ዓ.ም በሁለተኛው ወሰነ ትምህርት የቀረቡትን እንዲሁ ስንመለከት አራት መመሪዎች ያሉት ሲሆን መመሪያ አንድ ሶስትና አራት አጭር፣ግልፅና ቁጥብ ሲሆኑ መመሪያ ሁለት የግልፀኝነት ችግር ይታይበታል፡፡በዚሁ ወሰነ ትምህርት ቋንቋን ለመለካት የቀረቡ ይዘቶችን ስንመለከት በአመዛኙ የቁጥብነት ችግር አልተስተዋለባቸውም፡፡በጥቅሉ በሁለቱም አመት( በአራቱም ወሰነ ትምህርት) ከቀረቡት የቋንቋ ጥያቄዎች ውስጥ ከፍተኛውን ቦታ የሚይዘው  የቁጥብነት ችግር ያልታየባቸው መሆኑ ከፈተናዎቹ ሰነድ ለማረጋገጥ ተሞክሯል፡፡

### 4.1.5. ከቋንቋ የትምህርት ይዘት ቅለትና ክብደት መረጃዎች ትንተና

የአንድን ፈተና የቅለትና ክብደት ብሎም የመለየት ሀይል የምንለካበት ሂሳባዊ ስሌት ቢኖረውም በዚህ ጥናት ለመተግር የጥያቄዎቹ መልስ ስለሌሉ ለመተግበር አልተቻለም፡፡ነገር ግን ከተማሪዎቹ ትምህርት ደረጃ ከመርሃ ትምህርቱና ከመማሪ መፅሀፉ የይዘት አቀራረብን መሰርት ተደርጎ የፈተናዎቹን የቅለትና ክብደት ደረጃ ማብራራት ይቻላል፡፡በአራቱም ወሰነ ትምህርት የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ለመለካት የቀረቡት ፈተናዎች ከባድ የምንላቸው አይደሉም፡፡በአንፃሩም ሁሉም ቀላል ናቸው ለማለት ግን አያስደፍርም፡፡የተሰጡትን ጥያቄዎች በዝርዝር ስንመለከት የተማሪዎቹን የብስለት ደረጃ የሚመጥኑ አይደሉም፡፡ይዘቶቹ ከሰባተኛ ክፍል ጀምረው የሚታወቁ ሆነው ለዘጠነኛ ክፍል በፈተና መልክ ሲቀርቡ በተመሳሳይ መልክና ቅርፅ መጠናቸውን ሳይቀይሩ ለፈተና ከቀረቡ ይዘቶች ይስተዋላሉ፡፡ በ2013 ዓ.ም የመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት ከቀረቡት ፈተናዎች ውስጥ ጥያቄ ቁጥር 22 በየትኛውም አጋጣታሚና ሁኔታ ማስታወሻ መያዝ ስንፈልግ ምን ምን ማዘጋጀት አለብን? ሀ. ወንበርና ደብተር  ለ. ቦርሳና ደብተር  ሐ ብዕርና ቦርሳ  መ. ወረቀትና ብዕር፡፡ ይህ ይዘት በዝቅተኛ ክፍል ደረጃም ማስታወሻ ለመያዝ ምን ምን እንደሚስፈልግ በግልፅ ይታወቃል፡፡ ጥያቄ ተራ ቁጥር 24 ያላለቀ ሀሳብ መኖሩን የምናመለክትበት ስርዓተ ነጥብ የቱ ነው? የሚል ሲሆን ሀ. ቅንፍ  ለ. ህዝባር  ሐ. ትምህርት ጥቅስ  መ. ነጠብጣብ፡፡ ይህ ጥያቄ ስለስርዓተ ነጥብ በይዘት ደረጃ የሚካተተት ቢሆንም በአቀራብ ደረጃ ግን ለዘጠነኛ ክፍል ሚመጥን አይደለም፡፡ ጥያቄ ቁጥር 26 የቤተ መፅሀፍት ዋና ዋና ደንቦችና ስርዓቶችን መጠበቅ በተመለከተ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው? ሀ.ፀጥታን መጠበቅ  ለ. የግል መፅሀፍትን ይዞ አለመግባት  ሐ. መፅሀፍትን በተገቢው ሁኔታ አለመጠቀም መ› ነጠላ

ጫማ ለብሶ አለመግባት።ስለቤተ መፅሀፍት ሲነሳ ምን መደረግ እንደላበትና እንደሌለበት ከዝቅተኛ ክፍል ደረጃ ጀምሮ በግልፅ የሚታወቅ ጉይዳ ነው። ስለሆነም ይህ ጥያቄ ለዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ከአቅም በታች እንደሆነ መረዳት ይቻላል።ጥያቄ ተራ ቁጥር 33 እና 35 በተመሳሳይ መልኩ ለክፍል ደረጃው የማይመጥኑ በጣም ቃላል ጥያቄዎችና ተማሪዎችን በትክክል የማይለኩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል። በ2013ዓ.ም በሁለተኛው ወሰነ ትምህርት የቀረቡትን የቋንቋ ጥያቄዎችን ስንመለከት ደግሞ ጥያቄ ተራ ቁጥር 25 የአንድን ነገር አሰራር የሚያብራራ የድርሰት አይነት ------ይባላል።ሀ.ስዕላዊ ድርሰት ለ.አመዛዛኝ ድርሰት ሐ. ተራኪ ድረስት መ. ገላጭ ድርሰት። ስለ ድርሰት ምንነትና የድርሰት አይነቶች ይዘቱ አስፈላጊ መሆኑ ቢታወቅም ከጥቄው አወቃቅር አንፃር ሲታይ ግን ለዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የሚመጥን አይደለም።ጥያቄ ቁጥር 32 ልጁ ልብሱን በእናቱ----።ከባዶ ቦታው መግባት ያለበት ግስ የቱ ነው።ሀ. ታጠበ ለ. አጣጠበ ሐ.አጠበ መ. አሳጠበ።ይህ ጥያቄ ለዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ካላቸው ልምድና የክፍል ደረጃ የብስለት ደረጃ አንፃር አይመጥንም።ጥያቄ ተራ ቁጥር 34 እና 35 በተመሳሳይ ለዘጠነኛ ክፍል ደረጃ ተማሪዎች የማይመጥኑ መሆኑ ለማረጋገጥ ተችሏል።

በ2014 ዓ.ም የመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት የቀረቡትን ጥያቄዎች ስንለከት በእውነት ሀሰትና በምርጫ መልክ የቀረቡት ጥያቄዎች ከተማሪዎች ትምህርት ደረጃ አንጻር ሊመጥኑ የማችሉ በጣም ቀላል የሚባሉ ናቸው።ጥያቄ ተራ ቁጥር 1፣3፣7፣8፣9፣24፣25፣27፣30፣34 እና 39 ለዘጠነኛ የክፍል ደረጃ የማጠቃለያ ፈተና የሚመጥኑ አይደሉም።በ2014ዓ.ም በሁለተኛው ወሰነ ትምህርት የቀረቡትን ጥቄዎች ስንመለከት ደግሞ ከሁሉም በበለጠ መልኩ በአዛምድ መልክ የቀረቡት ጥያቄዎች በጣም ከደረጃ በታች ዝቅ ያሉ መሆናውን ከሰነዱ ማረጋገጥ ተችሏል።ለማሳያ ያክል ብንወስድ ከጥያቄ ተራ ቁጥር 11 እስከ 20 ያሉ የአዛምድ ጥያቄዎችን ማየት በቂ ነው።በጥቅሉ በሁለቱም አመት (በአራቱም ወሰነ ትምህርት) ከተሰጡት የቋንቋ ፈተናዎች አብዛኛዎቹ ጥያቄዎች በጣም ቀላል እንደሆኑ መረጃዎች ያሳያሉ።

**4.1.6. ከቋንቋ የይዘት አውዳዊነት በተመለከተ የተገኙ መረጃዎች ትንተና**

የቋንቋ ጥያቄዎች በአውድ እንዲቀርቡ ምሁራን ቢመክሩም በአራቱም ወሰነ ትምህርት የቀረቡትን ጥያቄዎች በምንመለከትብት ጊዜ በቀጥታ ከቋንቋ ስርዓት(መዋቅር) ጋር በሚገናኝ

መልኩ የተዘጋጁት ጥያቄዎች ይበዛሉ።በእውነት ሀሰት፣በአዛምድና በምርጫ የቀረቡት የቋንቋ ጥያቄዎች አውዳዊነት የጎደላቸው ናቸው።በሁቱም አመት (በአራቱም ወሰነ ትምህርት) ከቀረቡት ጥያቄዎች የተወሰኑ አስረጅዎችን ወስደን ስንመለከት በ2013ዓ.ም የመጀመሪው ወሰነ ትምህርት ከወጡት ጥያቄዎች ውስጥ ጥያቄ ተራ ቁጥር 8 ውውይይት በአጋጣሚ የተፈጠረ ክንውን ነው የሚል ሲሆን ይህ ጥያቄ ደረቅ የቋንቋ እውቀትን ለማስገንዘብ እንጅ የቋንቋ ተግባቦትን ለመፍጠር በሚያስችል መልኩ የቀረበ አይደለም።ጥያቄ ተራ ቁር 25 ግራና ቀኝ መሪ ያለው የሀረግ አይነት የቱ ነው።ሀ ስማዊ ለ. ግሳዊ ሐ. መስተዋድዳዊ መ. ተውሳከ ግሳዊ።ይህ ጥያቄ አወደድን ያገናዘበ አይደለም። ቢሆን የሚመረጠው ሀረጉን አዋቅሮ ቀኝ መሪና ግራ መሪ ያለበትን ሀረግ እንዲለዩ ማድረግ የተሻለ ይሆን ነበር።ሌሎቹ አብዛኛዎቹ ጥያቄዎች በዚሁ አግባብ የሚታዩ ናቸው።

በ2013 ዓ.ም በሁለተኛው ወሰነ ትምህርት ከተዘጋጁት የቋንቋ ፈተናዎች መካከል አብዛኞቹ ጥያቄዎች የአውዳዊነት ጉድለት ያለባቸው ናቸው።ለምሳሌ ብንመለከት ጥያቄ ተራ ቁጥር 9 የአንድን ቅኔ ግልፁንና ድብቁን መልዕክት በአንድ ላይ የሚይዘው ቃል ሰም ይባላል የሚል ሲሆን ይህ ጥያቄ በአውድ መልክ የቀረበ ሳሆይን በቀጥታ የቋንቋውን አወቃቅርና ስርዓት ለማስገንዘብ የተዘጋጀ ደረቅ ጥያቄ ነው።ጥያቄ ተራ ቁጥር 25 አንድን ነገር አሰራር የሚያብራራ የድርሰት አይነት-----ይባላል።ሀ. ስዕላዊ ድርሰት ለ.አመዛዛኝ ድርሰት ሐ.ተራኪ ድርሰት መ.ገላች ድርሰት።ይህ የቋንቋ ጥያቄ በአቀራረቡ ከላይ በተገለፀው አኳኋን ነው። የድርሰት አይነትን ለማሳየት ድርሰት በማዋቀር ከየትኛው የድርሰት አይነት እንደሚመደብ ቢገለፅ የተሻለ ነበር። በ2014 ዓ.ም በመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት ከቀረቡት የቋንቋ ጥያቄዎች መካከል አብዛኛዎቹ አውድን መሰረት ያደረጉ አይደሉም።ለምሳሌ ያክል ጥያቄ ተራ ቁጥር 34 የተለያዩ ተቃራኒ ሀሳቦችን ለማያያዝ የሚያገለግሉ አያያዥ የትኛው ነው? ሀ.ቢሆነም ለ.ስለሆነም ሐ.ስለዚህ መ. በመሆኑም።ይህ ጥያቄ በአውድ የተዋቀረ አይደለም።ቢሆን የተሻለ የሚሆነው የተለያዩ ተቃራኒ ሀሳቦችን በመስጠት አያያዞችን ተጠቅመው እንዲዋቅሩና እንዲያያዙ ቢደረግ ይመረጣል።በመጨረሻም በ2014 ዓ.ም በሁለተኛው ወሰነ ትምህርት ከቀረቡት የቋንቋ ጥያቄዎች መካከል አብዛኛዎቹ አውድን መሰርት ያደረጉ አይደሉም። ለማሳያ ያክልም ጥያቄ ተራ ቁጥር 5 ደብዳቤ በዋናነት በአራት ይከፈላል የሚል ሲሆን ይህ ጥያቄ አውድን መሰርት ያደረገ ሳይሆን በሽምደዳ ላይ ያተኮረ ነው።ጥቄ ተራ ቁጥር 25 ቃላትን አሳጥሮ ለመፃፍ የገለግል ስርዓተ ነትብ የቱ ነው። ሀ.

ሁለት ነትብ ለ. ይዘት ሐ. አመጫት መ.ንዑስ ጭረት።ይህ ጥያቄም ልክ ከላይ እንዳየናቸው ሁሉ በሽምደዳ ላይ የተመሰረተ እንጂ በአውድ የተዋቀረ አይደለም።ሌሎች መሰል ጥያቄዎችም በዚህ መልክ የተዋቀሩ በርካታ ናቸው።በጥቅሉ በሁለቱም አመት (በአራቱ ወሰነ ትምህርት) የተዘጋጁትን የቋንቋ ፈተናዎች ከዚህ መርህ አንፃር ሲታዩ አውድን መሰርት አድርገው የተዘጋጁ አለመሆናቸውን ከፈተናዎቹ ሰነዶች መረዳት የተቻለ ሲሆን በከፊልም ቢሆን አገባብን ወይም አውድን ተከትለው የቀረቡ የቋንቋ ጥያቄዎች እንዳሉ መረጃዎቹ ይጠቁማሉ።የቋንቋ ፈተናዎች ሲዘጋጁ እንደ ትልቅ ችግር ሆኖ የሚታየውና አሁንም ለመቅረፍ ያልተቻለው ጥያቄዎችን በአውድ አለማዘጋጀት እንደሆነ ከሰነዱ መረዳት ይቻላል።

### 4.1.7. ከቋንቋ ጥያቄዎች የየይዘት አወቃቀር ( አደረጃጀት) አንፃር የተገኙ መረጃዎች ትንተና

በሁለቱም አመት (በአራቱም ወሰነ ትምህርት) የቀረቡትን የቋንቋ ጥያቄዎች የይዘት አደረጃቶች ስንመለከት አፍላቂነት የሌላቸውና ውስንነት ያባለቸው ናቸው።ጥያቄዎቹ የቀረቡበትን ሁኔታ ከድርሳኖቹ መረዳ እንደሚቻለው አንዳንዶቹ ከቀላል ወደ ከባድ ሲደራጁ ሌሎቹ ድግሞ ከቀላል ወደ ከባድ፣አንዳንዶቹ ደሞግ በተቀላለቀለ መንገድ የቀረቡ እንደሆነ ከቀረቡት የቋንቋ ጥያቄዎች መረዳት ተችሏል።ከዚህ አንፃር በ2013ዓ.ም በመጀመሪው ወሰነ ትምህርት የቀረቡት የቋንቋ ጥያቄዎች ከአደረጃጀት አንጻር የተሻለ ሲሆኑ በ2013ዓ.ም የሁለተኛው ወሰነ ትምህርት በ2014ዓም የመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት እና በ2014ዓ.ም በ2ኛው ወሰነ ትምህርት ግን ውስነነት ያባቸው መሆናቸውን ለመረዳት ተችሏል። እነዚህ ጥያቄዎች አጀማመራቸው ላይ ከቀላል ወደ ከባድ ከሚታወቅ ወደ ማይታወቅ፣የቀረቡ ቢመስሉም በምርጫ የቀረቡትን ጥያቄዎች ስንምለከት ግን የተደበላለቁና ሳይንሳዊ አሰላፍን መሰረት ያላደረጉ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል። በሌላ በኩል የቀረቡት የቋንቋ ጥያቄዎች ተደጋጋሚነት ይስተዋልባቸዋል።በተለይምልቦለድ ፣የሀረግ አነቶች፣ድራማ(ተውኔት)፣ስርዓተ ነተጥቦች፣የቃል ክፍሎች ላይ ትኩረት ያደረጉ ናቸው።

ከዚህ አኳያ የቀረቡት የቋንቋ ጥያቄዎች የተደራጁበት ሁኔታ ውስንነት እንዳሉባቸው የሚያሳዩ ናቸው።በመሰረታዊነት የተዘጋጁት ጥያቄዎች ውጤት ተኮር የቋንቋ ይዘት አቀራርብ በሚባል መንገድ የተቀረፁ ናቸው።ይህም ማላት ተማሪዎቹ የቋንቋ አሀዶችን ነጥለው በመተንተን በቋንቋ ዝርዝር ህግ ላይ ተመስርተው ጥያቄዎችን እንዲለዩ የሚያስችሉ

ናቸው፡፡ይሁን እንጂ ያቀራረብ ስለቱ ልማዳዊ የሆነ የቋንቋ ፈተና ጥያቄዎች የአቀራርብ መርህን የተከተሉ፣የቋንቋ መዋቅራዊ ህግጋትና ብያኔዎች ላይ ያተኩሩ ሲሆን በዘዴ የሚቀርበው የቋንቋ ትምህርት አላማ ተግባቦት ላይ የተመሰረተ ሳይሆን ተማሪዎች ቋንቋውን ቃል በቃል ከፋፍለው እንዲለዩ ፣ቃላትን፣ሀረጋትንና አረፍተ ነገሮችን በተናጥል እንዲተነትኑና እንዲመሰርቱ የሚያደርጉ እንጂ እነዚህን ቅረፆች ከተግባቦት ጋር በማቀናጀት እንዲለማመደዋቸውና በቋንቋው ላይ ያላቸውን ትልቅ እውቀትና ክህሎት ለመለካት የሚያስችል አለመሆናቸውን ከሰነዱ ለመረዳት ተችሏል፡፡ የተማሪዎችን ቋንቋ ይበልጥ እንዲጎለብት ማላትም በአውድ ውስጥ ትርጉም ሰጭ የሀሳብ ልውውጥ በማድረግ የቋንቋውን ቅርፆች ከማወቅ ባለፈ ይበልጥ ለተግባቦት እንዲጠቀሙባቸው የሚያስችሉ የቋንቋ ጥያቄዎች የይዘት አቀራረብ አለመከተላቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡ከዚህ የምንረዳቸው ስልቱ ተማሪዎቹ በራሳቸው አውዶች ማላትም ከራሳቸው ገጠመኝ፣ዳራዊ እውቀት በመነሳት የቋንቋ ህግጋትን በራሳቸው ጥርት እንዲገነዘቧቸውና ከሽምደዳ በወጣ ፅንሰ ሀሳባዊ እይታዎች እንዲለያዩ በሚያስችል ሁኔታ ተደራጅተው እንዳልቀረቡ መረዳት ተችሏል፡፡

#### 4.1.8 የጥያቄዎቹን ማዕከላዊ ሀሳብ በግንዱ ላይ ከማቅረብ አንጻር የተገኙ መረጃዎች ትንተና

በሁለቱም አመት(በአራቱም ወሰነ ትምህርት)የቀረቡትን የቋንቋ ጥያቄዎች የይዘት ተገቢነት ሁኔታ ለመቃኘት ሲሞከር የጥያቄዎቹ ሀሳብ ከጥያቄው አልፎ ወደ አማራጮች በመግባት ተፈታኞችን ለማደናገር የሚሞክሩ የተወሰኑ ናቸው፡፡የተወሰኑ ጥያቄዎች ተፈታኞች መአከላዊ ሀሳቦች የሚረዱት ከራሱ ከጥያቄው ሳይሆን ከተሰጡት ምርጫዎች ነው፡፡ይህ መሆኑ ደግሞ የፈተና አግባብነት ችግር ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ከ2013ዓ.ም እስከ 2014ዓ.ም ከቀረቡት የቋንቋ ጥያቄዎች መካከል አብዛኞቹ ይህንን መስፈርት በአግባቡ የሚያሟሉ ሲሆኑ የተወሰኑት ጥያቄዎች ከዚህ መርህ ውጭ ናቸው፡፡ የተወሰኑ ማስረጃዎችን ወስደን ስንመለከት በ2013ዓ.ም በመጀመሪው ወሰነ ትምህርት ከተዘጋጁ የቋንቋ ጥያቄዎች መካከል መስፈርቱን ያላሟሉትን ለይተን ስንመለከት ጥያቄ ተራ ቁጥር 32 የስነ-ፅሁፍ ምንጩም ተቀባዩም ሰው ነው፡፡ የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍቺ የቱ ነው ?ሀ. መገኛ ለ. ችሎታው ሐ.ወሳጁ መ.አንባቢው፡፡በዚህ ጥያቄ ስር ሊጠየቅ የታሰበውን መአከላዊ ሃሳብ መረዳት

የሚቻለው ከጥያቄው ሳይሆን ከአማራጮቹ ነው፡፡የ2013ዓ.ም በሁለተኛው ወሰነ ትምህርት ከቀረቡት ጥያቄዎች መካከል ጥያቄ ቁጥር 21 እና 30 ተመሳሳይ ችግር የሚስተዋልባቸው ናቸው፡፡እንዲሁም በ2014ዓ.ም በመጀመሪው ወሰነ ትምህርት ከቀረቡት ጥያቄዎች መካካል ጥያቄ ተራ ቁጥር 13 እና 18 ከዚሁ ችግር ያልወጡ ናቸው፡፡በተመሳሳይ በ2014ዓ.ም በሁለተኛው ወሰነ ትምህርት የቀረቡትን ጥያቄዎች ስንመለከት ጥያቄ ቁጥር 23 እና 28 ከዚህ የፈተና መስፈር አንፃር ውስንት ያባቸው መሆኑን የፈተናዎቹ ሰነድ ያሳያል፡፡

**4.1.9. የቋንቋ ጥያቄዎች የይዘት ተገቢነት በነጠላ ሃሳብ ከመሆን አንፃር የተገኙ መረጃዎች ትንተና**

በሁለቱም አመት (በአራቱም ወሰነ ትምህርት) የተዘጋጁትን ፈተናዎች ስንመለከት ከተወሰኑ ጥያቄዎች በስተቀር አብዛኛዎቹ ጥያቄዎች መስፈርቱን ያሟሉ ናቸው፡፡በ2013ኣ.ም በመጀመሪው ወሰነ ትምህርት ከተዘጋጁት የቋንቋ ፈተናዎች መካከል አራት የሚሆኑት ጥያቄዎች ችግር ያሉባቸው ሲሆን በ2013ዓ.ም በሁለተኛው ወሰነ ትምህርት ከተዘጋጁት ጥያቄዎች መካከል አንድ ጥያቄ መስፈርቱን ያሟላ አይደለም፡፡ በ2014ዓ.ም በመጀመሪው ወሰነ ትምህርት አራት ጥያቄዎች ከዚህ ችግር ያልተላቀቁ ሲሆን በ2014ዓ.ም በሁለተኛው ወሰነ ትምህርት ከተዘጋጁት የቋንቋ ጥያቄዎች ከዚህ መስፈርት አንጻር የተሻሉ እንደሆኑ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡የዚህ አይነት ችግር ያለባቸውን የቋንቋ ጥያቄዎች የተወሰኑ ማሳያ ወስድን ስንመለከት በ2013ዓ.ም የመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት ከቀረቡት ጥያቄዎች መካካል ጥያቄ ቁጥር 5 ምዕላድ የምንለው ትርጉም አዘል የሆነና አነስተኛ ወደ ሆነ ትርጉም አዘል ክፍሎች ሊሸነሸን የሚችል የመጨረሻ ንዕስ አሀድ ነው፡፡ ጥያቄ ተራ ቁጥር 7 ቤተ መፅሀፍት ውስጥ የምንፈልገውን መረጃ ለማግኘት በቅድሚ የቤተመፅሀፍት ስነ-ስርዓትና የመፅሀፍት አፈላለግን ማወቅ ይጠበቅብናል፡፡ጥያቄ ቁጥር 6 በግጥም ቅርፅ የቀረበውን ፅሁፍና በዝርው ቅርፅ የቀረበውን ፅሁፍ ስናነብ የምንከተለው ስልት የተለያየ ነው፡፡ በ2013ዓ.ም በሁለተኛው ወሰነ ትምህርት ከቀረቡት ውስጥ ሁለት ሀሳብ ያለው ጥያቄ ስንመለከት ተራ ቁጥር 3 በቃል ወይም በፅሁፍ ፣በዝርው ወይም በግጥም የሚነገር ወይም የሚፃፍ ድርሰት ቅኔ ይባላል፡፡በ2014ዓ.ም በመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት ከቀረቡት የቋንቋ ጥያቄዎች መካከል የዚህ አይነት ችግር ያለባቸውን ስንመለከት ተራ ቁጥር 5፣9፣13 ለአብነት ያክል ይጠቀሳሉ፡፡በጥቅሉ የ2013ዓ.ም የመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት የቀረቡትን ጥያቄዎች ስንመለከት ጥያቄ ቁጥር 5 ትርጉም አዘል የሆነና የመጨረሻ ንዑስ አሃድ የሆነ፣ጥያቄ ቁጥር 7፣የቤተመፅፍ አጠቃቀምና የመፅሀፍ አፈላለግን የሚገልፁ ሁለት ሁለት

ሀሳቦችን የያዙ ጥያቄዎች ናቸው፡፡በ2013ዓ.ም በሁለተኛው ወሰነ ትምህርት ያለውን ስነፈትሽ ደግሞ በቃል ወይም በፅሁፍ የሚለውና በዝርውና በግጥም በሚል አገላለፅ ቀርቧል፡፡ በመጨረሻም በ2014ዓ.ም በመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት የቀረቡትን ስንመለከት ጥያቄ ቁጥር 5 የቃላት ፍካሬያዊና ፈሊጣዊ ፍቺዎች ፣ጥያቄ ቁጥር 13፣ቋንቋ መልክት መቀበያና ማስተላለፊያ እና የቋንቋ ትንሹ አሀድ የሚሉ የተለያዩ ሁለትና ከዚያ በላይ ሀሳብ ያዘሉ የቋንቋ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ስለሆነም በአንድ ቃል ነጠላ ሀሳብ የያዘ የቋንቋ ጥያቄ መቅረብ አለበት የሚለውን መርህ የጣሱ መሆናቸው ውስንነት እንዳላቸው የሳያል፡፡

### 4.1.10. የቀረቡት የቋንቋ ይዘቶች ከአሳሳች ተገቢነት አኳያ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

በሁለቱም አመት በአራቱም ወሰነ ትምህርት የቀረቡትን የቋንቋ ጥያቄዎች የይዘት አቀራረብ ከአሳሳች አንጻር ስንመለከት በበብዙዎቹ የተሸለ ነገር ቢታይም ከችግሩ ነፃ ናቸው ማላት ግን አይቻልም፡፡የአሳሳቾቹ አደረጃጀት ከተመሳሳይ (ቅርበት )ካላቸው የቋንቋ ይዘቶች መመረጥ እንዳለባቸው ምርጫዎቹ በቅርፅና በመጠን ተቀራራቢ እንዲሆኑ ቢመከረም ከዚህ ተፅዕኖ እንዳልወጡ ከፈተናዎቹ ሰነድ መረዳት ይቻላል፡፡ሁሉም መልስ ናቸው በሚልና መልስ የለም በሚል የታጠሩ የቋንቋ  ጥያቄዎች ይስተዋላሉ፡፡በ2013ዓ.ም በመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት ከቀረቡት የቋንቋ ጥያቄዎች ለአብት ወስደን ብንመለከት ጥያቄ ቁጥር 29 ከሚከተሉት አንዱ የቃል ክፍል አይደለም፡፡ ሀ. ግስ  ለ.ቅፅል ሐ.መስተዋድድ  መ. ቅኔ፡፡ ጥያቄው የቃል ክፍልብሎ ምርጫ መ ግን ቅኔ የሚለው ከጥያቄው ጋር የማይቀራረብ አሳሳችነት የጎደለው ነው፡፡በ2013ዓም በሁለተኛው ወሰነ ትምህርት ከቀረቡት የቋቋ ጥያቄዎች ውስጥ ደግሞ ጥያቄ ቁጥር 34 ከሚከተሉት አንዱ የሀትመት የመገነኛ ብዙሀን ነው፡፡ ሀ.ሬዲዎለ.ቴሌቪዥን ሐ. መፅሄት መ ሁሉም የሚሉ ናቸው፡፡በዚህ ጥያቄ አማራጭ መ አሳሳች ሊባል አይችልም፡፡በተመሳሳይ መልኩ ከምርጫ ሐ በስተቀር ሌሎቹ አማራጮች ከተሰጠውጥያቄ አንፃር በጣም ደካማ የአሳሳችነት ባህሪ ያላቸው ናቸው፡፡ጥያቄ ቁጥር 37 መነመነ ለሚለው ቃል በሀሳባ የሚዛመደው የትኛው ነው፡፡ሀ ከሳ ለ.አነሰ ሐ.  ቀነሰ መ.ሁሉም፡፡በዚህ ጥያቄ ከቀረቡት አመራጮች አማራጭ መ አሳሳች ሊሆን አይችልም፡፡ በ2014ዓ.ም በመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት ከተዘጋጁት የቋንቋ ጥያቄዎች ውስጥ ከአሳሳችነት አንፃር ጥያቄ ቁጥር 15 ስነ-ቃል ከሌሎች የስነ ፅሁፍ ዘርፎች የሚለይበት መሰረታዊ ባህሪ ሀ. ተለዋዋጭ  መሆን  ለ. አውዳዊ መሆኑ ሐ.ደረሲ አልባ መሆን መ.ሁሉም፡፡ በዚህ ጥያቄ ምርጫ መ አሁንም ትክክለኛ አሳሳች የሆነ አይደለም፡፡እንዲሁም

ጥያቂ ቁጥር 23 --------አንድ ቃል በመዝገበ ቃላት ከሚሰጠው ፍች ባሻገር ያለው ፊች ሊሆን ይችላል፡፡ ሀ. ፍካሬ ለ. እማሬ ሐ. ቅኔ መ. ምሳሌ፡፡በዚህ ጥያቂ ከተሰጡት አመራጮች አማራጭ ሐ እና መ አሳሰሳች ሊሆኑ አይችሉም፡፡እንዲሁም በ2014ዓ.ም የሁለተኛው ወሰነ ትምህርት ከተዘጋጁት የቋንቋ ጥያቄዎች ጥያቂ ቁጥር 21 ፣26.27፣29፣ 33 እና 35 የአሳሳችነት ውስንነት ያለባቸውና ሁሉም መልስ ናቸው መልስ የለም የሚሉ አማራጮችን ያካተቱ ናቸው፡፡

**4.1.11.የተዘጋጁት የቋንቋ ፈተናዎች የይዘት ተገቢነት ካላስፈላጊ ጥቆማ የወጡ ጥያቄዎችን መፈተሽ**

በሁለቱም አመት (በአራቱም ወሰነ ትምህርት) ከተዘጋጁት የቋንቋ ጥያቄዎች የተወሰኑት ብቻ ተማሪዎች ቀድመው መልሳቸውን እንዲለዩ የሚያደርጉ ሲሆን አብዛኞቹ ጥያቄዎች ግን ከዚህ መርህ ችግር ውጭ እንደሆኑ ሰነዶቹ ያሳያሉ ፡፡ከዚህ መስፈርት አንፃር ሲቃኙ ችግሮቹ በተለያየ መልክ የሚገለፁ ናቸው፡፡በተለይ ደግሞ ተመሳሳይ መልሶች፣ሁሉም መልስ ናቸው፣መልስ የለምና በቅርፅ ተመሳሳይ መልስ የያዙ ፊደሎችን በማድረግ ተማሪዎች መልሱን በቀላሉ በግምት ብጥልቀት ሳይመረምሩ እንዲያገኙ የሚያደርጉ ሁኔታዎች ይስተዋላሉ፡፡አላስፈላጊ ጥቆማ ከታየባቸው ለማሳያ ወስደን ብናይ በ2013ዓ፣ም በመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት ከቀረቡት ጥያቄዎች ውስጥ ጥያቂ ተራ ቁጥረ 27 እና 39 መጥቀስ ይቻላል፡፡በተመሳሳይ ሁኔታ ስንመለከት በ2013ዓ.ም በሁለተኛው ወሰነ ትምህርት ከተዘጋጁት ውሰጥ ጥያቂ ቁጥር 2 ፣27፣34፣እና 37 አላስፈላጊ ጥቆማ የሚያመላክቱ ናቸው እንዲሁም በ2014ዓ.ም በአንደኛው ወሰነ ትምህርት ከተዘጋጁት ጥያቄዎች መካከል ጥያቂ ቁጥር 19፣22፣ እና 37 ውስንነት ያለባው ናቸው፡፡እንዲሁም በ2014ዓ.ም በሁለተኛው ወሰነ ትምህርት ከቀረቡት ጥያቄዎች መካከል ደግሞ ጥያቂ ቁጥር 3፣28 እና 30 ውንነት የታየባቸው እንደሆኑ ከሰነዱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

አራተኛው የዚህ ጥናት መሰረታዊ ጥያቂ የተዘጋጀው የማጠቃለያ ፈተና ከፈተና የይዘት ተገቢነት መርሆዎች አኳያ ምን ይመስላል?የሚል ሲሆን የፈተናዎቹን ጠንካራ እና ደካማ ጎን ከፈተና ሰነዱና ከቃለ መጠይቁ የተገኘውን መረጃ በቅደም ተከተል በሚከተለው መልክ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ከ2013ዓ.ም እስከ 2014ዓ.ም በሁለቱም አመት (በአራቱ ወሰነ ትምህርት) በጉራጌ ዞን በእዣ ወረዳ በየሽንየ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተዘጋጅተው የቀረቡት የቋንቋ ማጠቃለያ ፈተናዎች ከፈተና መርሆዎች አንፃር ሲፈተሽ የራሱ የሆኑ

ጠንካራ ጎኖች አሉት፡፡በአራቱም ወሰነ ትምህርት ከቀረቡት ጥያቄዎች ካላቸው የቁጥብነት ደረጃ አንፃር አብዛኛው በሚባል መልኩ የተሸለ ተግብራት የታየባቸው ሲሆን የጥያቄዎቹን መአከላዊ ሀሳብ በግንዱ ላይ ከማቅረብ አንፃር የተገኙ መረጃዎችም ከሞላ ጎደል በጥንካራ የታዩ ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የቋንቋ ጥያቄዎች የይዘት አቀራረብ ነጠላ ሀሳብ ከመሆን አንፃር የተገኙ መረጃዎችና የቀረቡ ይዘቶች ከአሳሳች ተገቢነት አኳያ የተገኑት መረጃዎች በጠንካራ ጎናቸው የተሻሉ እንደሆኑ በተዘጋጁት ፈተናዎች የሰነድ ፍተሻ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በሁለቱም አመት( በአራም ወሰነ ትምርት) የቀረቡትን ፈተናዎች ከፈተና መስፈርቶች አንፃር ሲገመገም ከጥንካሪያቸው በላይ ውስንነቶች የበዙበት እንደሆነ በስነድ ፍትሻና በተደረገው ቃለ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አማካኝነት በተገኘው ውጤት ለማወቅ ተችሏል፡፡ በመሰረታዊነት በሁለቱም አመት (በአራቱም ወሰነ ትምህርት) ተዘጋጅተው የቀረቡት ፈተናዎች ሁሉንም ይዘቶች  በትክክል ሊወክሉ የሚችሉ የይዘት አካታችነት ወይም የንሞና አመራረጥ አግባብነታቸው ሲታይ ውስንት ያባቸው እንደሆኑ ለማረጋገጥ ተሞክሯል፡፡ ከዚህ አንፃር ለስነ-ፅሁፍና ለሰዋስው የበለጠ ትኩረት በመስጠት ለሌሎች ይዘቶች የተሰጡት ትኩረት ፍትሃዊ እንዳልሆነ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡በሳይንስ ከተቀመጠው መርህ በላይ የተካተቱ ይዘቶች እንዳሉ ሁሉ ከዚያ ባነሰ መልኩ የተካተቱት ደግሞ በርካታ ናቸው፡፡

ሌላው ከሰነድ መረጃውና ከቃለ መጠይቁ መረዳት የሚቻለው ፈተናዎች ሲዘጋጁ የፈተና እቅድ ሰንጠረዥ በተገቢው ሂሳባዊ ስሌት ባለመሆኑ በቋንቋ ይዘቶች ስር ለሚገኙ ንዑሳን ይዘቶች ተመጣጣኝ ሽፋን አለመሰጠቱ የጥናቱ ግኝት ያሳያል፡፡የፈተና እቅድ የተዘጋጀላቸውም ቢሆን የተዘጋጁትን ፈተናዎች ሊወክሉ የማችሉ መሆናቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡በሌላ መልኩ በነዚህ ፈተናዎች የታየው ድክመት በተዘጋጁት ፈተናዎች ሁሉንም ችሎታዎች በተቀራራቢ መልኩ ለመለካት አልተሞከረም፡፡የተጋጁት የቋንቋ ጥያቄዎች የቋንቋውን ህግጋት ወይም ስርዓትን ለማስገንዘብ የሚረዱ እንጂ ሌሎች የክህሎትና የአስተሳብ ፣የቋንቋ ተግባቦት ችሎታዎችን በአግባቡ ለመለካት የተዘጋጁ አለመሆናቸውን ከጥናቱ ውጤት ለመረዳት ተችሏል፡፡በሌላ መልኩ በፈተና የቀረቡ ይዘቶች ተገቢነታቸው ሲፈተሽ ያውዳዊነት ፣ከአቀራረብ ቅለትና ክብደት አንፃር አግባብነታቸው ሲታይ መሰረታዊ ችግር ያለባቸው እንደሆኑ ለመገንዘብ ተሞክሯል፡፡

## 4.2 የጥናቱ የውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ትኩረት በጉራጌ ዞን በእዣ ወረዳ በየሽንየ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ከ2013-2014 ዓ.ም ለዘጠነኛ ክፍል በተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ ማጠቃለያ ፈተናዎች የይዘት ተገቢነት መግምገም ሲሆን ጥናቱን እውን ለማድረግ በጥናቱ የተነሱ አላማዎችን መሰረት በማድረግ የተገኘውን ውጤት እንደ ሚመለከተው ለማሳየት ተሞክሯል።

የዚህ ጥናት የመጀመሪያው አላማ የተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ከመርሃ ትምህርቱና ከመማሪያ መፅሀፍቱ ጋር ምን አይነት ግንኙነት እንዳላቸው መፈተሸ የሚል ነበር። በመሆኑም በሁለቱም አመት (በራቱም ወሰነ ትምህርት) የተሰጡ የፈተና ሰነዶችን፣ መርሃ ትምህርቱንና መማሪያ መፅሃፉን በመፈተሸ የተገኙ ግኝቶችን ስንመለከት በሁለቱ አመት (በአራቱ ወሰነ ትምህርት)ከተሰጡ የቋንቋ ፈተናዎች መካከል የተካተቱት የቋንቋ ጥያቄዎች ከመርሃ ትምህርቱና የዘጠነኛ የክፍል ደረጃን ለማስተማር ከተዘጋጀው መማሪያ መፅሃፍ ጋር አንፃራዊ ግንኙነት እንዳላቸው ለመረዳት ተችሏል። ይህም ማለት በመርሃ ትምህርቱ 125፣ በመማሪያ መፅሀፉ 165፣ በፈተናዎቹ ደግሞ 160 የቋንቋ ይዘቶች ይገኛሉ። የግንኙነት ደረጃቸው በሁለት አመት የተሰጡት የቋንቋ ፈተናዎች ተደምረው በአማካኝ የሚገኘው ውጤት ከመርሀ ትምህርቱና ከመማሪያ መፅሀፉ ጋር ተቀራራቢ ቋንቋ ይዘት ምርጫ እንዳላቸው የሚያሳይ ነው።

ይህም ውጤት ከነ Harrison (1983) and Hughes (1989) የጥናት ግኝት ጋር ይደጋገፋል። ይህም ውጤት ከታለጌታ (2005 ዓ.ም)፣ ከአበበች (2004 ዓ.ም)፣ ከሲሳይ (2007 ዓ.ም)፣ ከበለጠ (1995 ዓ.ም) እና መሰረት (2005 ዓ.ም) የጥናት ውጤት ጋር ተደጋጋፊ ሆኖ ተገኝቷል።ስለሆነም በፈታናዎቹ የተካተቱት የቋንቋ ይዘቶች፣ ከመርሃ ትምህርቱና ከመማሪያ መፅሃፉ ይዘቶች ጋር በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ግንኑነት ያላቸው ሲሆን የግንኙነት ደረጃቸው ብዙም የሰፋ ባይሆንም በመካከላቸው ግን አንፃራዊ ልዩነቶች እንዳሏቸው ማወቅ ተችሏል።ልዩነቱም ከሌሎች የቋንቋ የትምህርት ይዘት የስርጭት መጠን አኳያ፣በመርሃ ትምህርቱና በመማሪያ መፅሀፉ ከተቀመጠው የቋንቋ ይዘት መጠን በላይ ፈተናዎች መገኘታቸው ነው። ይህ ሲባል ግን የተዘጋጁት የቋንቋ ጥያቄዎች ሲሰሉ በመርሀ ትምህርቱና በመማሪያ መፅሃፉ ከተቀመጡት የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ይበልጣሉ ለማለት

እንጂ ፍፁም ትክክል አይደለም ለማለት አይደለም፡፡ ነገር ግን ፈተናዎቹ ሲዘጋጁ ከነዚህ ጉዳዮች ጋር የበለጠ ቢቀራረቡ የተሻሉ ይሆን ነበር ለማለት ነው፡፡ ይህንን ሃሳብ Harrison (1983) እና Hughes (1989) ሲገልፁት አንድ ፈተና የይዘት ተገቢነት አለው የሚባለው መርሃ ትምህርቱንና መማሪያ መፅሀፉን መሰረት በማድረግ ሲዘጋጅ ነው በማለት ይህንን ሀሳብ ይደግፋሉ፡፡ ፅንስ ሀሳቡም የቋንቋ ፈተናዎች ሲዘጋጁ መርሃ ትምህርቱንና መማሪያ መፅሀፉን መሰረት በማድረግ መዘጋጀት እንዳለባቸው የሚያሳይ ነው፡፡

የዚህ ጥናት ሁለተኛው አላማ ከ2013-2014ዓ.ም በቀረቡት ጥያቄዎች ለየትኛው ይዘት የበለጠ ትኩረት የሰጠ እንደሆነ መፈተሽ የሚል ነበር፡፡ ለዚህ የጥናት አላማ ምላሽ የሚሆን የተገኘው ግኝት ጠቅለል ባለ መልኩ ሲገለፁ በጉራጌ ዞን እዣ ወረዳ በየኸንየ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከ2013-2014 ዓ.ም ለዘጠነኛ ክፍል ተዘጋጅተው በተሰጡ የአማርኛ ቋንቋ የማጠቃለያ ፈተናዎች ጥያቄዎችን ስንመለከት የሁለቱ አመት (የአራቱ ወሰነ ትምህርት) ሲጠቃለል በመጀመሪያ ደረጃ ለስነ-ፅሁፍ 63(39.37%) የተሰጠ ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ለሰዋስው 56(35%) የተሰጠ ሲሆን በመቀጠል ክሂል 20(12%) እና ቃላት 20(12%) ክብደት አግኝተዋል፡፡በመጨረሻም ዝቅተኛ መጠን የተሰጠው ቋንቋ ነክ የትምህርት ይዘት ነው፡፡የዚህ ጥናት ውጤት ግኝት ከታለጌታ (2005 ዓ.ም)፣ ከአበበች (2004 ዓ.ም)፣( ከሲሳይ 2007 ዓ.ም)፣ በለጠ(1995 ዓ.ም) እና መሰረት (2005 ዓ.ም) ካገኙት የጥናት ውጤት ጋር ይመሳሰላል፡፡ ምክንያቱም የቀረቡት ፈተናዎች ሲታዩ ሲገመግሙ የገኙት ውጤት የሚያሳየው በተሰጡት የሰዋስው ፈተናዎች ውስጥ የሰዋስው ፈተናዎችን ለመፈተሽ ሲሞከር ስነ-ድምፅን፣ ስነ-ምዕላድን፣ ስነ-አገባብንና ስነ-ፍችን የተመለከቱ የሰዋስው ፈተናዎች መቅረባቸውን ያስረዳሉ፡፡

ማህበራዊያን ንድፈ ሃሳብ የቋንቋ ፈተናዎች ሲዘጋጁ ሁሉንም የቋንቋ አሀዶች በትክክል አካቶ መያዝ አለበት ከሚለው ሃሳብ ጋር ይቃረናል Brown, (1996)፡፡ ስሆነም በሁለቱ አመት (በአራቱ ወሰነ ትምህርት)የቀረቡት ፈተናዎች ተማሪዎች ሊያውቋቸው፣ሊገነዘቧቸውና ሊረዷቸው የሚገቡ መሰረታዊ ቋንቋ ይዘቶች ቀርተዋል፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን በሁለቱ አመት በቀረቡት የቋንቋ ይዘቶች ስር የቀረቡት ንዑሳን የቋንቋ ትምህር ይዘቶች የስርጭት መጠን ፍትሃዊ ያልሆኑ ግን ደግሞ በተወሰኑ ከቋንቋ ነክ የትምህርት ይዘት ውጭ ያሉት ተቀራራቢ ይዘቶች ተካተዋል፡፡ Weir(1990) ተግባቦታዊ ንድፍ ሃሳብ ከሚያስቀምጠው የአካታችነት

የይዘት አመራረጥ አኳያ ሲታይ ውጤቱ ይለያያል፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ ከቋንቋ የፈተና ስርዓት አንፃር ችግሮች መኖራቸውን የሚያሳዩ ናቸው፡፡

ሶስተኛው የዚህ ጥናት አላማ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ማጠቃለያ ፈተናዎችን ከፈተ የይዘት ተገቢነት መርሆዎች አንፃር መፈተሽ የሚል ሲሆን ከቁጥብነት፣ከመአከላዊ ሀሳቡን በግንዱ ላይ ከማቅረብ አንፃር፣ከላስፈላጊ ጥቆማ የተሸለ መሆን፣የይዘት አቀራረብ በነጠላ ሀሳብ ከመሆን አኳያ፣ከአሳሳች ተገቢነት አንጻር ወዘተ ጥናቱ በጥናካሬ እንደታዩ የሚያመላክት ሲሆን በውስንነት ደግሞ የይዘት አካታችነት ወይም የንሞና አመራረጥ ፍትሃዊ አለመሆን፣የፈተና እቅድ ሰንጠረዥ በአግባቡ አለመኖር፣ፈተናዎቹ ሲቀርቡ በአውድ አለመሆን፣የፈተና አወቃቀርና አቀራረብ ፣የፈተና ቅለትና ክብደት አንፃር ውስንቶች እንደነበረባቸው የጥናቱ ውጤት ያመላክታል፡፡የዚህ የጥናት ውጤትም ከወንድምአገኝ (2005 ዓ.ም)፣ ከታለጌታ (2005 ዓ.ም)፣ ከመሰረት (2005 ዓ.ም) እና ሲሳይ (2007 ዓ.ም) የጥናት ውጤት ጋር ይመሳሳል፡፡ ይህ ማለት በፈተና አዘገጃጀት ሂደት ትክክለኛውን የቋንቋ ይዘት ንሞና ተከትለው እየተዘጋጁ እንዳልሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ሁሉንም የቋንቋ ንዑሳን ይዘቶች ምክንያታዊ በሆነ ስልት በፈተናው አካቶ ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል እንደተገነዘቡት በትክክል ለመለካት አልመቻሉን በጥናቱ ለማረጋገጥ ተሞክሯል፡፡

አራተኛው የዚህ ጥናት አላማ የተዘጋጀው ማጠቃለያ ፈተና ከፈተና የይዘት ተገቢነት መርሆዎች አኳያ ምን እንደሚመስል መፈተሽ ሲሆን ሌላው በዚህ ጥናት እንደ ድክመት የታየው የተዘጋጁት የቋንቋ ጥያቄዎች ከይዘት አካታችነት አንፃር ነው፡፡ በሁለቱ አመት (በአራቱ ወሰነ ትምህር) የተዘጋጁት ጥያቄዎች ለሁሉም የትምህርት ይዘት ትኩረት ተሰጥተዋል ቢባልም በዚያው ልክ ትክክለኛ የይዘት ንሞና መረጣ ተደርጎ ሁሉንም የቋንቋ ንዑሳን ይዘቶች በፈተናው አካታችነት አንፃር እንከኖች እንዳሉባቸው የጥናቱ ግኝት ያሳያል፡፡ የዚህ የጥናት ውጤትም ከወንድምአገኝ (2005 ዓ.ም)፣ ከታለጌታ (2005 ዓ.ም)፣ ከመሰረት(2005ዓ.ም) እና ሲሳይ (2007 ዓ.ም) የጥናት ውጤት ጋር ይመሳሳል፡፡በተመሳሳይ መልኩ ጥያቄዎች ሲቀርቡ አውዳዊ አለመሆን፣ፈተናዎች ሲዘጋጁ በፈተና እቅድ ሰንጠረዥ አለመሆን እና የፈተናዎቹ አወቃቀር ችግሮች እንዳሉባቸው ጥናቱ ይጠቁማል፡፡ነገር ግን

ከአሳሳች ተገቢነት አንፃር ፣ፈተናዎቹ ካስፈላጊ ጥቆማ፣ፈተናዎቹ ሲቀርቡ ካላስፈለጊ ጥቆማ ከማድረግ የተቆጠቡ መሆናቸውን የጥናቱ ግኝት ያመላክታል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና የመፍትሄ ሀሳቦች

## 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት መሰረታዊ አላማ በጉራጌ ዞን በእዣ ወረዳ በየዋኸንየ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ከ2013-2014 ዓ.ም ተዘጋጅተው በቀረቡ የአማርኛ ቋንቋ ማጠቃለያ ፈተናዎች ውስጥ የቀረቡ የቋንቋ ጥያቄዎች የይዘት ተገቢነት መገምገም እንደሆነ በቀደሙት ምዕራፎች ለመግለፅ ተሞክሯል፡፡ ስለሆነም በሁለቱም አመት (በአራቱ ወሰነ ትምህር) የተሰጡትን የቋንቋ ፈተናዎች ሰነድና ከፈተና ዝግጅ ክፍል በቃለ መጠይቅ የተገኙትን መረጃዎች መሰረት በማድረግ ጥናቱ ለሚከተሉት መሰረታዊ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ያለመ ነው፡፡

1. በፈተናው ውስጥ የተካተቱት የቋንቋ ጥያቄዎች ከመርሃ ትምህርቱና ከመማሪያ መፅሀፉ የቋንቋ ይዘቶች ጋር ምን አይነት ተመሳስሎ አላቸው?
2. ከ2013-2014 ዓ.ም ለዘጠነኛ ክፍል በተዘጋጁ የማጠቃለያ ፈተናዎች የበለጠ ለየትኛው የቋንቋ ይዘቶች የሰጠ ነው?
3. በፈተናዎቹ ውስጥ የተካተቱት ጥያቄዎች የቋንቋ የፈተና ይዘት ተገቢነት መርሆዎችን ያሟሉ ናቸው?
4. የተዘጋጁት የማጠቃለያ ፈተናዎች የይዘት ተገቢነት መርሆዎች  አኳያ ምን ይመስላሉ

የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ አይነታዊ እና መጠናዊ የምርምር ዘዴ የተመረጠ ሲሆን በአቀራረቡ ገምጋሚ የምርምር ንድፍን የተከተለ ነው፡፡ በዚህ ምርምር በመሰረታዊነት በመረጃ መሰብሰቢያነት ያገለገለው ሰነድ ፍተሻ ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በአጋዥነት ቃለ -መጠይቅ ተግባር ላይ ውሏል፡፡ ቃለ-መጠይቁ በትምህርት ቤቱ ለሚገኙ አማርኛ ቋንቋ የፈተና ዝግጅት ክፍል ሲሆን ቃለ-መጠይቁ ከተዘጋጀ በኋላ ሁለተኛ ዲግሪ ላላቸው የቋንቋ መምህራን እና ለአማካሪ መምህር በማቅረብ አስተማማኝነታቸውንና ተገቢነታቸውን ለማስገምገም ተሞክሯል፡፡

በሁለቱም አመት(በአራቱም ወሰነ ትምህርት) የተሰጡትን ፈተናዎች በማሰባሰብ እና በትምህርት ቤቱ የሚገኙ የቋንቋ መምህራን ቃለ-መጠይቅ በማድረግ ለጥናቱ የሚሆኑ ጠቃሚ መረጃዎች ለማግኘት ተችሏል፡፡ መረጃዎቹም በ2013 እና 2014ዓ.ም በአራቱ ወሰነ ትምህርት የተሰጡት የማጠቃለያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ከይዘት ተገቢነት አኳያ የተፈተሹ ሲሆን የቀረቡት የቋንቋ ጥያቄዎች ምን ምን፣ እንደሆኑ፣ ፈተናው የበለጠ ለየትኛው የቋንቋ ጥያቄ ትኩረት እንደሰጠ፣ ፈተናዎች ከፈተና መርሆዎች አንፃር ምን ጠንካራና ደካማ ጎን እንዳላቸው፣ከመርሃ ትምህርቱና መማሪያ መፅሀፉ ጋር ያላቸውን ትስስር ብሎም ከችሎታ መለኪያ ፈተና አዘገጃጀት መርሆዎች አንፃር ለመገምገም ተሞክሯል፡፡በሁለቱ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አማካኝነት የተሰበሰቡትን መረጃዎች በጭብጥ በጭብጣቸው ተለይተው ከተመደቡና ከተደራጁ በኋላ በሁለት መልኩ ተተንትነው

ቀርበዋል፡፡ የመጀመሪያው የጥናቱን ጥያቄዎች መሰረት በማድረግ የተገኘውን ውጤት በሀተታና በሰኝጠረዥ ለመተንተን ተሞክሯል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ጥናቱን እውን ለማድረግ የተነደፉትን አላማዎች ከተገኘው ውጤት በማስተሳሰር በአይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ስልት ለመተንተንና ለማብራራት ተሞክሯል፡፡

በሁለቱም አመት (በአራቱም ወሰነ ትምህርት) በጉራጌ ዞን በእዣ ወራደ በየኸንየ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 160 የቋንቋ ጥያቄዎች የቀረቡ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 63(39›375%)ስነ-ፅሁፍ ሲሆኑ በመቀጠል ሰዋስው 56(35%) ቦታ አግኝተዋል፡፡ሌሎቹ በተዋረድ ክሂል 20(12.5%)፣ ቃላት 20(12.5%) እና ቋንቋ ነክ ጉዳች 1(0.625%) ቦታ አግኝተዋል፡፡ የተዘጋጁት የቋንቋ ፈተናዎች ከመርሃ ትምህርቱና ከመማሪያ መፅሀፉ ጋር ያላቸው ትስስር የተሻሉ እንደሆኑ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ እነዚህ የቋንቋ ጥያቄዎች ከችሎታ መለኪያ የፈተና አዘገጃጀት መርሆዎች፣ ከይዘት የንሞና አመራረጥ ሂደት አኳያ ውስንነት ያሉባቸው እንደሆኑ መረዳት ተችሏል፡፡ ከትምህርት ቤቱ ቋንቋ መምህራን ቃለ- መጠይቁ መረዳት እንደተቻለው በመምህራን ፈተና ዝግጅት ክህሎት፣ ፍላጎት፣ የስልጠና ሁኔታ፣ የስራ ልምድ፣ የፈተና ዝግጅት የጊዜ መጠን፣ከሚከፈል ጥቅማጥቅም፣ ከክትትልና ቁጥጥር ጋር በተያያዘ በየጊዜው የሚዘጋጁት ፈተናዎች አግባብነታቸው ከአወንታዊነታቸው ይልቅ አሉታዊነታቸው የበዛ፣የፈተና መስፈርቶችን የጣሱ፣መለካት ያለባቸውን እውቀት፣ ክህሎትና አስተሳሰብ የማይለኩ፣ ትክክለኛ የይዘት ምርጫ ያልተከተሉ፣ በፈተና አዘጋጆች ፍልጎትና ምርጫ የተወሰኑ ፈተናዎች እንደሚዘጋጁ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ የቀረቡት የቋንቋ ፈተናዎች ከቀረቡት የፈተና መስፈርቶች አኳያ ውስንነት ያለባቸው እንደሆኑ መረዳት ተችሏል፡፡ በሁለቱም አመት( በአራቱም ወሰነ ትምህርት) ተዘጋጅተው የቀረቡት የፈተና ሰነዶች ሲፈተሹ የሚያሳዩት ይህንኑ ነው፡፡ነገር ግን ሁሉንም የፈተና ጥያቄዎች ውስንነት አለባቸው ለማለት ሳሆይን በአራቱም ወሰነ ትምህርት ከቀረቡት ፈተናዎች መካከል አብዛኛዎቹ ችግሮች አሉባቸው ለማላት ነው፡፡

## 5.2 መደምደሚያ

በጥናቱ መነሻ ችግር እንደተገለፀውና በሌሎች ጥናቶች ለማረጋገጥ እንደተሞከረው እስካሁን በቋንቋ ፈተናዎች የይዘት ተገቢነት ላይ የሚነሱ ችግሮች እንደቀጠሉ ናቸው፡፡ የጥናቱን ግኝቶች መሰረት በማድረግ በጉራጌ ዞን በእዣ ወረዳ በየዋኸንየ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

ከ2013-2014ዓ.ም እየዘጋጁ ይሰጡ የነበሩት የቋንቋ  ፈተናዎች የይዘት አግባብነታቸው ሲፈተሽ  ዝቅተኛ በሚባል ደረጃ የሚፈረጁ ናቸው፡፡ በፈተናው የቀረቡትን ጥያቄዎች በመማሪያ መፅሀፉና በመርሃ ትምህርቱ ከተሰጠው የትኩረት መጠን አንፃር ሙሉ በሙሉ ተመጣጣኝ ወይም እኩል ነው ባይባልም አንፃራዊ የሆነ ትስስሮሽ አላቸው፡፡ ነገር ግን በሁለቱ አመት በአራቱ ወሰነ ትምህርት ተዘጋጅተው የቀረቡት የቋንቋ  ፈተናዎች የተማሪዎችን ችሎታ በትክክል ከመለካት አኳያ ውስንነት ያለባቸው ናቸው፡፡ አንድ የቋንቋ የትምህርት ይዘት መያዝ ያለባቸውን የውክልና ወይም ንሞና መጠን በትክክል ያገናዘቡ አይደሉም፡፡

ስለሆነም ሁሉንም የቋንቋ ይዘቶች አመጣጥኖ ተማሪዎችን የእውቀት ክፍሎች ከመለካት አንፃር ክፍተቶች ይበዙበታል፡፡ በተለይም ፈተናው በአራቱ የሰዋስው ክፍሎች ማለትም በስነ-ድምፅ፣ በስ-ምዕላድ፣ በስነ-አገባብና በስነፍች ስር የሚገኙ ሌሎች ንዑሳን የሰዋስው የትምህርት ይዘቶችን አካቶ ከማቅረብ አንፃር ውስንነት ያሉባቸውናቸው፡፡እንዲሁም ከስነ-ፅሁፍ ንዑሳን ይዘቶች አንፃር ልቦለድ፣.ተውኔት፣ስነ-ቃል፣ስነ-ግጥም ወዘተ አመጣጥኖ ከማቅረብ አንፃር ውስንነቶች ይስተዋላሉ፡፡ ሌሎችም እንዲሁ ክሂል፣ቃላትና ቋንቋ ነክ የትምህርት ይዘቶች በተመሳሳይ ሁኔታ የሚገለፅ ነው፡፡ ጥያቄዎቹ በአውድ ካለመቅረባቸው ባሻገር ሲቀረፁ የተማሪዎችን አዕምሯዊ የማስላትና የማመዛዘን ክህሎት ለማሳደግ ታስቦ አይመስልም፡፡ ይልቁንም በሁለት አመት (በአራቱም ወሰነ ትምህርት) የተዘጋጁትን ጥያቄዎች የቅለት ክብደት ሁኔታ ስናይ ቀላል በሚባል ደረጃ የቀረቡ ናቸው፡፡ በየወሰነ ትምህርቱ የቀረቡት የቋንቋ ጥያቄዎች የሁሉንም አይነት የተማሪ ችሎታ ያገናዘበ ሳይሆን በዝቅተኛ ችሎታ ለሚገኙ ተማሪዎች አይነት የተዘጋጁ ናቸው፡፡

እንዲሁም የቀረቡትን የቋንቋ ጥቄዎች የይዘት አደረጃጀቶችን በምናይበት ጊዜ የተወሰኑት የጥያቄዎቹ ፅንስ ሀሳብ በጥቄው ግንድ ላይ ሳይሆን በምርጫዎቹ ፍንጭ ሰጭነት የተመሰረቱ ናቸው፡፡ የተወሰኑት ጥቄዎቹ ሲቀረፁ ነጠላ ሀሳብ መያዝ ሲገባቸው ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሀሳቦችን ያዘሉ ናቸው፡፡ ይህ ደግሞ ከፈተና መርሆዎች አንፃር የሚመከር ጉዳይ  አይደለም፡፡

## 5.3 የመፍትሄ ሀሳቦች

የቋንቋ ፈተናዎች በሚዘጋጁበት ጊዜ ፈተናዎቹ የትምህርቱን ዓላማ ከግብ ማድረስ ይችሉ ዘንድ፣ በፈተና የተፈለገውን መረጃ ማግኘት ያስችል ዘንድ የሚዘጋጁት ፈተናዎች የፈተና መመዘኛ መስፈርቶችንና መርሆዎችን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ማዘጋጀት ተገቢ ነው፡፡ በጥናቱ ላይ በተዘጋጁ ፈተናዎች ውስጥ በተካተቱት የቋንቋ ጥያቄዎች ይዘት ላይ ድክመቶች ይታያሉ፡፡ በፈተናዎቹ ላይ የታዩትን ጠንካራ ጎኖች የበለጠ አጠናክሮ በመቀጠል ድክመቶቹ ግን በቀጣይ በሚዘጋጁ ፈተናዎች እንዳይደገሙ የሚከተሉትን የመፍትሄ ሀሳቦች አጥኚው አቅርቧዋል፡፡ እነሱም፡-

- በችሎታ መለኪያ ፈተና ውስጥ ተካተው የሚገኙት የቋንቋ ጥያቄዎች አስቀድመው ተማሪዎች የተማሯቸውን ይዘቶች መነሻ በማድረግ የሚዘጋጁ ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት ጥያቄዎቹ ሲዘጋጁ ለየይዘቶቹ የተሰጠውን የትኩረት ደረጃ መሰረት በማድረግ ወካይ ጥያቄዎች በፈተና ውስጥ ቢካተቱ፣
- ፈተናዎች በሚዘጋጁበት ጊዜ የፈተና አዘጋጆች መርሃ ትምህርቱንና መማሪያ መፅሃፉን መሰረት በማድረግ የተማሪዎችን አጠቃላይ ችሎታ ሊለኩ የሚችሉ ሆነው ቢዘጋጁ መልካም ነው፡
- ተፈታኞች ለጥያቄዎቹ በግምት ምላሽ እንዳይሰጡ፣ ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ተገቢውን መልስ በማመዛዘን፣በመመራመር ይመልሱ ዘንድ በአማራጭነት የሚቀርቡት ትክክለኛና አሳሳች መልሶች በይዘት ተገቢነታቸው፣በቃላት መጠናቸው ተመጣጣኝ በሆነ መልክ ቢዘጋጁ፣
- ለጥያቄው በአማራጭነት የሚቀርቡት ምላሾች አንድ ትክክለኛ መልስ ብቻ እንዲይዙና መልስ የለም እንዲሁም ሁሉም መልስ ናቸው ከሚሉ አባዜ ቢላቀቁ ፣
- ፈተናውን ለሚያዘጋጁት አካላት ተገቢ ስልጠና በመስጠት ፈተናውን ረዘም ያለ ጊዜ ስጥቶ ፈተናውን ከማዘጋጀታቸው በፊት ተገቢ የፈተና እቅድ ተጠቅመው ይዘቱን በምን ያክል ውክልና መያዝ እንዳለበት የሚደነግገውን ሂሳባዊ ስሌት መሰረት ተደርጎ ቢሰራ፡
- በት/ቤት ደረጃ ተዘጋጅተው ለበርካታ ተማሪዎች የሚደደርሱ ፈተናዎች ስለሆኑ ፈተናዎችን በሀላፊነት በአመት ሁለት ጊዜ በክላስተር ደረጃ እንደ ማትሪክ የራሱ ባለሙያ በየትምህርት አይነቱ ተመድቦ ለጥራቱ ትኩረት ተሰጥቶ ቢሰራ፡

- ፈተናዎቹ ተዘጋጅተው ለተማሪዎች ከመቅረባቸው በፊት ስለትክክለኝነታቸው ማረጋገጥ ተገቢ ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም በት/ቤት ደረጃ የሚዘጋጁት ፈተናዎች ተገቢነታቸው ከፍ እንዲል በሚመለከተው አካል ከፈተና መርሆዎች አንፃር ቅድመ ግምገማ ቢደረግ፡
- በት/ቤት ደረጃ የሚዘጋጁት ጥያቄዎች የይዘት አመራረጣቸው የተማሪዎችን ሁለንተናዊ ሰብዕና፣ እውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት በወጉ የሚለኩ ሆነው ጥንቃቄ በተሞላበት መልኩ ቢዘጋጁ፡
- የቋንቋ ጥያቄዎችን በይዘትነት ሲመረጡና በፈተና መልክ ሲቀረፁ በደረቁ እንደወረደ ሳይሆን መዘጋጀት ያለባቸው ተመጥነው፣ አውዳዊነት ተላብሰው፣ ግልፅና ነጠላ ሀሳብን ይዘው ቢሆን፡
- የቋንቋ ፈተናዎች በሚዘጋጁበት ጊዜ ተማሪዎች እንዲማሩት ከተቀመጡት ይዘቶች በተሰጣቸው የጊዜ ክብደትና ቅለት መሰረት ሁሉንም ይዘቶች መሰረት በማድረግ ሁሉንም ችሎታዎች ለመለካት ጥረት ቢደረግ፡
- የቋንቋ ፈተናዎች ለክፍል ደረጃቸው ሲዘጋጁ የተማሪዎችን ከውስጣዊ ተገቢነትና (Internal validity) ውጫዊ ተገቢነት (external validity) ጭምር በደንብ ተቃኝቶ ቢሆን፡
- የቋንቋ ጥያቄዎች በሚዘጋጁበት ጊዜ የጥያቄዎቹ መአከላዊ ሀሳብ በጥያቄው ግንድ ላይ በማድረግ ፣ከአላስፈላጊ ጥቆማ በመጠንቀቅ፣ የቋንቋውን ስርአት ለማስገንዘብ ሳይሆን ተግባቦትን መሰረት ያደረገ ሆኖ ቢዘጋጅ፡
- በመጨረሻም በት/ቤት ደረጃ የተዘጋጁት የቋንቋ ፈተናዎች ከመርሃ ትምህርቱና ከመማሪያ መፅሀፍቱ ጋር ያላቸው ትስስር በተሻለ መልኩ ቢታይም ከቋንቋ ፈተና የይዘት ተገቢነት መርሆዎች አንፃር በርካታ ውስንነቶች እንዳሉ ጥናቱ አመላክቷል፡፡ ስለሆነም ሁሉንም የቋንቋ ይዘቶች ከፈተና ይዘት አቀራረብ አንፃር በቀጣይ ጥናት ቢደረግባቸው የተሻለ ውጤት ሊታይ ይችላል፡፡ እንዲሁም ፈተናዎቹ ከአስተማማኝነትና ከቅለት ክብደት አንፃር በዚህ ፈተና በሂሳባዊ ስሌት ስላልተፈተሹ በቀጣይ ሰፋ ያለ ጥናት ቢደረግባቸው የተሸለ ውጤት ሊያመላክቱ ይችላል፡፡

## ዋቢ መፅሃፍት


ሲሳይ ቴሌ። (2007)። ከ2001- 2006ዓ.ምበሀገር አቀፍ ፈተናዎች ድርጅት ለአጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠቃለያ በተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘትና አቀራረብ ግምገማ። ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያነት የቀረበ ፅሁፍ። አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)።

ቁምላቸው ጤናው፡፡ (2010 ዓ.ም) ፡፡ *ከ2007-2009 ዓ.ም ለዲላ መምህራን ትምህርት ኮላጅ ሰልጣኞች የተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ የሰዋስው ፈተና ጥያቄዎች የይዘትና*

*አዘገጃጀት ተገቢነት ፍተሻ። (ያልታተመ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሙያነት የቀረበ) ። ዲላ ዩኒቨርሲቲ፣ ዲላ።*

በለጠ ያዕቆብ ። (2006 ዓ.ም) ። *የበሳል ድርሰት ምዘና ውጤት አግባብነት፣* በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ተተካሪነት። ለዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት። አዲሳ አበባ

በለጠ ያዕቆብ። (1995 ዓ.ም)። "ለዘጠነኛ ክፍል የሚዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ለደረጃው ከሚቀርበው ትምህርት ጋር ያላቸው የይዘት አግባብነትና የአጠያየቅ ብቃት ትንተና።" አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት።

ተስፋዬ መኮንን። (2000) ። *"በኮምቦልቻ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከ1997 እስከ 2000 ዓ.ም ድረስ የቀረቡት የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ከመርሃ ትምህርቱ ጋር ያላቸው የይዘት አግባብነት እና የአጠያየቅ ብቃት።" ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ-ጽሑፍ ክፍል፣ ለቢ.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)።*

ታለጌታ ይመር ። (2005) ። በሀገር መከላከያ ሰራዊት ከ2001-2004ዓ.ም ለርቀት ትምህትር መርሃ ግብር የቀረቡ የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ብሄራዊ ፈተናዎች ከመማሪያ መፅሃፉ ጋር ያላቸው ዝምድና ።ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጽሁፍ ። አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ (ያልታተመ)።

ትንሳኤ ብርሀኔ።(1988)።"የአማርኛ ቋንቋ የቃላት አፈታተን በሁለተኛ ደረጃ አጠቃላይ ሀገር አቀፍ ፈተና መነሻነት" ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ፣ አዲስ አበባ

አበበች ገብሩ። (2004 ዓ.ም)።ከ1998-2003 ዓ.ም *በኦሮሚያ ክልል አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ተዘሃጅተው የቀረቡ የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተና ውስጥ የሰዋሰው ጥያቄዎች ግምገማ። (ያልታተመ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሙያነት የቀረበ) ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲሳ* አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ) ።

አገኘሁ ተስፋ:: (2006 ዓ.ም) ፡፡ የኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ወሽባክ፡፡ (ያልታተመ ለሰስተኛ ዲግሪ ማሙያነት የቀረበ) ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲሳ አበባ፡፡

ኤደን ብርሃኔ፡፡(2002) ፡፡"ከ1995 ዓ.ም እስከ 2001 ዓ.ም በቀረቡ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች የቃላት አፈታተን ግምገማ በደብረማርቆስ ከተማ በሚገኙ ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት፡፡" በቋንቋዎች ጥናት ተቋም፣ ለማስተርስ ዲግሪ ማሚያ የቀረበ የጥናት ፅሑፍ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)፡፡

ወንድሙ ነጋ:: (2011 ዓ.ም)፡፡‹‹በ2008 እና በ2009 የትምህርት ዘመን የተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ ማጠቃለያ ፈተናዎች የይዘት ተገቢነትና አስተማማኝነት በ7ተኛ ክፍል ፈተናዎች መነሻነት መፈተሽ›› (ያልታተመ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሙያነት የቀረበ ጥናት)፡፡ አርባ ምንጭ ዩኒቨሪሲቲ፣ አርባ ምንጭ፡፡ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሚያነት የቀረበ ጽሁፍ። አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ (ያልታተመ)።

ገነት አታቱ::(2011ዓ.ም)፡፡‹ከ2005–2010 ዓ.ም ለ10ኛ ክፍል በተዘጋጁ ብሔራዊ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱ የስነ-ጽሁፍ ጥያቄዎች የይዘት ተገቢነትና አቀራረብ ግምገማ››፡፡ (ያልታተመ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሙያነት የቀረበ )፡፡ ዲላ ዩኒቨርሲቲ፣ ዲላ፡

ጫንያለው ሲሳይ።(2010)። በአማራ ክልል በሚገኙ ሶስት የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች በአማርኛ ቋንቋ የተከታታይ ምዘና አተገባብር የምምህራንና የተማሪዎች ተነሳሽነተን መመርመር።ለሶስተኛ ድግሪ ማሚያነት የቀረበ ፅሁፍ። አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ(ያልታተመ)።

Alderson,J .C.(1995).Language testing consturaction and Evaluation.Cambridge : Cambridge University .

Bachman, L. F. (1990). Fundamental consideration in language testing.Oxfored: Oxfored university .

Bachman, L.F. (1995). *Fundamental consideration in Language Testing.* Oxford; Oxford university .

Bachman, L.F. and palmer, A. S. (1996). *Language Testing in Practice*, New York; Oxford University.

Bachman,L. F. and Palmer, A. S. (1996).Language testing practice.New yourk.Oxfored University.

Baker, D. (1989). Language testing .Acritical surey and practicale guide. Londn: Edwared Amold.

Baker, D. (1989). *Language Testing*: Critical Survye and Practical Guide. London: Edward Amold.

Brown, H.D. (1980). Principle of Learning and Teahcing. New Jeresey: Prentice Hall Ince.

Brown, H.D. (2004). Language Assessment principle and class room practices. New York: Pearson Education, Inc.

Gipps,V. (1996). Beyond Testing towards a theory of Educational assessment.

Harmer. J. (2001). *The practice of English Language Teaching*. 3rd ed. London: Pearson Education Limited

Harrison, A. C. (1983) . Language Testing hand book. London: Machmillan. Puplisher . Ltd .

Heaton J. B. (1980). Writing English language tests . London : group limetd.

Heaton, J.B. (1990). *Writing Engilsh Language Tests*. Londen; longman.

Henning, G. (1987). A Guide to Language Testing. Cambridge: Cambridge University.

Henning, G. (1987). *A Guide to language Testing*. Cambridge, mass; Newbury House.

Hughes, A. (1989). Testing for Language Teachers . Cambridge: Cambridge University .

Hughes, A. (1989). *Testing for language Teachers*. Cambridge; Cambridge University .

Madsen, H.S. (1983). Teaching in testing . Oxforde: Oxfored University .

Merharens, W .A. and J. J . Lehmana (1974). Standardized tests in education . New Yourk: prentice Hall. INC.

Messick, S . (1995) . Validity of pscological Assessiment validation of intrefrance from persons respons & performance as a scince inquiry in to score meaning . Ameriacan psychologist , 50 (9) 741-749.

New York MacMillan.

Nunan,D.(1989).Undersanding language Classrooms. New York: Prentice Hall.

Smisth , F. (1987) . Writing and the writing . Henieman . Education book.

Spoolsky, B. (1976).Measured Words. Oxford: Oxford University .

Tamene . (2007). Factor Afecting the inplemention of continouse Assessiment selecting writing Oromia teacher traning colleges, (mastersThesis) Adise Abeba,(unpuplished).

Ur, (1996). A *Course in Language Teaching.practice and Theroy Cambridge*: Cambridge University .

Weir, C. J. and Shaw, S . D . (2005) . Establishment o the validity of Cambridge ESOL writing testes: towared the implemention socio cognitive model for test validation. Research note, 23: 10-14.

# አባሪዎች

## አባሪ አንድ

### በ2013 ዓ. ም በየዋኸንየ አጠ/2ኛ/ደ/ ት/ቤት የ1ኛው ሴ/ር የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ማጠቃለያ ፈተና

**የጥያቄ ብዛት 40**
**ሰዓት 50 ደቂቃ**

I የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን እውነት ስህተት የሆነውን ሀሰት በማለት መልስ ( ሸ )

1.አንድ ቃል በተለያየ አውዶች ውስጥ ሲገኝ የሚኖረው አገባባዊ ፍች እንደ ዓ.ነገሮቹ

አይለያይም።
2.እያነበብን /እያዳመጥን) ማስታወሻ የምንይዝባቸው አጋጣሚዎች በርካታ ናቸው።
3.የአንድ ነገር ውጤት ከሱ በፊት በሚኖረው ምክንያት / መንስኤ / ላይ የተመሰረተ ነው።
4.ስነ _ጽሁፍ ግለሰብ ወይም ደራሲ የማንጠቅስለት የህዝብ ፣የቡድን አእምሮና የልማድ ውጤት ነው።
5.ምዕላድ የምንለው ትርጉም አዘል የሆነና አነስተኛ ወደ ሆኑ ትርጉም አዘል ክፍሎች ሊሸነሽን የሚችል የመጨረሻ ንዑስ አሀድ ነው።
6.በግጥም ቅርጽ የቀረበን ጽሁፍና በዝርው ቅርጽ የቀረበውን ጽሁፍ ስናነብ የምንከተለው ስልት የተለያየ ነው።
7.ቤተ_መጽሀፍት ውስጥ የምንፈልገውን መረጃ ለማግኘት በቅድሚያ የቤተ_መጽሀፍት ስነ_ስርዓትና የመጽሀፍት አፈላለግን ማወቅ ይጠበቅብናል።
8.ውይይት በአጋጣሚ የሚፈጠር ክንውን ነው።
9.አንቀጽ ብዙውን ጊዜ አንድ ሀይለ ቃል አለው።
10.በጽሁፍ ውስጥ የስርዓተ ነጥቦች ዋነኛ ተግባር የጽሁፍን መልዕክት ሳይድበሰበስ በአፍታ እይታ ለአንባቢው ምስል እንዲከሰት ማገዝ ነው ።
II በ "ሀ " ለተዘረዘሩት ስርዓተ ነጥቦች እና የቃል ክፍሎች በ "ለ " ስር ከቀረቡት በመምረጥ አዛምድ (ጂ )

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 11.ደሳለኝ መኪና ገዛ። | ሀ.ስም |
| 12.ፍቅር ረቂቅ ነገር ነው። | ለ.ግስ |
| 13.አየለ ጎበዝ ተማሪ ነው። | ሐ.ተውሳከ ግስ |
| 14.መጽሀፉን በፍጥነት መለሰ። | መ.ቅጽል |
| 15.ዛሬ ስለ ቃል ክፍል ተማርን። | ሠ.መስተዋድድ |
| 16.የሌላ ሰው ስራ እንደ እራስ አድርጎ ከመጠቀም እንደ ሌባ ከመቆጠር ያድናል። | ረ. ድርብ ሰረዝ |
| 17. በመጨረሻ በመግባት የአንድን ሀሳብ መጠናቀቅ ያመለክታል። | ሰ.ትምህርተ ጥቅስ |
| 18.ተያያዥነት ያላቸውን ሀሳቦች አጣምሮ ለማቅረብ ይጠቅማል። | ሸ.ነጠላ ሰረዝ |
| 19.የተጻፈ ጽሁፍ እርማት ስንሰጥ መሰግባት ያለበት የተረሳ ቃል ካለ የምናመለክትበት ስርዓተ ነጥብ | ቀ.አራት ነጥብ |
| 20.ተመሳሳይ ሙያ ያላቸውን ዝርዝር ጉዳዮች ለይቶ ለመጻፍ ይጠቅማል። | በ.እመጫት |

III. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ምረጥ (ጭ)
21.ስለውይይት ዝግጅት ትክክል የሆነው የቱ ነው?
ሀ.ስለርዕሰ ጉዳዩ የጠለቀ እውቀት አላቸው የሚባሉ ሰዎችን ጠይቆ ፍሬ ሀሳቦችን መመዝገብ
ለ.ተራ ጠብቆ መናገር ሐ.ፍርሀትን ማስወገድ መ.የሌሎችን ሀሳብ ማክበር
22.በየትኛውም አጋጣሚና ሁኔታ ማስታወሻ መያዝ ስንፈልግ ምን ምን ማዘጋጀት አለብን?
ሀ.ወንበርና ደብተር ለ.ቦርሳና ወንበር ሐ.ብዕርና ቦርሳ መ.ወረቀትና ብዕር

23.በክርክር ጊዜ ትኩረት ከምንሰጣቸው ነጥቦች ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ.በቂ ዝግጅት ማድረግ ሐ.ለተቃዋሚ ተገቢ መልስ አለመስጠት
ለ. ተራ ጠብቆ መናገር መ. የሌላውን ሀሳብ አለማንቋሸሽ
24.ያላለቀ ሀሳብ መኖሩን የምናመለክትበት ስርዓተ_ነጥብ የቱ ነው?
ሀ. ቅናፍ ለ.እዝባር ሐ.ትምህርተ ጥቅሰ መ.ነጠብጣብ
25.ግራና ቀኝ መሪ ያለው የሀረግ አይነት የቱ ነው? ሀ. ስማዊ ለ.ግሳዊ
ሐ. መስተዋድዳዊ መ.ተውሳከ ግሳዊ
26.የቤተ መጽሐፍት ዋና ዋና ደንቦችንና ስነ_ስርዓቶችን መጠበቅ በተመለከተ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው? ሀ.ፀጥታን መጠበቅ ለ.የግል መጽሀፍ ይዞ አለመግባ
ሐ. መጽሀፍትን በተገቢው ሁኔታ አለመጠቀም መ.ነጠላ ጫማ ለብሶ አለመግባት
27.ነገሮችን በጊዜ ቅደም ተከተል ነሚተርክልን የድርሰት አይነት የቱ ነው?
ሀ.አመዛዛኝ ለ.ተራኪ ሐ. ገላጭ መ. ስዕላዊ
28.ከሚከተሉት የስነ ቃል ዘውግ ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ.ቃለ ግጥም ለ.ዝርው ቃል ትረካ ሐ. አጫጭር ቅርጾች መ. አውዳዊነት
29.ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ከቃል ክፍሎች አይመደብም፡፡
ሀ. ግስ ለ.ቅጽል ሐ. መስተዋድድ መ.ቅኔ
30. ________ከስም በፊት በመግባት ስሙን ከመጠን፣ከባህሪ አንጻር የሚገልጽልን የቃል ክፍል ነው፡፡ ሀ.ተውሳከግስ ለ.ቅጽል ሐ. ስም መ.ግስ
31.ግልገሏ በሚለው ቃል ጥገኛ ምዕላድ የሆነውየቱ ነው?
ሀ.ዋ ለ.እ ሐ. ሏ መ.ግ
32.የስነ_ጽሁፍ መንጨም ተቀባዩም ሰው ነው፡፡ የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍች የሆነው የቱ ነው? ሀ.መገኛ ለ.ችሎታው ሐ. ወሳጁ መ.አንባቢው
33.ቂመኛ ከሚለው ቃል ነጻ ምዕላድ የሆነው የቱ ነው?
ሀ.ቂማ ለ.ቂሙ ሐ.ቂም መ.ቀሞች
34.ወታደሩ ጠላቱን በሳንጃ ሸረከተው፡፡ ለተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍች የሆነው የቱ ነው?
ሀ.ቀደደው ለ.ወጋው ሐ.ከካው መ. ገረደፈው
35.ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ከስነ_ቃል ሊመደብ አይችልም፡፡
ሀ.ምሳሌያዊ አነጋገር ለ.እንቆቅልሽ ሐ.የሥራ ላይ ግጥሞች መ.ልቦለድ መጽሀፍ
36.ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የውይይት አቀራረብ መመሪያ አይደለም፡፡
ሀ.ተራ ጠብቆ መናገር ለ.ርዕሱን በተመለከተ መረዳት ሐ.የሌሎችን ሀሳብ ማክብር
መ.ሲናገሩ ድምፅን መመጠን
37.አንድ ተማሪ ቤተ_መጽሀፍት ውስጥ ገብቶ ጥናት ሲያደርግ ማስተዋሻ በመያዝ ተግባር መከተል ያለበት የቱን ነው? ሀ.ያነበበውን ሁሉ መጻፍ ለ.እያንዳንዱን ሀሳብ ለመጻፍ መሞከር ሐ.መሠረታዊ የሆኑ ነጥቦችን መዝግቦ መያዝ መ.ከጓደኛ ጋር ድምፅን ከፍ አድርጎ መወያየት
38.ከሚከተሉት አንዱ የአንድ ጽሁፍ ኪነ_ጥበባዊ ብቃት መመዘኛ አይደለም፡፡

ሀ.በአገላለጹ የተባ መሆን ለ.ህይወትን ማሳየት ሐ.በጽሁፍ አማካኝነት መግለጽ
መ.ማራኪና ሳቢ መሆን

39.ሰዎች ጊዜና ቦታ ወስነው በመገናኘት አንድና ከአንድ በላይ በሆኑ ርዕሰ ጉዳዮች ሀሳብ የሚለዋወጡበት እና የጋራ መግባባት የሚደርሱበት ምን ይባላል?

ሀ.ጭውውት ለ.ክርክር ሐ.ውይይት መ.አንቀጽ

40.ቁርኝት ለሚለው ቃል ቀጥተኛ ፍች የሆነው የቱ ነው?

ሀ.ልዩነት ለ.ትስስር ሐ.ጥንቅር መ.ዝግጅት

አዘጋጅ መ/ርት አጃኢባ መሀመድ

**2013 ዓ .ም በየዋኽንየ አጠ/2ኛ /ደ/ት/ቤት የ2ኛው ሴ/ር የ9ኛ ክፍል አማርኛ ማጠቃለያ ፈተና**

**የጥያቄ ብዛት 40**

**የተሰጠ ሰዓት 1: 00**

I ትክክል የሆነውን እውነት ስህተት የሆነውን ሀሰት በማለት መልስ ( ሽ )

1.ከገፀ ባህሪ አንደበት የሚፈልቅና በተመረጡ ቃላት የሚፃፍ ተውኔት አላባዊያንሴራ ይባላል

2..የሰውን ስሜት ጨቁኖና በፍርሀት አስሮ የሚይዝ የተውኔት አይነት ኮሚዲ ነው።

3.በቃል ወይም በጽሁፍ በዝሩ ወይም በግጥም የሚነገር ወይም የሚጻፍ ድርሰት ቅኔ ይባላል ።

4.ስነ ቃልን በሁለት መንገድ መሰብሰብ ይቻላል ።

5.የንግግር ርዕስ መምረጥ ንግግር በሚቀርብበት ጊዜ የምንከተለው መመሪያ ነው ።

6. ልብሷ ከጥጥ ተሰርቷል ።የተሰመረበት ቃል እንደ ባለቤት የገባ ነው።

7.ጎጆ የሚለው ቃል ፍካሪያዊ ፍቹ ትዳር ይሆናል።

8.ገፀ ባህሪያቱን ለማስገረም ወይም ሰውን ለማሳቅ ሲባል በተጋነነ መንገድ መንገድ እቃ ሲሰበር የሚታይበት የተውኔት አይነት ፋርስ ይባላል።

9. የአንድን ቅኔ ግልጹንና ድብቁን መልዕክት በአንድ ላይ የሚይዘው ቃል ሰም ይባላል።

10. "ከርክር "ለመጻፍ የቋንቋ ክሂል ምሳሌ መሆን ይችላል።

II በ" ሀ "ስር ለተዘረዘሩት በ" ለ " ስር ከሚገኙት ጋር በሀሳብ የሚገናኚትን አዛምዱ

| ሀ | ለ |
| --- | --- |
| 11.ድንገት ተከሰተ | ሀ.ሰምናወርቅን በአንድ ላይ የያዘ |
| 12.የወጣው ፈተና ምንኛ | ለ.ልብሴ |
| 13.የዘንድሮ ዓመት | ሐ.ዱላውን |
| 14.የተማሪ አጭበርባሪ | መ.መስተዋድዳዊ ሀረግ |
| 15.በመረከብ ላይ | ሠ.ቅጽላዊ ሀረግ |
| 16.ተሳቢ አመልካች | ረ..ስማዊ ሀረግ |
| 17.የዘርፍነት አመልካች | ሰ.ተውሳከ ግሳዊ ሀረግ |
| 18.ህብረ ቃል | ሸ.ግሳዊ ሀረግ |

19.እሷ ቀ.ድርጊት አመልካች

20.ግስ በ.ተውላጠ ስም

III ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ምረጥ ( ጭ)

21.ለሰው መድሀኔቱ ሰው ነው ::________ማንም ሰው በራሱ ምዕሉ አይደለም። ሁለቱን ነጣላ ሀሳቦች የሚያይዝልን የቱ ነው?

ሀ. ቢሆንም ለ.ምክንያቱም ሐ.ነገር ግን መ. ይሁን እንጅ

22. ከሚከተሉት የተውኔት አላባዊያን ውስጥ አንዱ ሌሎቹን ያጠቃልላል።

ሀ.መቼት ለ.ግጭት ሐ.ትልም መ.ታሪክ

23.በአቀራረብ ወቅት የሚከናወን የንግግር መመሪያ የትኛው ?

ሀ. ርዕስ መምረጥ ለ.የንግግሩን አላማ ለአድማጭ ማሳወቅ ሐ.ርዕስ መወሰን መ.መረጃ መሰብሰብ

24.ህፃኑ ልጅ የመስኮቱን መጋረጃ ጎተተው ::የተሰመረበት ሀረግ ሙያ_______ነው።

ሀ.ባለቤት ለ.ማሰሪያ አንቀጽ ሐ.ባለገንዘብነት መ.ተሳቢ

25.የአንድን ነገር አሰራር የሚያብራራ የድርሰት አይነት________ይባላል።

ሀ.ስዕላዊ ድርሰት ለ.አመዛዛኝ ድርሰት ሐ.ተራኪ ድርሰት መ.ገላጭ ድርሰት

26.በሽታው በየጊዜው እየተነሳበት ያሰቃየዋል _______እስካሁን ግን ለከፋ አልሰጠውም።

በባዶ ቦታው መግባት ያለበት ሥርዓተ ነጥብ ምንድን ነው?

ሀ.ነጠለ ሰረዝ ለ.ድርብ ሰረዝ ሐ. ጥያቄ ምልክት መ.አራት ነጥብ

27.በተውኔት ውስጥ የሚካሄዱትን ነገሮች ምክንያትና ውጤት የሚያሳይ የቱ ነው?

ሀ. ታሪክ ለ.መቼት ሐ.ግጭት መ.ሴራ

28.በስራ ደብዳቤ ወቅት የተቀባዩ አድራሻ በወረቀቱ የት ቦታ ይጻፋል ፡፡

ሀ.በስተቀኝ ራስጌ ለ.በስተግራ ራስጌ ሐ.በስተቀኝ ግርጌ መ.በስተግራ ግርጌ

29." በሬ "በሚለው ቃል ላይ መግባት ያለበት ያለበት መድረሻ ቅጥያ የትኛው ነው?

ሀ. ዎች ለ.ኦች ሐ.ኣች መ.ኡ

30.በረሀብ የተጠቃ ወገኑን ለመታደግ ቆርጦ ተነሳ። የሰመረበት ቃል አገባባዊ ፍች የቱ ነው?

ሀ.ለማበሳጨት ለ.ለማዳን ሐ.ለማነሳሳት መ. ለማስቆጣት

31. "አጠና "የሚለው ቃል ላልቶ ሲነበብ የሚሰጠው ፍች

ሀ.መረመረ ለ.ትኩረት ሐ.ወራጅ እንጨት መ.አስተዋለ

32.ልጁ ልብሱን በእናቱ________፡፡ከባዶ ቦታው መግባት ያለበት ግስ የቱ ነው?

ሀ.ታጠበ ለ.አጣጠበ ሐ.አጠበ መ.አሳጠበ

33.የመተባበር ሀያልነት ሊገልጽ የሚችለው ምሳሌያዊ አነጋገር የቱ ነው?

ሀ.አትኩራ ገብስ ጎመን ባወጣው ነብስ ለ.አተርፍ ባይ አጉዳይ

ሐ.በአንድ እጅ አይጨበጨብም መ.የረጋ ወተት ቅቤ ይወጣዋል

34.ከሚከተሉት አንዱ የህትመት መገናኛ ብዙሀን ነው።

ሀ.ሬዲዮ ለ.ቴሌቪዥን ሐ.መጽሔት መ.ሁሉም

35.ዓ.ነገሮች ከግስ ብዛታቸው አንጻር በስንት ይከፈላል?

ሀ. በአራት ለ.በሶስት ሐ. በሁለት መ.በአምስት36.ስጋ እበላ ብየ የቆረጥኩትን ፣
ላሳያችሁ መጣሁ እኔማጣቴን። በዚህ ግጥም ህብረ ቃሉ ምን የሚለው ነው?
ሀ.የቆረጥኩትን ለ.ላሳያችሁ ሐ.መጣሁ መ.እኔማ ጣቴን
37 "መነመነ " ለሚለው ቃል በሀሳብ የሚዛመደው የትኛው ነው?
ሀ.ከሳ ለ.አነሰ ሐ.ቀነሰ መ.ሁሉም
lv ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ስጥ ( ጭ "
38. የህይወት ስርጓጎጥ የሚለው ሀረግ ፈሊጣዊ ፍች ምንድን ነው ?
39. "ውሻ " በሚለው ቃል ተሳ አመልካች ዓ .ነገር መስርቱ።
40 .እያለለት መልኬ ካንገቴ በላይ፣
እጅ እጄን ያየኛል ያለም አታላይ። በዚህ ቅኔ ውስጥ ህብረ ቃሉን በመለየት የሰሙን ፍችእና የወርቁን ፍች ግለጡ

አዘጋጂ መ/ርት አጃኢባ መሀመድ

**በ2014 ዓ. ም በየዋኽንየ አጠ/2ኛ/ደረጃ ት/ቤት የመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት የ9ኛ ክፍል አማርኛ ትምህርት የማጠቃለያ ፈተና**

**የጥያቄ ብዛት 40**

**የተሰጠው ሰዓት 55 ደቂቃ**

I የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን እውነት ስህተት የሆነውን ሀሰት በማለት መልስ (ሽ)

1.ስነ_ቃል የምንለው በጽሁፍ የሰፈረውን ብቻ ነው።
2.ለስነ_ጽሁፍ መፈጠር አንዱ ምክንያት የሰው ልጅ ለውበት ያለው ፍቅር ነው።
3.ቋንቋ ሃሳብ መቀበያ እንጅ ማስተላለፊያ ሊሆን አይችልም።
4.ልቦለድ ከደራሲው ምናባዊ ፈጠራ የሚመነጭ ህይወትን በማመሳሰል የሚያቀርብ ነው።
5.የቃላት ፍካሬያዊና ፈሊጣዊ ፍች ተመሳሳይ ናቸው።
6.በአማርኛ ቋንቋ የሚጠብቁ ድምጾች የሚገኙት በቃል መካከልና መጨረሻ ነው።
7.ሐረግ እንደ ዓረፍተ ነገር ሙሉ መልእክት የሚያስተላልፍ ነው።
8.አርኬ (አንጓ)የተውኔት አላባውያን መሆን ይችላል።
9.ግጥምና ዝርው ሀሳብን በጽሁፍ የማቅረቢያ ቅርጾች ናቸው።
10.አንድ ጽሁፍ ስነ_ጽሁፋዊ ነው ለመባል በጽሁፍ መቅረቡ ብቻ በቂ አይደለም።
II.ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ምረጥ (ጭ)
11.ስነ_ጽሁፍን በተመለከተ ከሚከተሉት አንዱ ትክክል ነው።
ሀ.ስነ_ጽሁፍ እውነተኛ ገጠመኝ የሚንፀባረቅበት ነው። ለ.ስነ_ጽሀፍ የገሀዱ አለም ነጸብራቅ ነው
ሐ.ስነ_ጽሁፍ የተጻፈ ብቻ መ.ስነ_ጽሁፍ በዜማ ብቻ ይቀርባ
12.ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ስለ ቋንቋ ምንነት ትክክል ነው።
ሀ.መግባቢያ ሁሉ ቋንቋ ቋንቋ ነው። ለ.ቋንቋ ሁሉ በውሰት ስርዓት አያልፍም።

ሐ.ሁሉም ቋንቋ በቋንቋነቱ እኩል ነው። መ.ቋንቋ ስርዓታዊ እንጅ አንደበታዊ አይደለም።
13.በሁሉም የኢትዮጵያ ቋንቋዎች መልዕክት ለመቀበልና ለማስተላለፍ መሠረቱና ትንሹ የቋንቋ አሀድ_________ነው። ሀ.ቃል ለ.ምዕላድ ሐ.ድምፅ መ.ሀረግ
14.ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ለግል አስተያየት ምሳሌ ሊሆን ይችላል።
ሀ.ት/ት የዕድገት ሁሉ መሰረት ነው። ለ.ሙስና ከማጣት የሚመነጭ ነው።
ሐ.ማርፈድ የስንፍና ምልክት ነው። መ.የቤት ስራ መስራት የተማሪ ግዴታ ነው።
15.ስነ_ቃል ከሌሎች ከሌሎች የስነ_ጽሁፍ ዘርፎች የሚለይበት መሠረታዊ ባህሪ
ሀ.ተለዋዋጭ መሆኑ ለ.አውዳዊ መሆኑ ሐ.ደራሲ አልባ መሆኑ መ.ሁሉም
16.የአንድን አንቀጽ ቅርጽ ሊወስን የሚችለው______ነው። ሀ.የሀሳቡ አንድነት
ለ.የሀሳቡ ቁርኝት ሐ.የዓ.ነገር ብዛት መ.የሀይለ ቃል መገኛ ቦታ
17.ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ጠብቆና ላልቶ በመነበብ የትርጉም ለውጥ ያመጣል።
ሀ.ቤት ለ. ልጅ ሐ.ስራ መ.አያት
18.ልጁ በይተዋር ስለሆነ ልዩ ድጋፍ ያስፈልገዋል። የተሰመረበት ቃል ተመሳሳይፍች____ነው
ሀ.ሰነፍ ለ.መጤ ሐ.ፈሪ መ.እንግዳ
19.ከሚከተሉት ምሳሌያዊ አነጋገር ውስጥ አንዱ ሴቶችን ዝቅ የሚያደርግ ነው።
ሀ.ልጅ ያቦካው ለራት አይበቃም። ለ.ብርሌ ከነቃ አይሆንም እቃ።
ሐ.ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል መ.ምን ሴት ብታውቅ በወንድ ያልቅ።
20.ከዚህ በታች ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ አንዱ በውስጡ መስራች ምዕላድ አለው።
ሀ.ልጅ-ኡ ለ.ልብስ_ሀ ሐ.ደብተር-ሀ መ.ነገር-ኛ
21. ከዚህ በታች ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ አንዱ ባለአንድ ምዕላድ ነው።
ሀ.ተማሪነት ለ.ሴትነት ሐ.ወተት መ.ሰዎች
22.አንድን ጽሁፍ ጊዜ ወስደን ከቀደመ እውቀት ጋር በማዛመድ በስፋትና በጥልቀት አንበብን ለመረዳት የምንችልበት የንባብ ስልት_____ነው።
ሀ.የገረፍታ ለ.የአሰሳ ሐ.የፍጥነት መ.የምርምር(የዝግታ)
23._______አንድ ቃል በመዝገበ ቃላት ከሚሰጠው ፍች ባሻገር ያለው ፍች ሊሆንይችላል።
ሀ.ፍካሬ ለ.እማሬ ሐ.ቅኔ መ.ምሳሌ
24.አንድ ረጅም ልቦለድ ከአጭር ልቦለድ የሚለይበት አብይ ባህሪ
ሀ.ውስብስብነት ለ.ነጠላ ውጤት ሐ. ዜማዊነት መ. ቁጥብነት
25.ተማሪው ክፍል ገብቶ እየተማረ ነው። የዚህ ዓ.ነገር ማሰሪያ አንቀጽ የትኛው ነው?
ሀ.ነው ለ.ገብቶ ሐ.እየተማረ መ.ክፍል
26.ከዚህ በታች ከቀረቡት ዓ.ነገሮች መካከል መጠይቃዊ ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ.እባክህን ስሌዳውን አጥፋው ለ.አንተ መቼ ትሄዳለሀ
ሐ.ዛሬ የቤት ስራ አልተሰጠም መ.ለምን በስነ ምግባር አትሻሻልም
27.ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ለረጅምና አጭር ልቦለድ የጋራ ባህሪ መሆን ይችላል።
ሀ.እምቅነት ለ.ነጠላ ውጤት ሐ.ቁጥብነት መ.ምናባዊነት
28.ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የውይይት የመጨረሻ ግቡ መሆን ይችላል።
ሀ.ርዕሱን ለሌሎች ማስተዋወቅ ለ.የሌሎችን አቋም ማስለወጥ

ሐ.አድማጭን መቃኘት መ.የጋራ መግባባት ላይ ማድረስ
29.ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የምርጥ ንግግር መሠረታዊ ባህሪ ነው፡፡
ሀ.ስሜታዊነት ለ.ግልጸኝነት ሐ.አጭርነት መ.ወሰን አልባነት
30.ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ በምንባብ መረጃ የምናገኝበት የመገናኛ ብዙሃን አይነት ነው፡፡
ሀ.ቴሌቪዥን ለ.ሬድዮ ሐ.ስልክ መ.ጋዜጣ
31.ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ መካከል በስራ ደብዳቤ ቅርጽ የማይካተተው የቱ ነው?
ሀ.የተጻፈበት ጉዳይ ለ.የተጻፈለት ክፍል ሐ.የተጻፈበት ቀን መ.የተቀባይ ፊርማ
32.ድርሰት ከመጻፋችን በፊት አስተዋጽኦ መንደፍ ያስፈለገበት መሰረታዊ ምክንያት
ሀ.የድርሰት ምንነትን ለማሳየት ለ.ከድርሰቱ ሀሳብ ላለመውጣት
ሐ.የድርሰትን ርዕስ ለመወሰን መ.የድርሰት ማስፋፊያ ስልትን ለመወሰን
33.አንድ ፀሐፊ ጽሁፍ በሚጽፍበት ጊዜ መጀመሪያ ማከናወን ያለበት ተግባር የቱ ነው?
ሀ.ግብረ መልስ መስጠት ለ.ርዕስ መምረጥ ሐ.አስተዋጽኦ መንደፍ መ.ሀሳብማስፈር
34.የተለያዩ ተቃራኒ ሀሳቦችን ለማያያዝ የሚያገለግለው አያያዥ የትኛው ነው?
ሀ.ቢሆንም ለ.ስለሆነም ሐ.ስለዚህ መ.በመሆኑም
35.ከሚከተሉት መካካል የንግግር መመሪያ ዝግጅት ምዕራፍ ነው፡፡
ሀ.ርዕስ መምረጥ ለ.ርዕሱን ማስተዋወቅ ሐ.አላማውን መግለጽ መ.ጥያቄ መቀበል
36.በክርክር አቀራረብ ሂደት መጀመሪያ መምጣት ያለበት ነጥብ የትኛው ነው፡፡
ሀ.መረጃ መሰብሰብ ለ.ርዕስ መወሰን ሐ.ርእሱን ማስተዋወቅ መ.አስተያየትመቀበል
37."ካለመናገር ደጃዝማችነት ይቀራል"ለሚለው አባባል የበለጠ ቅርብ መሆን የሚችለው የቱ ነው? ሀ.መናገር ለ.መጻፍ ሐ.ማንበብ መ.ማዳመጥ
38.አበበች ወተቱን________ቅቤ አወጣች፡፡ ከባዶ ቦታው መግባት ያለበት የቱ ነው?
ሀ.ንጣ ለ.አፍልታ ሐ.አሙቃ መ. አቅልጣ
39.ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት አንዱ የህትመት መገናኛ ብዙሃን መሆን አይችልም፡፡
ሀ.ጋዜጣ ለ.መጽሄት ሐ.መጽሀፍ መ.ቴሌቪዥን
40.ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ከስነ-ቃል ዘርፎች ሊመደብ አይችልም ፡፡
ሀ.አፈ ታሪክ ለ.ግጥም ሐ.ተረት መ.ሀተታ ተፈጥሮ

አዘጋጂ መ/ር አበበ ጋሻው

**በ2014 ዓ.ም በየዋኸንየ አጠ/2ኛ/ደ/ ት/ቤት የሁለተኛው ወሰነ ትምህርት የ9ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ማጠቃለያ ፈተና**

**የጥያቄ ብዛት 40**

**የተሰጠ ጊዜ 50 ደቂቃ**

I. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን እውነት ስህተት የሆነውን ሀሰት በማለት መልስ / ሽ/
1.በተውኔት ታሪክ ውስጥ ሊተላለፍ የተፈለገው ዋና መልክት ትልም ይባላል፡፡
2.ልቦለድ ማለት ፀሃፊው በተጨባጭ እውነት ላይ ተመስርቶ የሚጽፈው ታማኒነት ያለው የጽሁፍ ዘርፍ ነው፡፡

3.ከድርጅት ወደ ግለሰብ የሚጻፍ ደብዳቤ የድርጅት ደብዳቤ በመባል ይታወቃል ።
4.የአንድን ነገር አይነት፣ መጠን ፣ባህሪና መልክ የሚገልጽ የቃል ክፍል ተውሳከግስይባላል።
5.ደብዳቤ በዋናነት በአራት (4 )ይከፈላል።
6.ቅኔ የንግግር ስልት ሲሆን የሚነገረው (የሚፃፈው)በሰም እና በወርቅ ነው።
7. "ሳቢያ" ለሚለው ቃል መዝገበ ቃላዊ ፍችው "ምክንያት" ነው።
8.በግጥም ውስጥ እያንዳንዱ ስንኝ ያለቀበት የመጨረሻ ፊደል ቤት ይባላል።
9. "አረጀ"ለሚለው ቃል ፈሊጣዊ ፍችው "ሰማንያ ጎሰመው " ነው።
10. ዓ.ነገር ከግስ ብዛታቸው አንፃር በአራት ይከፈላል።
Ⅱ.በ "ሀ"ስር የተዘረዘሩትን የልቦለድ አላባዊያንና የግጥም ሙያዊ ቃላትን በ" ለ"ስር ከሚገኙት ጋር ተስማሚ የሆኑትን አዛምዱ

| ሀ | ለ. |
|---|---|
| 11.በልቦለድ ውስጥ የድርጊት ቅደምተከተላዊ ሂደት | ሀ.ገፀባህሪይ |
| 12.በልቦለድ ውስጥ የመንስኤና ውጤት ትስስር | ለ.መቼት |
| 13.በአንድ ልቦለድ ውስጥ ወደ ፀብ የሚያስገባ አስገዳጅ ሁኔታ | ሐ.ቤት ደፊ |
| 14.በአንድ ልቦለድ ውስጥ የተለያየ ባህሪይ ወክለው | መ.ታሪክ |
| 15.በልቦለድ ውስጥ ሊተላለፍ የተፈለገው መልዕክት | ሠ.ጭብጥ |
| 16.በመነሻና በመድረሻ ሊከፈል ይችላል | ረ.አንፃር |
| 17.የልቦለዱ ታሪክ የሚከናወንበት ጊዜና ቦታ | ሰ.ሀረግ |
| 18.የግጥም የመጨረሻ ስንኝ የመጨረሻ ቃል | ሸ.ትልም |
| 19.የልቦለድ ጽሁፍ የሚቀርብበት ዘዴ | ቀ.ግጭት |
| 20.ፈጣንነት ጎልቶ የሚታይበትና ነጠላ ውጤት ያለው | በ.አጭር ልቦለድ |

Ⅲ.ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ምረጥ (ጭ)
21.የፈተና ጊዜ ደርሷል። ______ አላጠናችም።ባዶ ቦታውን ሊያሟላ የሚችል አያያዥየቱነው?
ሀ. ወደ ፊት ለ.ይሁን እንጅ ሐ.ከዚህ በላይ መ.ስለሆነም
22.እግር ኳስ እወዳለሁ _______ከቅርጫት ኳስ አይበልጥም።ከባዶ ቦታው መግባት ያለበት አያያዥ የቱ ነው? ሀ.የሆነ ሁኖ ለ.ስለዚህ ሐ.በዚያ ሳቢ መ.በመሆኑም
23.ሲበሉ የላኩት ለሚለው በፍች የሚስማማው የቱ ነው?
ሀ.ሰነፍ ለ.ችኩል ሐ.ተላላኪ መ.ወሬኛ
24."አሳት"ለሚለው ቃል ፍካሪያዊ ፍች የሆነው የትኛው ነው?
ሀ.ነበልባል ለ.የሚያቃጥል ሐ.ፈጣን መ.ነደድ
25.ቃላትን አሳጥሮ ለመፃፍ የሚገለግል ስርዓተ ነጥብ የቱ ነው?
ሀ.ሁለት ነጥብ ለ.ይዘት ሐ.እመጫት መ.ንኡስ ጭረት
26.ረጅም ለሚለው ቃል ፈሊጣዊ ፍች ________ነው።
ሀ.ብቅል አውራጅ ለ.ሰጎን ሐ.መሰላል መ.ሁሉም
27.የግጥም አንድ መስመር ተሳክቶ ሲያበቃ ______ይባላል።
ሀ.ስንኝ ለ.ሀረግ ሐ.ዓ.ነገር መ.ቀለም

28.በዓ.ነገር ውስጥ ሁለትና ከዚያ በላይ ግሶች ያሉት ዓነገር ____ይባላል።
ሀ.ውስብስብ ዓ .ነገር ለ.ተራ ዓ .ነገር ሐ.ትዛዛዊ ዓነገር መ.ሀተታዊዓ.ነገር
29. "ገና"የሚለው ቃል ጠብቆ ሲነበብ ያለው ፍች ___ነው።
ሀ.ክብረ በዓልን ለ.መዘግየትን ሐ.መጥበቅን መ.መልስ የለም
30.ዝምታን የሚያበረታታ ምሳሌያዊ አነጋገር የቱ ነው?
ሀ.ዝምታ ወርቅ ነው ለ.ዝም አይነቅዝም ሐ.መታፈር በከንፈር መ.ሁሉም
31".በለስ ቀናው" ለሚለው ሀረግ በፍች የሚስማማው የቱ ነው?
ሀ.ቸገረው ለ.ሀገሩ ገባ ሐ.ተሳካለት መ.ቸኮለ
32.በተውኔት ውስጥ በምክንያትና ውጤት የተሳሰረ የታሪክ ቅደምተከተል ምን ይባላል?
ሀ.መቼት ለ.ጭብጥ ሐ.ትልም መ.ግጭት
33. የሰዎች ማህበራዊ ህይወት በመድረክ ላይ በድርጊት የሚያሳይ የስነ_ጽሁፍ ዘርፍ_____
ነው። ሀ.ልቦለድ ለ.ኢ_ልቦለድ ሐ.ተውኔት መ.ሜሎ ድራማ
34." ተውሳክ" ለሚለው የግዕዝ ቃል ትርጉም _____ነው።
ሀ.አዲስ ለ.ጭማሪ ሐ.ንዑስ መ.አብይ
35.የሴት አጭር "ሴት ወይዘሮ" ከተባለ የወንድ አጭር "____"ይባላል።
ሀ.ስንዝሮ ለ.አውራ ዶሮ ሐ.ወንድ አማሮ መ.ሁሉም
36.የግለሰብ ደብዳቤ ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ.የግብዣ ደብዳቤ ለ.የፍቅር ደብዳቤ ሐ.የሰላምታ ደብዳቤ መ.የቅጥር ደብዳቤ
lv.ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛና አጭር መልስ ስጥ (ጭ)
37.የጅብ ችኩል_______።
38.የአነጋገር ስልቶች___፣____፣____እና____ናቸው።
39.ቅኔ የተመሰረተበት ቃል______ይባለል።
40.የቃል ክፍሎች____፣_____፣_____፣_____እና_____ናቸው።

አዘጋጅ መ/ር አበበ ጋሻው

# አባሪ ሁለት

## ለመምህራን የቀረበ ቃለ መጠየቅ

የቃለ መጠየቁ ዋና ዓላማ ለ2013 እና 2014ዓ.ም ዓ.ም ለዘጠነኛ የክፍል ደረጃ የዐማርኛ ቋንቋ ማጠቃለያ ፈተናዎች የይዘት ተገቢነት ምን እንደሚመስል መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ ይህን መረጃ መሰብሰብ ያስፈለገበት ምክንያት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የማህበራዊ ሳይንስና ስነሰብ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ስነ-ፅሁፍ - ዐማርኛ ትምህርት ክፍል ለድህረ ምረቃ መርሀ ግብር ጥናታዊ ፅሁፍ ለማዘጋጀት ነው፡፡ በመሆኑም ከመጠይቁ

የሚገኘው መረጃ ለተጀመረው ጥናት መሳካት ከፍተኛ ሚና አለው፡፡ ይህ የሚሆነው ደግሞ የእርሶዎ ቀና ትብብርሲታከልበት ነው፡፡

ውድ መምህራን ለቃለ መጠይቁ ፍቃደኛ በመሆኖዎ አስቀድሜ ከልብ አመሰግናለሁ

1. የሚዘጋጁት ፈተናዎች ከመማሪያ መጽሃፉ ጋር ግንኙነት አላቸው?
2. መርሀ ትምህርትና መማሪያ መፅሃፍ ፈተና ለማውጣት እገዛ አላቸው?
3. በመርሀ ትምህርቱና በመማሪያ መፅሃፍ ሰፊ ትኩረት የተሰጣችው ይዘቶች አሉ?
4. ፈተናዎች ከተዘጋጁ በኋላ ተመጣጥኗቸውንና ውካይነታቸውን ለማረጋገጥ ግምገማ ይደረጋል?
5. በፈተናው በመርሀ ትምህርትና በመማሪያው መፅሃፍ ስፊ ሽፋን የተሰጣቸው ይዘቶች ተገቢውን ትኩረት አግኝተው ቀርበዋል?
6. በመርሀ ትምህርቱና መማሪያ መፅሀፉ ሽፋን የተሰጠው ይዘት አለ ይላሉ?
7. በመርሀ ትምህርቱና መማሪያ መፅሃፉነኖርው ወይም እያሉ በፈተናው ያልተካተቱ ይዘቶች ይኖራሉ? ለምን
8. ፈተናው የሁሉም ይዘቶች ወካይ እንዲሆን ምን ምን መንገዶች ትከተለላቸው?
9. ፈተናው በመርሀ ትምህርቱና መማሪያ መፅሃፉ የቀርቡትን ሁሉንም ይዘቶች እንደ ትኩረት ደረጃቸው ወክሏል ይላሉ?
10. የሚዘጋጁት ፈተናዎች ጥንካሬና ድክመት በትምህርት ክፍሉ ተፈትሸው ግብረ መለስ ለአዘጋጆች ይሰጣል?
11. ፈተናዎቹ የፈተና መርዎዎችን ባከበረ መልኩ እነዲዘጋ የሚደረግ ጥረት አለ? ለፈተና አዘጋጆች ዐጭር ስጠና ሰጣል?
12. የፈተናውንና አዘገጃጀት በተመለከተ ተጨማሪ ሃሳብ ካለዎት ሲሰጡኝ?